# ማውጫ


መቅድም……………………………………………………………………… iii

አጠቃሎ (Exceutive Summary)........................................................ vi

1. መግቢያ …………………………………………………………….... 1

1.1 የጥናቱ ቱራ …………………………………………...………... 2

1.2 በጥናቱ ምላሽ ያገኙ ጥያቄዎች……………………………........... 5

1.3 የጥናቱ ዓላማ ……………………………………………….…..... 6

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ……………………………………………….…..... 7

1.5 የጥናቱ ወሰን……………………………………………………....... 8

1.6 የጥናቱ ውጤቶች ..................................................................... 8

8

2. የጥናቱ □ጸ ……………………………………………….................

2.1 የጥናቱ ዲዛይን 9

………….………………………………………......

2.2 የመረጃ ምንጮች ………..….……………………….….…... 10

2.3 የተቋማትና የመላሾች አመራረጥ……..…………………….…..... 10

2.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ……………………………… 12

2.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተገቢነት ……………..... 13

2.6 የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ……………….……….......... 14

2.7 የመረጃ ትንተና ዘዴዎች…………………..………………… 15

2.8 የቅድመ ጥናት ሙከራ (Pilot Test) እና የተገኙ ውጤቶች … 16

2.9 የጥናቱ ውስንነትና ያጋጠሙ ችግሮች …..…………………….. 18

3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ……………………………………...... 18

3.1 መግቢያ ……………………………..…………………….. 18

3.2 የሙስና ደረጃ ቅርጽና ይዘት …………………………………. 23

3.3 ሙስናን ለመዋጋት የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርትና
ሥልጠና ያለው ሚና ........................................... 29
3.4 የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴዎች (ጅምሮች) በኢትዮጵያ............. 35
4. ሙስና እና ሕግ ........................................................ 38
4.1 መግቢያ ............................................................ 38
4.2 የሕጐች አጠቃላይ ይዘትና ሙስናን ለመከላከልና
ለመቆጣጠር የሚኖራቸው ፋይዳ.................................... 41
4.3 የሙስና ችግሮች እና የመከላከልና የመቆጣጠር አስፈላጊነት 52
4.4 የሙስና ወንጀልንና ብልሹ አሠራርን የመከላከል ምንነት ..... 56
5. የጥናቱ ግኝቶች .................................................... 64
5.1 መፅቢጸ ............................................................ 64
5.2 መረጃ ለመሰብሰብ ሥራ ላይ የዋሉ መሣሪያዎችና የተገኙ
ምላሾች ............................................................ 66
5.3 የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርትና ሥልጠናን በተመለከተ 66
5.3 የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በማቋቋምና በማገዝ
ኮሚሽኑ የተጫወተውን ሚና በተመለከተ ........................ 81
5.4 የአሰራር ሥርዓት ጥናትን በተመለከተ ........................... 84
5.5 የሙስና ወንጀልን በመመርመር፣ በማጋለጥና በመክሰስ ረገድ 96
5.6 ስለ ኮሚሽኑ እንቅስቃሴ አጠቃላይ እይታ ........................ 103
6. ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት .............................. 113
6.1 ማቷቃለጸ ............................................................ 113
6.2 መ□ም□ሚጸ ........................................................ 117
6.3 አስተያየት........................................................... 118
7. ዋቢ መጽሐፍትና ሠነዶች .............................................. 121
8. አባሪዎች................................................................ 123

# መቅድም

የሙስና ወንጀል የሀገርን ልማትና ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ ከመሆኑም ባሻገር የመንግሥትንና ማህበራዊ ተቋማትን ተአማኒነት የሚያጠፋ በመሆኑ መልካም ሥነምግባርን የማስፋፋት፣ ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ተልዕኮን ለማስፈጸም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ቀርጾ በተደረገው እንቅስቃሴ የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ግንቦት 16 ቀን 1993 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 235/1993 ተቋቁሟል፡፡

የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሥራውን ሲጀምር በሲቪል ሰርቪሱ ማሻሻያ ፕሮግራም የሥነምግባር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም አማካኝነት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም በ1993 ዓ.ም የተጠናው የመጀመሪያው የሙስና ቅኝት ጥናት ያስገኘውን ውጤት ግምት ውስጥ በማስገባት ሙስናን የመታገያ ልዩ ልዩ ስልቶችን ቀይሶ በርካታ የፀረ-ሙስና ተግባራትን አከናውኗል፡፡ ሙስና በሀገሪቱ ያለበትን ደረጃና ባሕሪይ በመገንዘብ የሙስና መታገያ ስልቶችን ለመቀየስ እንደሚረዳ ሁሉ ሙስናን ለመዋጋት የተደረጉና በመደረግ ላይ ያሉ ጥረቶች ያስገኙትን ውጤት ማጥናት ለቀጣዩ ትግል ተገቢውን ስልት ለመንደፍና በትክክለኛው አቅጣጫ ለመጓዝ አስፈላጊ ነው፡፡

ኮሚሽኑ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት የተለያዩ የሙስና መታገያ ስልቶች ቀይሶ በርካታ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴዎችን ያከናወነ ቢሆንም የተደረጉ ጥረቶች ያስገኙትን ውጤት ለማወቅ ጥናት ባለመደረጉ የዚህ ጥናት መካሄድ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

ይህ ጥናት ስድስት ምዕራፎችን ይዟል፡፡ እነሱም መግቢያ፣ የአጠናን ዘዴ፣ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት፣ ሙስናና ሕግ የጥናቱ ግኝቶችና የጥናቱ ማጠቃለያ መደምደሚያና አስተያየት ናቸው፡፡ በመጨረሻም ዋቢ መጽሐፍትና ሰነዶች እንዲሁም ተቀጥላዎች (መጠይቆች) ተካተዋል፡፡

ኮሚሽኑ ጥናቱ ገለልተኛ በሆነና ተመሳሳይ ጥናቶችን በማካሄድ ልምድና አቅም ባለው ተቋም ቢካሄድ ውጤቱ ደረጃውን የጠበቀና ተአማኒነት ያለው መሆን እንደሚችል በማመን ከራሱ ውጭ በሆነ አካል እንዲጠና በወሰነው መሠረት ጥናቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተካሂዷል፡፡ ይህ ጥናት የፌደራል ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በጥናትና ምርምር ሥራዎችና በአቅም ግንባታ በጋራ ለመሥራት ነሐሴ 4 ቀን 2002 ዓ.ም በተፈራረሙት የጋራ መግባቢያ ሰነድ መነሻነት ጥቅምት ወር 2003 ዓ.ም ተጀመረ፡፡

ለዚህ ጥናት መሳካት አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች በኮሚሽኑ በኩል በዲሞክራቲክ ተቋማት ፕሮግራም የተሸፈኑ ነው፡፡

ኮሚሽኑ ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት በፀረ-ሙስና ትግል ባከናወናቸው ተግባራት ያስገኘውን ውጤት ለማስጠናት በወሰደው ተነሳሽነትና አስፈላጊውን ወጪ የመሸፈን ፈቃደኝነት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ካለው ከፍተኛ ልምድና የሰው ኃይል አንጻር የተቋማትን አቅም ለመገንባትና በጥናትና ምርምር መስክ ለሚያደርጋው እገዛና ድጋፍ በተለይም ይህን ጥናት ለማካሄድ ባደረገው ፈቃደኝነት ተመስጋኝ ይሆናል፡፡

ጥናቱ በዩኒቨርስቲው የሥነምግባር ጽ/ቤት አስተባባሪነት በተቋቋመው 7 ከፍተኛ ልምድና ዕውቀት ባላቸው አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት እየተመራ ሁለት ዋና አጥኚዎች፣ ሦስት ረዳት አጥኚዎች፣ ሁለት የስታትስቲክስ ባለሙያዎችና ሦስት የመረጃ አቀናባሪዎች ተሳትፈዋል፡፡ እነሱም፤ የጥናቱ አስተባባሪዎች ዶ/ር እንጉዳይ አደመ፣ ዶ/ር ወሰኑ ይማምና አቶ በዛብህ ታምሩ፤ ዋና አጥኚዎች ፕ/ር ሀብታሙ ወንድሙና ዶ/ር አበጀ ብርሃኑ፤ ረዳት አጥኚዎች አቶ ሞላ መንግሥቱ፣ ዶ/ር ዋና ሌቃ እና አቶ በኩረ ከተማ፤ የስታትስቲክስ ባለሙያዎች ዶ/ር ስለሺ ዘለቀና አቶ ታምሬ አንዱዓለም እንዲሁም የመረጃ አቀናባሪዎች አቶ አበባው ምናየ፣ አቶ ወንድማገኝ ቱጅና አቶ ካሣሁን ሀብታሙ ናቸው፡፡ እነዚህ የጥናት ቡድኑ

አስተባባሪዎችና የጥናት ቡድኑ አባላት ለጥናቱ መሳካት ላበረከቱት ሙያዊ ሥራ በከፍተኛ ደረጃ ባለውለታ ናቸው፡፡

ለዚህ የጥናት ሥራ ሱፐርቫይዘሮች፣ መረጃ ሰብሳቢዎች፣ መረጃ በመስጠት የተባበሩና የተሳተፉ የፌደራል የመንግሥት መ/ቤቶች፣ የፌደራል የመንግሥት ልማት ድርጅቶች፣ በየደረጃው ያሉ የአዲስ አበባ ከተማና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ የሲቪክ ማህበራት፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ት/ቤቶችና የመጀመሪያ ት/ቤቶች ኃላፊዎችና ሠራተኞች ምስጋና ይድረሳቸው፡፡

# አጠቃሎ (Executive Summary)

## መግቢያ

*የሙስና ወንጀል የሀገርን ልማትና ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ ከመሆኑም ባሻገር የመንግሥትንና ማህበራዊ ተቋማትን ተአማኒነት የሚያጠፈ በመሆኑ መልካም ሥነምግባርን የማስፋፋት፣ ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ተልዕኮን ለማስፈጸም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ቀርጾ በተደረገው እንቅስቃሴ የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ግንቦት 16 ቀን 1993 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 235/1993 ተቋቁሟል፡፡*

*የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሥራውን ሲጀምር በሲቪል ሰርቪሱ ማሻሻያ ፕሮግራም የሥነምግባር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም አማካኝነት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም በ1993 ዓ.ም የተጠናው የመጀመሪያው የሙስና ቅኝት ጥናት ያስገኘውን ውጤት ግምት ውስጥ በማስገባት ሙስናን የመታገያ ልዩ ልዩ ስልቶችን ቀይሶ በርካታ የፀረ-ሙስና ተግባራትን አከናውኗል፡፡ ሙስና በሀገሪቱ ያለበትን ደረጃና ባሕሪይ በመገንዘብ የሙስና መታገያ ስልቶችን ለመቀየስ እንደሚረዳ ሁሉ ሙስናን ለመዋጋት የተደረጉና በመደረግ ላይ ያሉ ጥረቶች ያስገኙትን ውጤት ማጥናት ለቀጣዩ ትግል ተገቢውን ስልት ለመንደፍና በትክክለኛው አቅጣጫ ለመጓዝ አስፈላጊ ነው፡፡*

*ኮሚሽኑ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት የተለያዩ የሙስና መታገያ ስልቶች ቀይሶ በርካታ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴዎችን ያከናወነ ቢሆንም የተደረጉ ጥረቶች ያስገኙትን ውጤት ለማወቅ ጥናት ባለመደረጉ የዚህ ጥናት መካሄድ አስፈላጊ ሆኗል፡፡*

ይህ ጥናት ስድስት ምዕራፎችን ይዟል:: እነሱም መግቢያ፣ የአጠናን ዘዴ፣ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት፣ ሙስናና ሕግ የጥናቱ ግኝቶችና የጥናቱ ማጠቃለያ መደምደሚያና አስተያየት ናቸው:: በመጨረሻም ዋቢ መጽሐፍትና ሰነዶች እንዲሁም ተቀጥላዎች (መጠይቆች) ተካተዋል::

## በጥናቱ ምላሽ ያገኙ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ዋና ዋና ጥያቄዎች መልሷል፤

1. በሥነምግባር ትምህርት የተሠሩ ሥራዎች በህብረተሰቡ ዘንድ መልካም ሥነምግባርን በማስረፅ እና ሙስናን የማይሸከም ዜጋን ከመፍጠር አኳያ ምን ያህል የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጥ አምጥተዋል?
2. ብልሹ አሠራርን እና ሙስናን በመከላከል የተከናወኑ ተግባራት በተቋማት ዘንድ ያስከተሉት □መልካም የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጥ ምን ያህል ነው?
3. በሙስና ወንጀል ምርመራ እና ለሕግ በማቅረብ የተሠሩ ሥራዎች በህብረተሰቡ ዘንድ ያመጡት ፀረ-ሙስና የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦች ምን ያህል ናቸው?
4. በፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተሠሩ ሥራዎች በህብረተሰቡ ዘንድ አወንታዊ የሆነ የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦች ምን ያህል አምጥተዋል፤
5. የሥነምግባር ትምህርትን በማስፋፋት፣ ሙስናን በመከላከል እና የሙስና ወንጀልን በመመርመር በማጋለጥና ለሕግ በማቅረብ የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጥንካሬዎች እና ጉድለቶች ምንድን ናቸው?

## የጥናቱ ዓላማ

የዚህ የተፅዕኖ ትንተና (Impact Assessment) ጥናት ዋና ዓላማ በፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ላለፉት ዘጠኝ (1994-2002) ዓመታት በሥነምግባር ትምህርት፣ በሙስና መከላከል እና የሙስና ወንጀሎችን በመመርመር እና ለሕግ በማቅረብ የተሠሩ ሥራዎች በተቋማትና በህብረተሰቡ ዘንድ መልካም ሥነምግባርን በማስረፅ እና የሙስና ችግሮችን በመቅረፍ ያስገኙትን የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦችን ለመገምገም ነው፡፡

# የጥናቱ ዘዴ (Methodolgy)

የዚህ ጥናት መላሾች ብዛት 3048 (27% ሴቶች) ሲሆን የየተቋማት መላሾች የተመረጡበት ዘዴ ዓላማ ተኮር ዘዴ (Purposive Sampling) ነው። ይህንንም ዘዴ በመጠቀም የተቋማት ኃላፊዎችና በኃላፊዎች ሥር ያሉ ባለሙያዎች እንዲሁም የሥነምግባር መኮንኖች ተሳታፊ ሆነዋል።

ምንም እንኳ ከአጠቃላይ 1381 ተቋማት መካከል ለጥናቱ በናሙናነት የተመረጡት ተቋማት 210 ቢሆኑም የናሙና አመራረጡ ኮሚሽኑ ከልማትና ዲሞክራሲ ግንባታ ስትራቴጂ አንጻር ቁልፍ ሚና የሚጫወቱና ለሙስናና ብልሹ አሠራር በመጋለጣቸው በአጠቃላይ በተያዘው የልማትና ዲሞክራሲ ጎዳና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርሱ በሚችሉ ከፍተኛ የመንግሥት ገንዘብ፣ የሰው ኃይልና ንብረት የሚንቀሳቀስባቸው ተቋማት በተለይም፤

- ገቢ ሰብሳቢ
- የፋይናንስ
- የመሠረተ ልማት
- ልማታዊ ባለሀብትን በማሳደግ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ
- በጤናና በትምህርት ዘርፍ

በተሰማሩ ተቋማት የቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ በሠራባቸው ከመሆኑ አንጻር ሲታይ የተወሰደው ከየምድቡ የተቋማት ናሙና ቁጥር ተገቢ ነው።

ይህን ጥናት ለማካሄድ አራት ዓይነት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በተግባር ላይ የዋሉ ሲሆን እነሱም፤

1. □□ሑአ መጠይቆች፣
2. ቃለመጠይቆች፣
3. ቡድን ተኮር ውይይቶች (FGD) እና
4. ሰነዶች ናቸው።

## የጥናቱ ግኝቶች

በአኃዝ የተደገፉም ሆኑ በአኃዝ ያልተደገፉ መረጃዎች ከተጠናቀሩ እና ከተተነተኑ በኋላ የሚከተሉትን ግኝቶች ጥናቱ አመላክቷል፡፡

1. በኮሚሽኑ የወጣ መረጃ □ንደሚያሳየው ባለፉት የ9 ዓመ□ት ጊዜ 1500 የሚሆኑ የሙስና ወንጀሎችን በማጣራትና በመመርመር ባብዛኞዎች ላይ ክስ መስርቶ 520 የሚሆኑ ተከሳሾችን አስቀጥቷል፡፡

2. ከጽሑፍ መጠይቅ ከተገኙ አጠቃላይ መረጃዎች አንዱ ባለፉት ዘጠኝ □መታት ውስጥ ሙስና ስለመቀነሱና አለመቀነሱ ጉዳይ ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ መልስ ከሰጡ 2577 ሰዎች ውስዓ ወ□ ፅማሽ የሚጠጉት 55.7% መወሰን አልችልም ሲሉ 33.3% ቀንሷል ብለዋል፡፡ የተቀሩት 12% አካባቢ ጨምሯል ወይም ለውጥ አላሳየም ብለዋል፡፡

3. የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ትምህርትና ሥልጠናን በተመለከተ ኮሚሽኑ የሚሰጠውን የአጭር ጊዜ ስልጠና 40 በመቶ የሚሆኑት የጥናቱ ተሳ□ፊዎች የሚያውቁ ሲሆን ቀሪዎቹ የዚህ ዓይነት ሥልጠና ለመስሪያ ቤ□ቸው ኃላፊዎችና ሠራተኞች አለመሰጠቱን ወይም መስጠቱን አለማወቃቸውን ቆልጸዋል፡፡ በኮሚሽኑ ትምህርት አሰጣጥ ዙሪያ አሉ ያሏቸውን ችግሮች □ንዲገልጹ በተጠየቁት መሠረትም ተሳ□ፊዎች ትምህርቱ ተከ□□ይነት እና ዘላቂነት እንደሌለው፣ የትምህርቱ አቀራረብ ሳቢ አለመሆኑን እና በሬዲዮና በቴሌቪዥን ብቻ ከሚሰጥ ይልቅ ትምህርቱን በአካል ወደ ህብረተሰቡ ወርዶ መስጠት □ንዳለበት □ንዲሁም ሰው በብዛት በሚገኝባቸው □ንደ ትምህርት ቤቶችና የሀይማኖት ማራመጃ ቦ□ዎች በመሳሰሉ ተቋማት ሁሉ ትምህርቱ መሰጠት □ንዳለበት ገልጸዋል፡፡ በሙያው የሰለጠኑና የማስተማር ክህሎት ያላቸው ሰዎች ስልጠናውን ቢሰጡ የተሻለ ውጤት ሊጸመ□ □ንደሚችልም ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ለስልጠናው የሚሆኑት ርዕሶች በጥንቃቄ ቢመረጡና በድራማ፣ በጭውወት፣ በዝማሬ □ና በዶክመን□ሪ ኻልም ቢቀርብ □ተሻለ ውጢት ያመጣል ብለው □ንደሚያምኑ፤

4. የስልጠናውን ጊዜ በቂነት በተመለከተ ተሳታፊዎች የተለያየ ሀሳብ እንዳላቸው ግኝቱ ያሳየ ሲሆን ከፍ ያለ ቁጥር ያላቸው (74 በመቶ ተሳ□ፊዎች) ቷ□ዉ በቂ አለመሆኑን ወይም መወሰን እንደማይችሉ ቶል□ዥል፡፡ በ□ህም ረቶት ኮሚሽኑ ሥልጠና ወደፊት ለመስጠት ሲያቅድ የጊዜውን በቂነት መመርመርና ማሻሻል □ንዳለበት ጥናቱ ያመላክ□ል፡፡

5. የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርቱ ወይም ስልጠናው በመስሪያ ቤቶች ውስጥ መልካም ሥነ ምግባርን ለማስረጽ ምን ያህል □ንደረቴ □ንቷቶል□ ተጠይቀው አብዛኞቹ (44 በመቶ) አዎን□ዊ መልስ □ሰቷ ሲሆን ሌሎች (41 በመቶ) □ንዲሁ □ርዕቷኛ መሆን እንደማይችሉ ገልፀዋል፡፡ አዎንታዊ መልስ ከሰጡት መካከል ትምህርት ከተሰጠው ህብረተሰቡ የአመለካከት ለውጥ የማያመጣበት ምክንያት እንደሌለ፣ ኮሚሽኑ ከተቋቋመ በኋላ በህብረተሰቡ ዘንድ የአመለካከት ለውጥ □ንደታየና በአንዳንድ መስሪያ ቤቶች እየተወሰዱ ጸሉ እርምጃዎች አስተማሪ እንደሆኑ በመግለጽ ስልጠናው ያመጣውን ለውጥ በማስረጃ አቅርበዋል፡፡

6. □ሥነምግባርና ናረ-ሙስና ትምህርትና ሥልጠና ጸቶኙበትን ዘዴ ተጠይቀው አብዛኞቹ (43.9 በመቶ) የጥናቱ ተሳ□ፊዎች በሬዲዮና በቴሌቪዥን አማካኝነት ያገኙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

6. ኮሚሽኑ በየመስሪያ ቤቱ የተለያዩ የሥራ ዘርፎች አሠራር ላይ ጥናት ማካሄድ አለማካሄዱን ተጠይቀው ጥያቄውን ከመለሱት ውስጥ 35 በመቶው ባለፉት ዘጠኝ ዓመ□ት ኮሚሽኑ የተለያዩ ጥናቶችን እንዳካሄደ ጠቁመዋል፡፡ የጥናቶቹ ትኩረትም በዕቃ ግዥ፣ በፋይናንስ፣ በሠራተኛ አስተዳደር፣ በንብረት አጠቃቀምና ደንበኞች መስተንግዶ ላይ □ንደነበር የጥናቱ ወጤት አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም 67 በመቶ የሚሆኑት ተሳ□ፊዎች ሙስናን ከመከላከል አንፃር የተደረገው ጥናት ቷቃሚ □ንደነበርና ጥናቱም በጣም አስፈላጊ መሆኑን □ንደሚያምኑበት ቶል□ዥል፡፡

8. ኮሚሽኑ የሚያጠናቸው ጥናቶች □ና የሚያቀርባቸው የመፍትሔ ሀሳቦች □ንዲተገበሩ የጥናቱ ተሳ□ፊዎች ካቀረቧቸው ሀሳቦች መካከል 1/ የአፈፃፀም ክትትል ማድረግ 2/ ለሰራተኞች የሚቀርቡትን የመፍትሔ ሐሳቦች በግልፅ ማሳወቅ □ና 3/ ከሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል መድረክ ኮሚሽኑ ሊኖረው ይገባል የሚሉ ይገኙበ□ል፡፡

9. በኮሚሽኑ ምርመራ የሚያስፈልጋቸው ሙስና - ነክ ሁኔ□ዎች በመስሪጸ ቤ□ቸው መከሰቱን ተጠይቀው አብዛኞቹ (44.8 በመቶ) መከሰቱን የገለፁ ሲሆን በቁጥር አነስ ያሉ (20.1 በመቶ) ተሳ□ፊዎች ግን እንዳልተከሰተ ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ በማያያዝም ኮሚሽኑ የሙሰኞችን ወንጀል መመርመሩን፣ መክሰሱንና ማስቀጣቱን ያውቁ □ንደሁ ተጠይቀው ብዙዎቹ መልስ ያልሰጡ ሲሆን ከሰጡት ውስጥ ግን ኮሚሽኑ መመርመሩን □ና መክሰሱን ግን አለማስቀጣቱን በዛ ያሉት ገልጸዋል፡፡

10. ኮሚሽኑ በድርጅቶች ውስጥ ሙስና ሲፈጸም መረጃ □ንዴት ይደርሰዋል ለሚለው ጥያቄ ከመለሱት ውስጥ አብዛኞቹ (55.5 በመቶ) በጥቆማ መሆኑን ወጁም መረጃው □ንደሌላቸው (22.7 በመቶ) ገልፀዋል፡፡

11. አብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳ□ፊዎች ኮሚሽኑ መልካም ሥነ - ምፅባር በማስረ□ ውጤ□ማ መሆኑን (62.5 በመቶ) ያመኑ ሲሆን ሙስናን በመከላከልም ረገድ ኮሚሽኑ (53.3 በመቶ) ውጤ□ማ ነው ብለው □ንደሚያምኑ ገልጸዋል፡፡ በአጠቃላይ የጥናቱ ተሳ□ፊዎች የኮሚሽኑን ውጤ□ማነት በተመለከተ የሰጡት ግምገማ አበረታች እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በዛ ያሉ ጥያቄዎች ላይ ግን ብዙ ተሳ□ፊዎች መረጃው እንደሌላቸው ወይም መወሰን □ንደማይችሉ ገልፀዋል፡፡

## አስተያየት (Recommendations)

በዚህ ጥናት ከተደረሰባቸው ግኝቶች እና መደምደሚያዎች በመነሳት የሚከተሉትን በኮሚሽኑ ሊተገበሩ የሚገባቸውን አስተያየቶች ለመሰንዘር እንወዳለን፡፡

1. ብዛት ያላቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደገለፁትና በልምድም እንደሚታወቀው የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርትና ሥልጠና

አመለካከትን በመለወጥ መተኪያ የሌለው መንገድ ነው፡፡ ስለሆነም ትምህርቱ በተከታታይነት ወይም ዘላቂነት ባለው መንገድ ለሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች መዳረስ አለበት፡፡ ይህ ከተደረገ ሙስናን የሚጠየፍ እና በስነ-ምግባር የጎለበተ ዜጋን በማፍራት ሙስናን ከስር መሰረቱ ማጥፋት ይቻላል፡፡

2. ሌላው ኮሚሽኑ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያለበት በትምህርቱ አቀራረብ ዙሪያ ነው፡፡ ትምህርቱ የተለያዩ ተግባራዊ ልምዶችን እና ተሞክሮዎችን በማቅረብ ከተቻለ ስነ-ጥበባዊ በሆነ መልኩ ካልተቻለ ደግሞ የተለያዩ መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም በማያሰላችና ሳቢ በሆነ መልኩ መሰጠት ይኖርበታል፡፡ የትምህርቱ አሰጣጥ ዘዴም ከላይ ወደ ታች እና እውቀትን እና መረጃን በማስተላለፍ መልኩ ሳይሆን አሳታፊና ውይይትን የተመረኮዘ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. በሚዲያ የሚተላለፉ ማስታወቂያዎችና ድራማዎች የጎንዮሽ አሉታዊ ውጤት እንዳይኖራቸው ጥንቃቄ ቢደረግ የተሻለ ይሆናል፡፡ ከመለቀቃቸው በፊት በየዘርፉ ያሉ ባለሙያዎች ግምገማ የሚያደርጉበት አሰራር ቢመቻች የተሻለ ይሆናል፡፡ እነዚህ የማስተማሪያ ስልቶች ጠቀሜታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሕብረተሰቡን ባህል እና ወግ ያገናዘቡና የተለያየ የዕድሜ ክልልን ያገናዘቡ ቢሆን የተሻለ ይሆናል፡፡
4. የፊት ለፊት ስልጠና በሚሰጥበት ጊዜ አሰልጣኞች በዘርፉ ትምህርት ያላቸው፣የማስተማር ክህሎት እና ስልጠና ያላቸው እንዲሁም ሞዴል ሊሆኑ የሚችሉና ልምድ ያላቸው ቢሆኑ ትምህርቱ ለውጥ የሚያመጣ እንዲሆን የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡
5. ኮሚሽኑ በየመስሪያ ቤቱ የአሰራር ሥርዓት መሻሻል □ንዲኖር የሚያጠናቸው ጥናቶች □ና የሚያቀርባቸው የመፍትሄ ሐሳቦች መተግበራቸውን ኮሚሽኑ ክትትል በማድረግ □ርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ የአሰራር ሥርዓት ጥናት በማትረፅ እና የመፍትሄ ሐሳቦችን በመስጠት ኮሚሽኑ አበረታች ሥራ እያከናወነ እንደሆነ ይህ ጥናት ያመለክታል፡፡ ነገር ግን በዓ ናቱ መሰረት የሚቀርቡት የመፍትሄ አቅጣጫዎች ምን ያህል □□ተተቹሩ እንደሆነ ክትትል በማድረግ በኩል ክፍተት ስላለ በዚህ በኩል ለዉዓ ቢ□ረፅ፡፡ ጁህም □ንዲሆን የመፍትሄ ሐሳቦችን ለሰራተኞች ማሳወቅ፤ የሙያ □ገዛ ማድረግና □ትትል በማድረግ አስፈላጊውን □ርምጽ መዉሰት ጁቷበቅበ□ ል፡፡

6. የሙስና ወንጀለኞችን በመመርመርና በማስቀጣት በኩል ኮሚሽኑ ለጠቋሚዎች አስተማማኝ የሕግ ከለላ መስጠት አለበት። ጠቋሚዎች አስተማማኝ ከለላ ከሌላቸው በግልፅ የሚ□ዩትን ወንጀል ደፍረው ለመጠቆም ጁ□ራሉ።
7. የሙስና ወንጀሎችን በመመርመርና በማስቀጣት ሂደት አንዳንዴ ንፁሐን □የተጎዱ መሆኑ በጥናቱ ታይቷል ኮሚሽኑ ችግሩን ሙሉ ለሙሉ ለመቅረአ አስቸጋሪ ቢሆንም የሚችለውን ያህል ጥንቃቄ ቢያደርግና ችግሩ የሚቀነስበትን አቅጣጫ አጥንቶ ተግባራዊ ቢያደርግ።
8. የሙስና ወንጀለኞችን የመመርመሩና የማስቀጣቱ ሂደት ረጅም □ና ብዙ ጊዜን የሚወስድ በመሆኑ ይህንንም ችግር ለመቀነስ ከሚመለከ□ቸው ጋር (ለምሳሌ፣ ከፍትሕ አካላት ጋር በመሆን) ጥናት ተደርጎ የመፍትሄ አቅጣጫ ቢ□ፈሩ።
9. ይህ ጥናት እንደሚያሳየው ኮሚሽኑ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትና የፖለቲካ ተሿሚዎችን "□ንደሚፈራና" በዚህ አካባቢ የሚፈፀመውን የሙስና ወንጀል ለመመርመር ድፍረት እንደሌለው የተገለጸ ሲሆን ኮሚሽኑ በዚህ ዙሪያ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ቢችል እና በሕግ የተሰጠውን ስልጣን ሙሉ ለሙሉ ለመጧቀም ቢተፉ።

## 1. መግቢያ

ሙስና በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ ዕድገት ከሚያደርሰው ከፍተኛ ጉዳት አንጻር ከታላላቅ ዓለም ዓቀፍ ችግሮች መካከል አንዱ ሙሆኑ የማይታበል ሀቅ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትም ይህን አደጋ በመገንዘብ መልካም ሥነምግባርን በህብረተሰቡ ዘንድ ለማስረጽ እና ሙስናን ለመከላከል ብሎም ለመዋጋት እንዲቻል የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ግንቦት 16 ቀን 1993 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 235/93 በማቋቋም የፀረ- ሙስና ትግሉን በኖደራል ደረጃ እንዲያስተባብርና እንዲመራ አድርጓል፡፡

ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሁም □ተ□ናሙ ወንጀሎችን ለመመርመርና ወንጀለኞችን ለመክሰስ መልካም ሥነምግባር በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲስፋፋ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሠራርን በብቃት መዋጋት እንዲቻል፣ የኮሚሽኑ አሠራር ግልጽነትና □ተጠያቂነት መርሆዎችን በሚገልጽ መልኩ እንዲሁም ኮሚሽኑ ኃላፊነቱን በብቃት እንዲወጣ በሚያስችለው መልኩ በአዋጅ ቁጥር 433/97 የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ተሻሽሏል፡፡

በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 6 መሠረት ኮሚሽኑ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፤

1. አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ትምህርቶችን በማስፋፋት የነቃና ሙስናን ሊሸከም የማይችል ሕብረተሰብ እንዲፈጠር ጥረት ማድረግ፣
2. አግባብነት ካላቸው አካለት ጋር በመተባበር የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሰራርን መከላከል እና
3. የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሠራርን ማጋለጥ፣ መመርመር እና መክሰስ ናቸው፡፡

ኮሚሽኑ ባለፉት 9 ዓመታት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ከማስቻል አንጻር የኮሚሽኑን ራዕይ ተልዕኮና ስትራቴጂ በመቅረጽ በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ ይሁን እንጂ እስከ አሁን ድረስ በኮሚሽኑ ለረዥም ዓመታት በሥነምግባር እና በፀረ-ሙስና ትምህርት፣ በሙስና መከላከል፣ በሙስና ወንጀል ምርመራ እና ሙሰኞችን ለህግ በማቅረብ የተሠሩ ሥራዎች በኅብረተሰቡ ዘንድ መልካም ሥነምግባርን ከማስረፅ እና ሙስናን ከመቀነስ አኳያ የተገኙ ውጤቶችን በጥናት ለማወቅ ጥረት አልተደረገም፡፡

ስለሆነም ኮሚሽኑ በአዋጅ ከተቋቋመ ጀምሮ መልካም ሥነምግባርን ከማስፈን፣ሙስናና ብልሹ አሠራርን ከመከላከልና የሙስና ወንጀልን ከመመርመርና ከመክሰስ አንጻር ያስገኛቸው ውጤቶች ላይ የተጽእኖ ትንተና (Impact Assessment) ጥናት ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ /Background/

የፌዴ ራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአዋጅ ከተቋቋመ ወዲህ በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ ከሚገኙ አጋር ድርጅቶችና ተቋማት ጋር በመተባበር በአገር ውስጥ የሚካሄደውን የፀረ-ሙስና ትግል እየመራ ይገኛል፡፡

ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት ኮሚሽኑ የተቋቋመበትን ዓላማዎች ለማሳካት ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎች የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፤

1. **የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ትምህርትና ሥልጠናን ማስፋፋት፤**

ሙስናንና ብልሹ አሠራርን ለመዋጋት በሚደረገው ጥረት የሙስና ወንጀል ተጠርጣሪዎችን ሕግ ፊት ማቅረብና ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ ብቻውን የሚፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ እንደማይችል ሙስናን ለመከላከል የተደረጉ የሌሎች ሀገሮች ጥረቶች ተሞክሮ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በሙስና ወንጀል ፈፃሚዎች ላይ ከሚደረገው የምርመራ እና የክስ ሂደት ጐን ለጐን ሙስና እና ብልሹ አሠራር

በአንድ አገር ላይ ስለሚያደርሰው የከፋ ጉዳት ሕብረተሰቡን በስፋት በማስተማር ሙስናን የማይሸከም ሕብረተሰብ በመፍጠር በፀረ-ሙስና ትግሉ ላይ የሁሉንም ሕብረተሰብ ተሳትፎ ማግኘት የግድ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ኮሚሽኑ በመልካም ሥነምግባርና በፀረ-ሙስና ዙሪያ የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን (Modalities) ማለትም፤

- መገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም፣
- የኮሚሽኑን የሕትመት ውጤቶች በመጠቀም እና
- የፊት ለፊት (face to face) የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርትና የአሠልጣኞች ስልጠናዎችን በመስጠት በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል።

ኮሚሽኑ ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን እንዲቋቋሙ በማገዝ፣ እነዚህን የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በኃላፊነት የሚመሩ የሥነምግባር መኮንኖችን በማሰልጠንና የምክር አገልግሎት በመስጠት በተቋማት እንዲሁም በትምህርት ተቋማት የሥነምግባር ትምህርት በመደበኛ ትምህርት እንዲካተት በማድረግ፣ የሥነምግባር ክበባት በማቋቋምና ሥልጠና በመስጠት መልካም ሥነምግባርን ለማስፋፋትና ሙስናን ለመዋጋት የሚያግዙ እንቅስቃሴዎች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡

## 2. የአሠራር ሥርዓት ጥናትና የማማከር ተግባራት፤

ኮሚሽኑ በአዋጅ ተቋቁሞ ወደ ተግባር ከገባ ጊዜ ጀምሮ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ሙስናና ብልሹ አሠራርን አስቀድሞ ለመከላከል አገሪቱ የምትመራበትን የልማትና የዲሞክራሲ ግንባታ ስትራቴጂ በማስፈጸም ቁልፍ ሚና የሚጫወቱና በባህሪያቸው ለሙስና ተጋላ□ የሆኑ የመንግሥት መ/ቤቶችንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አሠራር በማጥናት ለሙስናና ብልሹ አሠራር በር የሚከፍቱ አሠራሮች የሚወገዱበትን መንገድ የማመላከት እንዲሁም የምክር አገልግሎት የመስጠትና አሠራሮቹ እንዲሻሻሉ እገዛና ድጋፍ የማድረግ ተግባር

አከናውኗል፡፡ በዚህም 160 ለሚደርሱ የመንግስት መ/ቤቶችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የአሠራር ሥርዓቶችን በማጥናት የማስተካከያ እርምጃዎችን ለየመ/ቤቶቹ በማቅረብ የማሻሻያና የእርምት እርምጃዎቹን አፈፃፀም ሲከታተል ቆይቷል፡፡

## 3. የሙስና ወንጀልን መመርመር፣ ማጋለጥና ለሕግ ማቅረብ፤

ኮሚሽኑ በመንግሥት መ/ቤቶች ወይም በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወይም የፌዳ ራል መንግሥቱ ለክልሎች ከሚሰጠው ድጎማ ጋር በተያያዘ በክልል መ/ቤቶች በወንጀል ሕግ እና በሌሎች ሕጎች ውስጥ የተመለከቱት የሙስና ወንጀሎች በመንግሥት ሠራተኞች ወይም ባለሥልጣኖች ወይም በሌሎች ሰዎች ስለመፈፀማቸው ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው የመመርመር ወይም እንዲመረመር የማድረግ ተግባርና ኃላፊነት አለው፡፡ ከዚህ አንፃር ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ከ1500 በላይ የሙስና ወንጀሎችን መርምሮ 520 የሚጠጉ ወንጀለኞችን ከ3-21 ዓመት በሚደርስ እሥራት እንዲቀጡ አድርጓል፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት ዋና ዋና ተግባራት በተጨማሪ ኮሚሽኑ የአፈፃፀም ብቃቱንና ውጤታማነቱን ከፍ ለማድረግ መሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ለውጥ (BPR) ጥናት በማካሄድ ወደ ሙሉ ትግበራ ገብቷል፡፡

ኮሚሽኑ መንግሥት ከነደፈው የሀገሪቱ □እድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አኳያ የራሱን የአምስት አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት በሚከተሉት አምስት ስትራቴጂክ የትኩረት አቅጣጫዎች ማለትም፤

1. የፌዴራል መንግሥት የመሬት አስተዳደር አሠራር
2. የመንግሥት ትላልቅ ግዥና ሽያጭ አሠራር
3. የፌዴራል መንግሥት ገቢና ታክስ
4. የመንግስት ሹመኞች፣ ተመራጮችና ሠራተኞች ሃብት አመዘጋገብ

5. የመንግሥት የፍትህ አስተዳደር ላይ ትኩረት በማድረግ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን የተሠሩ ሥራዎች ምን ለውጥ አስገኝተዋል? የሚለውን የወቅቱን ጥያቄ ለመመለስ እንዲቻል ኮሚሽኑ ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት በሠራቸው ሥራዎች እና በተገኙ ውጤቶች ላይ የተፅዕኖ ግምገማ (Impact Assessment) ጥናት ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ይህ ጥናት ተካሂዶአል፡፡

## 1.2. በጥናቱ ምላሽ ያገኙ ጥያቄዎች

ከላይ የተጠቀሱትን ሀሳቦች መሠረት በማድረግ ይህ ጥናት የሚከተሉትን ዋና ዋና ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሯል፡፡

1. ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት በሥነምግባር ትምህርት የተሠሩ ሥራዎች በህብረተሰቡ ዘንድ መልካም ሥነምግባርን በማስረፅ እና ሙስናን የማይሸከም ዜጋን ከመፍጠር አኳያ ምን ያህል የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጥ አምጥተዋል?
2. ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት ብልሹ አሠራርን እና ሙስናን በመከላከል የተከናወኑ ተግባራት በተቋማት ዘንድ ያስከተሉት መልካም የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጥ ምን ያህል ነው?
3. ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት በሙስና ወንጀል ምርመራ እና ለሕግ በማቅረብ የተሠሩ ሥራዎች በህብረተሰቡ ዘንድ ያመጡት ፀረ-ሙስና የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦች ምን ያህል ናቸው?
4. ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት በፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተሠሩ ሥራዎች በህብረተሰቡ ዘንድ አወንታዊ የሆነ የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦች ምን ያህል አምጥተዋል?

5. የሥነምግባር ትምህርትን በማስፋፋት፣ ሙስናን በመከላከል እና የሙስና ወንጀልን በመመርመር በማጋለጥና ለሕግ በማቅረብ የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጥንካሬዎች እና ጉድለቶች ምንድን ናቸው?

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ የተፅዕኖ ትንተና (Impact Assessment) ጥናት ዋና ዓላማ በፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ላለፉት ዘጠኝ (1994-2002) ዓመታት በሥነምግባር ትምህርት፣ በሙስና መከላከል እና የሙስና ወንጀሎችን በመመርመር እና ለሕግ በማቅረብ የተሠሩ ሥራዎች በተቋማትና በህብረተሰቡ ዘንድ መልካም ሥነምግባርን በማስረፅ እና የሙስና ችግሮችን በመቅረፍ ያስገኙትን የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦችን ለመገምገም ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ነበሩት፡፡

1. ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት በሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ትምህርት የተሠሩ ሥራዎች በተቋማትና በህብረተሰቡ ዘንድ መልካም ሥነምግባርን በማስረፅ እና ሙስናን የማይሸከም ዜጋን ከመፍጠር አኳያ ያመጡትን የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦች መፈተሽ፣

2. ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት ብልሹ አሠራርን እና ሙስናን በመከላከል የተከናወኑ በተቋማት ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሠራር የተዘረጉ አሠራሮች ያስገኙትን ለውጦች መዳሰስ ተግባራት በተቋማትና በህብረተሰቡ ዘንድ ያስከተሉትን የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦች መዳሰስ፣
3. ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት የሙስና ወንጀልን በመመርመር እና ለሕግ በማቅረብ የተሠሩ ሥራዎች በተቋማትና በህብረተሰቡ ዘንድ ያመጡትን የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦች መዳሰስ፣

4. በተፅዕኖ ትንተናና በጥናቱ ግኝቶች መሠረት የፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን ጥንካሬዎች እና ጉድለቶችን መለየት እና
5. የጥናቱን ግኝቶች መሠረት በማድረግ ኮሚሽኑ የወደፊት አሠራሩን እንዲያሻሽል አስተያየት መስጠት ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ (Significance of the Study)

የዚህ የተፅዕኖ ትንተና ጥናቱ ጠቀሜታና አስፈላጊነቱ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት በሥነ-ምግባር ትምህርት የተሠሩ ሥራዎች በህብረተሰቡ ዘንድ መልካም ሥነ-ምግባርን በማስረፅ እና ሙስናን የማይሸከም ዜጋን ከመፍጠር አኳያ ያመጡትን የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦች ለመፈተሽ ያስችላል፡፡
2. ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት ብልሹ አሠራርን እና ሙስናን በመከላከል የተከናወኑ ተግባራት በተቋማት ዘንድ ያስከተሉትን የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦች ለመዳሰስ ይረዳል፡፡
3. ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት የሙስና ወንጀል ምርመራ እና ተጠርጣሪዎችን ለሕግ በማቅረብ የተሠሩ ሥራዎች በህብረተሰቡ ዘንድ ያመጡትን የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦችን ለመገምገም ይጠቅማል፡፡
4. በተፅዕኖ ትንተና ጥናቱ ግኝቶች መሠረት የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን ጥንካሬዎች እና ጉድለቶችን ለመለየት ይረዳል፡፡
5. የጥናቱን ግኝቶች መሠረት በማድረግ የኮሚሽኑን የወደፊት አሠራር ለማሻሻል ይጠቅማል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በኮሚሽኑ የሥልጣን ክልል ውስጥ ያሉትን የፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች፣ የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ የአዲስ አበባ ከተማ

አስተዳድር፣ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም የሲቪክ ማህበራት፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያዶች)፣ የመንግሥት እና የግል የመገናኛ ብዙሃን፣ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የመንግሥት የትምህርት ተቋማት እና በአጠቃላይ የኮሚሽኑ አገልግሎት ተጠቃሚ አካላትን ቴክሷል፡፡

### 1.6 የጥናቱ ውጤቶች (Outcomes)

ከዚህ የተፅዕኖ ትንተና ጥናት የሚከተሉት ውጤቶች፡-

1. ኮሚሽኑ በተቋማትና በህብረተሰቡ ዘንድ እስካሁን በሠራቸው ሥራዎች የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት እና የአሠራር ለውጦች መምጣት አለመምጣታቸውን ለመለየት ይቻላል፡፡
2. ኮሚሽኑ ባከናወናቸው መልካም ሥነምግባርን በማስፈን፣ በአሠራር ሥርዓት ጥናትና በማማከር እና የሙስና ወንጀልን በመመርመር፣ በማጋለጥና በመክሰስ ተግባራት የኮሚሽኑን ጥንካሬዎች እና ጉድለቶችን ለይቶ ማወቅ ያስችላል፡፡
3. ከጥናቱ የሚገኙ ውጤቶችን መሠረት በማድረግ የኮሚሽኑን የወደፊት አሠራሮች ለማሻሻል ይቻላል፡፡

## 2. የጥናቱ ዘዴ (Methodolgy)

ስለምርምር ሥራ በሰፊው ከጻፉት ደራሲያን መካከል Best & Kahn (እ.ኤ.አ 2003:p.114) እንደገለጹት፤ "Assessment describes the status of a phenomenon at a particular time. It may deal with prevailing opinion, knowledge, practice, or conditions.

ከላይ ከተገለጸው ሀሳብ አንጻር ኮሚሽኑ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ባከናወናቸው ሦስት ቁልፍ ተግባራት ላይ የተፅዕኖ ትንተና ጥናት (Impact Assessment) ለማካሄድ የጥናቱ ዘዴ ያካተታቸው ዐበይት ጉዳዮች፤

- የጥናቱን ዲዛይን ምንነትና ተገቢነት፣

- የመረጃ ምንጮች፣
- የተቋማትና የመላሾች የናሙና አመራረጥ ዘዴና ተገቢነት፣
- የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችና የመሣሪያዎቹ ተገቢነት፣
- የመረጃ አሰባሰብ ሂደት፣
- የመረጃ ትንተና ዘዴዎች፣
- የቅደመ ጥናት ሙከራ፣
- በተካሄደው የቅድመ ጥናት ሙከራ የተገኙ ውጤቶች፣
- የጥናቱ ውስንነትና ያጋጠሙ ችግሮች እና
- መረጃ ለመሰብሰብ ሥራ ላይ የዋሉ መሣሪያዎችና የተገኙ ምላሾች ናቸው፡፡

## 2.1 የጥናቱ ዲዛይን

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ኮሚሽኑ ላለፉት ዘጠኝ (1994-2002) ዓመታት በሥነምግባር ትምህርት፣ በሙስና መከላከል እና የሙስና ወንጀሎችን በመመርመር እና ለሕግ በማቅረብ የተሠሩ ሥራዎች በተቋማትና በህብረተሰቡ ዘንድ መልካም ሥነምግባርን በማስረፅ እና የሙስና ችግሮችን በመቅረፍ ያስገኙትን የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦችን ለመገምገም ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ የጥናቱ ዲዛይን የተፅዕኖ ትንተና ጥናት (Descriptive Assessment Study) ነው፡፡ ይህም ዲዛይን የተመረጠበት ምክንያት ከጥናቱ ባህሪይ አንጻር ነው፡፡ ”Assessment is a fact-finding activity that describes conditions that exist at a particular time, (Best & Kahn, 2005: 21).

## 2.2 የመረጃ ምንጮች

እንደማንኛውም የጥናትና ምርምር ሥራ የዚህ ጥናት የመረጃ ምንጮች በሁለት የተከፈሉ ሲሆን እነሱም፤

ሀ. የመጀመሪያ የመረጃ ምንጭ (Primary Data Source) ማለትም በናሙና ከተመረጡ ተቋማት ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎች፣ የሥነምግባር መኮንኖች፣ ከነዋሪዎች ፎረም ከመጠይቆች፣ ከቃለመጠይቆች፣ ከቡድን ተኮር ውይይት የሚገኙ መረጃዎች እንዲሁም፤

ለ. ሁለተኛ የመረጃ ምንጭ (Secondary Data Source)፦ ከተጻፉ ጽሑፎች፣ ከመንግሥት አዋጆች፣ ከመጽሐፍትና ከኮሚሽኑ ሰነዶች የሚገኙ ሲሆኑ የተገኙት መረጃዎች በአሀዝ የሚገለጹ (Quantitative data) እና/ወይም በቃላት የተገለጹ (Qualitative data) ናቸው፡፡

## 2.3 የተቋማትና የመላሾች አመራረጥ

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም አካል የሆነው የሥነምግባር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ካከናወናቸው ተግባራት አንዱ የሆነው በ1993 ዓ.ም የተጠናውና ኮሚሽኑ እንደግብዓት የተጠቀመበት የመጀመሪያው የሙስና ቅኝት በኢትዮጵያ ጥናትን መሠረት በማድረግና ኮሚሽኑ በህግ በተሰጠው የስልጣን ክልል ሥር ያሉ ቁልፍ ተቋማትን በመለየትና ትኩረት በመስጠት የፀረ-ሙስና ትግሉን አካሂዷል፡፡ ከዚህ አንጻር ጥናቱ በዋናነት ትኩረት የሰጠው ኮሚሽኑ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት በይበልጥ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ትምህርትን በማስፋፋት፣ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድና የሙስና ወንጀል ለመፈጸሙ ጥርጣሬ ሲኖር የሙስና ወንጀሎችን በመመርመር በመክሰስና በማስቀጣት በሠራባቸው ተቋማት ላይ መሆኑ ተገቢነት ያለው ይሆናል፡፡

ኮሚሽኑ ከልማትና ዲሞክራሲ ግንባታ አንጻር ቁልፍ ሚና የሚጫወቱና በባህሪያቸው ለሙስና ተጋላጭ በሆኑ በፌደራል ደረጃ የሚገኙ የመንግሥት መ/ቤቶችና የመንግሥት

የልማት ድርጅቶች፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርና በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የትምህርት ተቋማት ላይ የቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ የሠራባቸው ተቋማትና በፌደራል ደረጃ የሠራባቸውን መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በጠቅላላው 1381 ተቋማትን ዝርዝር በማሰባሰብ ኮሚሽኑ ያከናወናቸውን ሦስት ቁልፍ ተግባራት መነሻ በማድረግ እነዚህን 1381 ተቋማት በሦስት ምድብ ማለትም የፌደራል የመንግሥት መ/ቤቶች፣ የፌደራል የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና የሲቪል ማህበራት ምድብ የመከፋፈል ሥራ ተሰርቷል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 1 ተመላክቷል)

ከላይ ከተገለጸው አንጻር፤

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች
- የፌዴራል የመንግሥት የልማት ድርጅቶች
- የአዲስ አበባ ከተማና የድሬዳዋ ከተማ በተለያየ ደረጃ ላይ ያሉ የመስተዳደር አካላት
- የሲቪል ማህበራት
- የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት
- ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ት/ቤቶች
- የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች

በጠቅላላው 210 ተቋማት በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ጥናቱ ናሙናን ለመምረጥ የተጠቀመበት ዘዴ ሁለት ዓይነት ሲሆን ይኸውም ተቋማትን በምድብ ለመከፋፈል ዓላማ ተኮር ዘዴ (Purposive Sampling Technique) በጥቅም ላይ አውሏል፡፡ ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት ኮሚሽኑ ተቋማት ካላቸው ለሙስና ተጋላጭነት ባህሪይና በተቋማት ውስጥ ሙስና ቢፈጸም ከሚያደርሰው ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ከባቢያዊ ከፍተኛ ጉዳት አንጻር ኮሚሽኑ ትኩረት ሰጥቶ የሠራባቸውን ተቋማት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ሁለተኛው ዘዴ ደግሞ ተቋማት በምድብ የመከፋፈሉ ተግባር ከተከነወነ በኂላ ከየምድቡ ተቋማትን ለመመረጥ ጥቅም ላይ የዋለው ድንገቴ ናሙና (Incidental Sampling) ነው፡፡

የዚህ ጥናት መላሾች ብዛት 3048 ሲሆን የየተቋማት መላሾች የተመረጡበት ዘዴም ዓላማ ተኮር ዘዴ ነው፡፡ ይህንንም ዘዴ በመጠቀም የተቋማት ኃላፊዎችና በኃላፊዎች ሥር ያሉ ባለሙያዎች እንዲሁም የሥነምግባር መኮንኖች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

ምንም እንኳ ከአጠቃላይ 1381 ተቋማት መካከል ለጥናቱ በናሙናነት የተመረጡት ተቋማት 210 ቢሆኑም የናሙና አመራረጡ ኮሚሽኑ ከልማትና ዲሞክራሲ ግንባታ ስትራቴጂ አንጻር ቁልፍ ሚና የሚጫወቱና ለሙስናና ብልሹ አሠራር በመጋለጣቸው በአጠቃላይ በተያዘው የልማትና ዲሞክራሲ ጎዳና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርሱ በሚችሉ ከፍተኛ የመንግሥት ገንዘብ፣ የሰው ኃይልና ንብረት የሚንቀሳቀስባቸው ተቋማት በተለይም፤

- ገቢ ሰብሳቢ
- የፋይናንስ
- የመሠረተ ልማት
- ልማታዊ ባለሀብትን በማሳደግ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ
- በጤናና በትምህርት ዘርፍ

በተሰማሩ ተቋማት የቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ በሠራባቸው ከመሆኑ አንጻር ሲታይ የተወሰደው ከየምድቡ የተቋማት ናሙና ቁጥር ተገቢ ነው፡፡

"All research, including qualitative research, involves sampling. This is because no study, whether qualitative, quantitative or both, can include every thing: you can't study every one everywhere doing every thing" (Keith F Punch, 1998:105).

## 2.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ይህን ጥናት ለማካሄድ አራት ዓይነት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በተግባር ላይ የዋሉ ሲሆን እነሱም፤

1. □□ሑአ መጠይቆች፣
2. ቃለመጠይቆች፣

3. ቡድን ተኮር ውይይቶች (FGD) እና
4. ሰነድ  ናቸው፡፡

## 2.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎቹ ተቁኒነት

1. መጠይቆች- የጥናቱ ዲዛይን የተፅዕኖ ትንተና ጥናት (Descriptive Assessment Study) በመሆኑና ብዛት ያለው መጠይቆችን ማሰራጨት የሚጠይቅ በመሆኑ ከፍተኛ ወጪን ሳይጠይቅ መረጃዎችን በአጭር ጊዜ ለመሰብሰብ ከማስቻሉም በተጨማሪ በመጠይቅ አማካኝነት የሰዎችን እምነት፣ ዝንባሌ፣ ፍላጎት አመለካከታቸውን ለማወቅ የሚያስችል መሆኑ ነው፡፡

ለዚህ ጥናት የተዘጋጁ መጠይቆች ባሕሪያት በሁለት የተከፈሉ ናቸው፡፡ አንደኛው ለተጠያቂው የሚቀርበው ጥያቄ አማራጭ መልሶችን የያዘ ሲሆን መላሹ በተሰጠው መልስ የመስጠት መመሪያ መሠረት የሚሰጥበት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ መላሹ ለቀረበለት ጥያቄ የራሱን ሀሳብ በጽሑፍ እንዲገልጽ የሚያስችል ሆኖ የተዘጋጅ ነው፡፡

ለጥናቱ መረጃ ለመሰብስብ የተዘጋጀው መጠይቅ አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ይኸውም፤

ሀ. የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ትምህርትና የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን እንቅስቃሴ በተመለከተ 19 ጥያቄዎች

ለ. የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድ ሙስናና ብልሹ አሠራርን መከላከል የተመለከቱ 15 ጥያቄዎች

ሐ. የሙስና ወንጀሎችን መመርመር መክሰስና ማስቀጣት የተመለከቱ 17 ጥያቄዎች

መ. አጠቃላይ የኮሚሽኑን አሠራር በተመለከተ 17 ጥያቄዎችን የያዘ መጠይቅ ነው፡፡

2. ቃለመጠይቆች- የዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ጠቀሜታ ከመላሹ ግለሰብ ጋር ብዙውን ጊዜ ፊት ለፊት ተገናኝቶ መረጃን በቃለመጠይቅ መሠረት የሚሰበሰብ ሲሆን የሚሰበሰበው መረጃ ጥራት ያለው ነው፡፡ "With a skillfull Interviewer, the interview is often superior to other data gathering devices, (Best & Kahn, 2005: 323). ሆኖም ይህ መረጃ የመሰብሰቢያ መሣሪያ ጊዜ ወሳጅ ከመሆኑ አንጻር በዚህ ጥናት ላይ በ21 ተቋማት ከአርባ ሁለት መላሾች መካከል የተቋማት የበላይ ኃላፊዎች ወይም ተወካዮቻቸው እና የተቋማት የሥነምግባር መኮንኖች ተሳትፈዋል፡፡

3. ቡድን ተኮር ውይይት (Focused Group Discussion)- ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ መረጃ ለመስጠት ተገቢነት ያላቸውን ቁጥራቸው ከ5 እስከ 10 የሚደርሱ ግለሰቦችን በአንድ ቦታ በማሰባሰብ ቀደም ብለው በተዘጋጁ የውይይት ፍሬ ነገሮች ላይ የየራሳቸውን አስተያየት፣ እምነትና ሀሳብ በሰፊው እንዲገልጹ የሚያስችል በመሆኑ በዚህ ጥናት ከነዋሪዎች ፎረም ከክፍለ ከተማ አስተዳደር ከተውጣጡ አሥር የቡድኑ አባላት ጋር ለመወያየት በተግባር ላይ ውሏል፡፡

4. ከሰነድ የሚሰባሰቡ መረጃዎች በምዝገባ የተያዙና በሌሎች የመረጃ መሣሪያዎች የተገኙ መረጃዎች ለማነጻ□ሪያነት ጭምር የሚጠቅሙ በመሆናቸው በዚህ ጥናት በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህ ሰነዶች በጽሑፍ የሚገኙ ስለሆነ ከነዚህ የሚገኘው መረጃ የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው ይታመናል፡፡ በዚህም አግባብ ያላቸው አዋጆች፣ ደንቦች፣ የታተሙና ያልታተሙ ጽሑፎችና የኮሚሽኑ ከ1994 በጀት ዓመት እስከ 2002 በጀት ዓመት ያሉ ሪፖርቶችን ያካትታል፡፡

## 2.6 የመረጃ አሰባሰብ ሂደት

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፤

- 9 ሱፐርቫይዘሮች
- 49 መረጃ ሰብሳቢዎች

ተቀጥረው የማሰልጠኛ ማንዋል በማዘጋጀት ለሱፐርቫይዘሮችና ለመረጃ ሰብሳቢዎች ስልጠና ተሰጥቷል።

ሱፐርቫይዘሮችንና መረጃ ሰብሳቢዎችን በቡድን በማደራጀት በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጪ በናሙና ከተመረጡ ተቋማት ከ2996 ተሳታፊዎች መጠይቆችን፣ ከ35 ቃለመጠይቆችንና 10 አባላት ካሉት ከነዋሪዎች ፎረም ቡድን ተኮር ውይይት መረጃ ለማሰባሰብ ተችሏል።

## 2.7 የመረጃ ትንተና ዘዴዎች

በዚህ ጥናት መረጃዎችን ለመተንተን ጥቅም ላይ የዋሉ ስታትስቲካዊ ዘዴዎች፣

1. መቶኛ (Percentage)፣ የመላሾችን ቁጥር በመቶኛ ስሌት ለማሳየትና በመጠይቆቹ ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች ስንቱ መላሽ እንደመለሰና እንዳልመለሰ ለማወቅ፣

2. ካይስኴየር ቴስት (Chi-Square Test) የተገኙ ስሌቶች አንዱ ከሌላው ምን ያህል ተቀራራቢነትና ልዩነት እንዳለውና እንደሌለው ለማየትና ድምዳሜ ላይ ለመድረስ፣

3. ፒርሰን ኮርሌሽን (Pearson Correlation) ምላሾች/መረጃዎች ያላቸውን ተዛምዶ ለማሳየት፣

4. አ ኖ ቫ (ANOVA) ከቡድኖች የተገኙ ምላሾች ያላቸውን ተቀራራቢነትና ልዩነት ለማመላከት እና

5. የተአማኒነት ትንተና (Reliability Analysis) የተሰራጩ መጠይቆች ለጥናቱ የሚፈለጉ ምላሾች ለማስገኘት ያላቸውን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ

ከላይ የተገለጹትን ስታትስቲካዊ የትንተና ዘዴዎችን በመጠቀም ከመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ማለትም መጠይቅ፣ ቃለመጠይቅ፣ ቡድን ተኮር ውይይት (FGD) እና

ከሰነድ የተገኙ ምላሾችን በማጣመር (Triangulate) በጥናቱ ምላሽ ማግኘት ለሚገባቸው 5 መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ ለማስገኘት ትንተና ተሰርቷል፡፡

## 2.8 የቅድመ ጥናት ሙከራ (Pilot Test) እና □ቱቶኙ ውጤቶች

ዋናው ጥናት ከመካሄዱ በፊት በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ከየሴክተሩ አንዳንድ ተቋማትን በመምረጥና ለእያንዳንዱ ለሙከራ የተመረጠ ተቋም 18 መጠይቆችን በጠቅላላው 108 መጠይቆችን በማሰራጨትና 96 ያህሉን በማሰባሰብ የጥናቱ ሙከራ (Pilot Test) የተካሄደ ሲሆን ከመጠይቁ መካከል በተዛማጅ ጥያቄዎች ላይ በተሠራው የአስተማማኝነት መለኪያ 0.71 ሆኖአል፡፡ ይኸ የአስተማማኝነት መጠን ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ ለሙከራ የተመረጡ ተቋማትም፡-

1. የኢትዮጵያ የሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን
2. የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት
3. የካቲት 12 አጠቃላይ ሆስፒታል
4. የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ
5. አራዳ ክፍለ ከተማ
6. ዳግማዊ ሚኒሊክ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት ቤት ናቸው፡፡

በተካሄደው ቅድመ ጥናት ሙከራ (Pilot Test) የተገኙ ውጤቶች፤

1. ለሙከራ ጥናት ለተመረጡ ለሁሉም ተቋማት አራቱም ዓይነት መጠይቆች ተሰራጭተው የተገኘው ውጤት ኮሚሽኑ ከሚያከናውናቸው ሦስት ቁልፍ ተግባራት በአንዳንድ ተቋማት ያልተሰራባቸው በመሆኑ ለቀረቡ ጥያቄዎች ሙሉ ለሙሉ አናውቅም የሚል ምላሽ በመገኘቱ ለዋናው ጥናት መጠይቆቹን ኮሚሽኑ በተቋማት ላይ ከሠራባቸው የሙስናን የመታገያ ዘዴዎች አንጻር በመከፋፈል፤

   1.1 በናሙና በተመረጠው ተቋም ኮሚሽኑ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ትምህርትን የሚመለከት ተግባር ብቻ ካከናወነ የሚሰራጨው መጠይቅ

የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ትምህርትና የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን እንቅስቃሴ በተመለከተ እና አጠቃላይ የኮሚሽኑን አሠራር በተመለከተ የተዘጋጀውን መጠይቅ፣

1.2 በናሙና በተመረጠው ተቋም ኮሚሽኑ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ትምህርትና የአሠራር ሥርዓት ጥናት ተግባራትን ካከናወነ የሚሰራጨው መጠይቅ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ትምህርትና የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን እንቅስቃሴ በተመለከተ፣ የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድ ሙስናና ብልሹ አሠራርን መከላከል እና አጠቃላይ የኮሚሽኑን አሠራር በተመለከተ የተዘጋጀውን መጠይቅ፣

1.3 በናሙና በተመረጠው ተቋም ኮሚሽኑ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ትምህርትና የሙስና ወንጀሎችን መመርመር መክሰስና ማስቀጣት ተግባራትን ካከናወነ የሚሰራጨው መጠይቅ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ትምህርትና የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን እንቅስቃሴ በተመለከተ እና የሙስና ወንጀሎችን መመርመር መክሰስና ማስቀጣት እና አጠቃላይ የኮሚሽኑን አሠራር በተመለከተ የተዘጋጀውን መጠይቅ፣

1.4 በናሙና በተመረጠው ተቋም ኮሚሽኑ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ትምህርትና የአሠራር ሥርዓት ጥናት፣ የሙስና ወንጀሎችን መመርመር መክሰስና ማስቀጣት ተግባራትን ካከናወነ የሚሰራጨው መጠይቅ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ትምህርትና የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን እንቅስቃሴ በተመለከተ፣ የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድ ሙስናና ብልሹ አሠራርን መከላከል፣ የሙስና ወንጀሎችን መመርመር መክሰስና ማስቀጣት እና አጠቃላይ የኮሚሽኑን አሠራር በተመለከተ የተዘጋጀውን መጠይቅ፣

በአራት ምድብ ከፋፍሎ በናሙና ለተመረጡ ተቋማት ለዋናው ጥናት መጠይቆቹን ለማዘጋጅትና ለማሰራጨት፤ እንዲሁም

2. ከሙከራው በተገኘው ውጤት መነሻነት ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ሱፐርቫይዘሮች ተጨማሪ ስልጠና መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ለመረዳት አስችሏል፡፡

## 2.9 የጥናቱ ውስንነትና ያጋጠሙ ችግሮች

- ጥናቱ ትኩረት ያደረገው ኮሚሽኑ በሠራባቸው የፌደራል የመንግሥት መ/ቤቶችና የፌደራል የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ላይ በመሆኑ በመላ ሀገሪቱ የተከናወኑ የፀረ-ሙስና ትግሎችንና ያስገኙትን ውጤቶች ያላካተተ መሆኑ የጥናቱን ውስንነት ሲያሳይ ያጋጠሙ ችግሮች ደግሞ
- ለጥናቱ የተመደበው ጊዜና በጀት ውስን መሆኑ
- በተቋማት አደረጃጀት ለውጥ ምክንያት በናሙና የተመረጡ ተቋማት ቀደም ሲል በነበራቸው ስያሜና አደረጃጀት አለመገኘት
- አሁን ከተፈጠረው ምቹ ሥራ የማግኘት ሁኔታ አንጻር የመንግሥት መ/ቤትና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ኃላፊዎችና ሠራተኞች መለዋወጥ ኮሚሽኑ ሥራውን ባከናወነበት ወቅት የነበሩ ኃላፊዎችና ሠራተኞች መጠይቅ ለማስሞላትና ውይይት ለማካሄድ አለመገኘትና አዲስ የተቀጠሩ ስለተሠራው ሥራ አለማወቅ፡፡
- የፌደራል የመንግሥት መ/ቤቶችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ኃላፊዎች ለውይይትና ቃለመጠይቅ በቀጠሮ አለመገኘት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

# 3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

## 3.1 መግቢያ

የኢትዮጵያ መንግሥት የፌደራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን (FEACC) እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ2001 ዓ.ም. አቋቋመ፡፡ ዋና አላማውም ሙስና በመላ ሀገራችን ከቁጥጥር ውጭ ከመሆኑ በፊት ለመዋጋት ነው፡፡ የፌደራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን (FEACC) ከተቋቋመ ወዲህ በሦስት ዋና ዋና መንገዶች ማለትም አስቀድሞ በመከላከል (በማስተማርና ብልሹ አሰራርን በመከላከል)፣ ወንጀልንና ብልሹ አሰራርን በማጋለጥ እና በመክሰስ ሙስናን ይዋጋል፡፡

የዚህ አጭር ቅኝት ዋና ትኩረት በዋናነት ትምህርትና ሥልጠናን በተመለከተ ሙስናን የመከላከል ዘዴና ስልት ላይ ያተኩራል፡፡ ትምህርትና ሥልጠናም ሙስናን በመዋጋት ረገድ ዋናውን ሚና እንደሚጫወቱ በጥብቅ ይታመናል፡፡ ጉዳዩን ግልጽ ለማድረግ የሙስናን ትክክለኛ ትርጉም መስጠት ያስፈልጋል፡፡

በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ መንግሥት የፌደራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን (FEACC) ሙስናን እጅ መንሻ ማቅረብ፣ ስጦታ፣ መጠየቅና መቀበል፣ መገፋፋት፣ ተስፋ መስጠት፣ ውለታ መዋል፣ በቃል ወይም በተግባር ማስፈራራት፣ ሥልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም ተጽእኖ ማሳደር፣ ፊትን መለዋወጥ፣ የሌላውን ጥቅም ለመጠበቅ ድርጊቱ በሚመለከታቸው አካላት፣ አባላትና ባለሥልጣኖች ላይ ተዘዋዋሪ ተጽእኖ ማድረግ በማለት ይገልጸዋል፡፡

የአፍረቃ ወጣቶች ትረስት[1] (2009) አለማቀፋዊ ግልጽነት የተባለውን ድርጅት ጠቅሶ ሙስና ታማኝነት የጎደላቸው ኀይሎች የግል ትርፍ ወጹም ጥቅም የሚያገኙበት ዘዴ ነው በማለት ይገልጸዋል፡፡

ከዚህም ጋር የሕዝብ አገልጋይ ባለሥልጣን፣ ወይም አንድን ተግባር ለማከናወን መደለያ ለመስጠትም ሆነ ለመቀበል ሁኔታዎች የሚፈቅዱለት ማንኛውም ሰው፣

- የንብረት ባለቤትነትን (ምሳሌ የመንግሥት ቤቶችን) ለሌላ ማስተላለፍ የሚችል፣
- ጥቅም የሚቀበል ለምሳሌ ገንዘብ በመስጠትና በመቀበል፣ በስጦታ፣ በእጅ መንሻ፣ በስጦታና በማባበልና ተስፋ በመስጠት ወይም ገንዘብና ስጦታ በመስጠትና በመቀበል ጥቅም ማግኘት ሙሰኛ ይባላል በማለት ይገልጸዋል፡፡

  የተለያዩ ምንጮች ሙስና አዲስ ክስተት እንዳልሆነ ያሳያሉ፡፡ የኦክስፎርድ እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት ሙስናን ሕዝባዊ አገልግሎትን በመደለያ ወይም በጥቅም ማባበል በመለወጥ ታማኝነትን ማጉደል

[1] Africa Youth trust organization

እንደሆነና ቢያንስ ከ1425 ዓ ም. ጀምሮ በዚሁም መንፈስ እንደሚታወቅ ያመለክታል፡፡

ይህንን ክስተት በተመለከተ Zvekic (2002:4) ሙስና አዲስ እድገት አይደለም፡፡ በብዙ ሺ ከሚቆጠሩ ዓመታት በላይ ሕጋዊ ያልሆነና ስፍር ቁጥር የሌለው የሀብት ማካበቻና የልዩ ጥቅም ማግኛ፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማረጋገጫና ማጠናከሪያ በመሆን አገልግሏል፡፡ ይህ ሁኔታ ሙስና ሰብአዊ ባህርይ ነው እንድንል ቢፈትነንም ሙስና ያለና የነበረ ወደፊትም ከእኛው ጋር የሚኖር ነው ብሎ መደምደሙ ግን ሙስናን የተመለከቱ ርምጃዎችን ከመውሰድና የእርምጃዎቹን አስፈላጊነት ከማመን ወደ ኋላ እንድንል ይገታናል፡፡ ምንም እንኳን ደረጃው ቢለያይም የዓለም ሕዝቦች በሙሉ አንድ ዐይነት የሙስና ልምድ አላቸው፡፡ አብዛኞቹ ያደጉ አገሮች የሀገራቸውን የኢኮኖሚ እድገት መሠረት ያደረገ ግልጽና አስነዋሪ ሙስና ይፈጽማሉ፡፡

የአፍሪቃውያን ወጣቶች አደራ የተባለው ድርጅት ይህንን ተልእኮ በተመለከተ ከሙስና የጸዳ ትልውድ ማፍራትና ከግቡ ለማድረስ እንፈልጋለን፡፡ ስለ ሙስና መከላከል፣አስቀድሞ መከላከል፣ ወሬ ማናፈስ፣ ማቃለል፣ ቁጥጥር የፀረ ጉቦ መከላከል፣ በማለት ሙስናን ይገልጸዋል፡ ሆኖም እያንዳንዳችን ምክንያቱን፣ ውጤቱንና የሙስናውን ጉዳት መጠን መረዳት መቻል አለብን፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ ራሱን ከሙስና መጠበቅና በሙስና ላይ መነሳሳት አለበት፡፡

እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ2002 በደቡብ አፍሪካ የእድገት ማኅበረሰብ[2] በሙስና ላይ የተሠራው ቅኝት ቁጥር አንድ ሰንጠረዥ ለሙስና በቀላሉ የተጋለጡ አካባቢዎችን ያሳያል፡፡ ከሰንጠረዡም በ SADC ጥናት በቀላሉ ለሙስና የተጋለጡ አካባቢዎች መጠን እንደቅደም ተከተላቸው ወሲብ ልማድ፣ የአደንዛዥ ዕፅ ዝውውር፣ ፖሊስ፣ፍልሰትና የፍትሕ አካላት ናቸው፡፡

[2] Southern African Development Community (SADC)

ሠንጠረዥ 2 በSADC. ለሙስና የተጋለጡ ክፍሎች (አገሮች)

| አገር | ለሙስና የተጋለጡ ተቋሞች/ድርጅቶች | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | **1** | **2** | **3** | **4** | **5** | **6** | **7** | **8** | **9** | **10** | **11** |
| አንጎላ | | X | | | | | | | | | |
| ቦትስዋና | | | | X | X | | | X | | | |
| ዲሞክራቲክ ሪፓብሊክ ኮንጎ | x | | | | | | | | | | X |
| ሌሴቶ | X | | | | | | | | | | X |
| ማላዊ | | | X | X | | | | X | | X | |
| ሞሪሽስ | X | | X | X | | | | | X | | |
| ሞዛምቢክ | X | | | | | | | X | | | X |
| ናሚብያ | X | | X | X | X | | | X | | | X |
| ሲሼልስ | X | | | | | | | | | | |
| ደቡብ አፍሪቃ | | | X | X | X | | | X | | | X |
| ሳዋዚላንድ | | X | | X | | | X | | | | |
| ታንዛንያ | | X | | X | | X | | | X | X | X |
| ዛምብያ | X | | | X | | | | | | | |
| ዚምባቤ | | | X | | | | | | | | |
| ድምር | **7** | **3** | **5** | **8** | **3** | **1** | **1** | **5** | **2** | **2** | **6** |

ምንጭ፡ Corruption and Anti-Corruption in Southern Africa (2002).

ቁልፍ : (Key) - በተመለከቱት ሀገሮች የተገኙ ችግሮች 1= ልማድ 2= ዳኝነት 3=ፖሊስ 4= ዕዴ 5= ፈቃድ 6= ትምህርት 7= ቅጥር 8= ስደተኝነትና የጠረፍ ቁጥጥር 9= ጤና 10= የገቢ ስብሰባና 11= የአደንዛዥ ዕፅ ዝውውር

ቀደም ብሎ □ንደተገለጸው ሙስና በተለያየ ደረጃ ሊከሰት ይችላል፡፡ በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ፣ በብሄር፣ በዞን፣ በአገር □ና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ፡፡ የSADC ጥናት □ንደሚያሳየው አንዳንድ መንግሥታዊ ድርጅቶች ከሌሎቹ የበለጠ ወደ ሙስና ያዘነበሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከሙስና ጋር በተዛመደ የሚሰጥ ትምህርትና ሥልጠና ይህንን ዕውነታ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፡፡

በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ የተከሰተን ሙስና /በአግባቡ/ ለመዋጋት □ንዲቻል ለሙስናው መንሥዔ ነው ተብሎ የሚገመተውን ምክንያት፣ ሙስናው የሚፈጥረውን

ተጽዕኖ፤የሙስናውን ሥፋት □ና አንደምታ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በሆነ ሕብረተሰብ ውስጥ የሚታይን የሙስና ውስብስብ ባሕርያት በተጣራ ሁኔታ ሳይረዱ ሙስናውን ለመዋጋት የሚያስችል ነው ብሎ ሁነኛ ብልሃት መንደፍ አይቻልም፡፡ የሌሎች ሀገራት ተሞክሮም የሚነግረን ይህንኑ ነው፡፡ /አንድ የዴሞክራሲና አስተዳደር ማ□ከል ነኝ የሚል ድርጅት ያወጣው የሙስና ፍልሚያ ማስታወሻ ደብተር (1999፡ 1) የሚከተለውን ያስነብበናል፡፡

ዘዴዎቹ መመረጥ የሚገባቸው የሙስናውን ባሕርይ ካጠኑና ለችግሩ የሚበጁ መፍትሔዎችና □ንቅፋቶች ተለይተው ከታወቁ በሁዋላ መሆን ይገባዋል፡፡ የሚነደፈው ዘዴ በአንድ አገር ውስጥ ለአሉት የተለያዩ ሁኔታዎች □ንደሚስማማ ሆኖ መነደፍ ስላለበት፤ የዚህ ዓይነት ዘዴ አዘገጃጀት፡ በጠቅላላ በሃገሩ ውስጥ □ና ሃገሩ ውስጥ በሚገኙት ልዩ ልዩ የመንግሥት ተቋማት ውስጥ የሚታየውን የሙስና ደረጃ፡ ቅርፅና ምክንያት መመርመርን ይጠይቃል:: □ዘዴ አቀራረፁ ጸረ-ሙስና ትግሉን በመንግሥትና በሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የማካሄዱን ተግባር በተመለከተ የመንግሥትን የፖለቲካ አመለካከትና የፈቃደኝነት ደረጃ በጥንቃቄ ማስተዋልንም ግድ ይላል፡፡

ከዚህም በላይ የዲሞክራሲና አስተዳደር ማዕከል (1999፡1)[3] የተባለ ተቋም ሙስናን እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡፡

ሙስና ከመንግሥታዊና ሕዝባዊ ተቋማትና ባሕርያት አወቃቀር ይጀምርና ወደ መደበኛው የፖለቲካ ሂደት ያድጋል፡፡ ሙስና ለሙስና በር ከሚከፍት አደረጃጀት በተጨማሪ ለሙስና ሁኔታዎቹን የሚያመቻቹና የሙስና መንስኤዎችን የሚቀንስ ተጠያቂነትን የሚያንኳስሱ፣ በመንግሥት ሠራተኛ ቅጥር ወቅት ተገቢ ያልሆኑ ማበረታቻዎችን የሚወስዱ፣ ከሕዝባዊ አገልግሎት ይልቅ ለግላዊ አገልግሎት ቅድሚያ የሚሰጡ የመንግሥት ባለሥልጣኖችንም አሠራርና ባህርይ ይጨምራል፡፡

[3] Center for Democracy and Governance (1999:1)

ከተደነገገው ደንብ ይልቅ ለግለሰብ ታማኝነት፣መንግሥታዊ ሕግን አሳንሶ ማየት፣ ከፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሂደት ይልቅ የፖለቲካ ፓርቲውና የጥቂት ተመራጮች አምባገነንነት ያየለበት አሠራር ሙስናን ጸ□ኛአራል፡፡

## 3.2 የሙስና ደረጃ፣ ቅርጽና ይዘት

ዜጎችን ለማስተማርና ስሜታቸውን በሙስና ላይ ለማነሳሳት በማኅበረሰቡ፣ ተቋማትና ድርጅቶች ወዘተ.... ያለው የሙስና ደረጃ፣ ቅርጽና ምልክት በግልጽ መታወቅ እንዳለበት በሙስና ላይ የተሠሩ ጥናቶች አጽንኦት ሰጥተው ያስረዳሉ፡፡ ያለ እንደዚህ ዓይነት የጠራ ዕውቀት የሚነደፍ ስትራቴጂ ሙስናን በመዋጋት ረገድ ውጤታማ አይሆንም፡፡ እንደ ዲሞክራሲና አስተዳደር ማዕከል (1999) ሙስናን የመዋጋት ስትራቴጂ ሀገሪቱ ያለችበትን የሙስና ችግርና ባሕርይ እንዲሁም አጋጣሚዎችንና አስገዳጅ ሁኔታዎችን ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ ስትራቴጂውን ለማቀድ በጥቅሉ የሀገሪቱን በከፊል ደግሞ የመንግሥት ተቋማትን የሙስና ደረጃና ቅርጽ መመርመርና መገምገም ያስፈልጋል (ቅ.15)፡፡ ያለን የጽሑፍ መረጃ ሙስና በተለያ□ ቅርጾች፣ በተለያዩ ደረጃዎችና ዓይነቶች እንደሚከፋፈል ያሳያል፡፡

እንደ AYT (2009) ሙስና በሚከተሉት ደረጃዎች ሊገለጽ ይቻላል፡፡ በግለ ሰብ፣ ቤተሰብ፣ ማኅበረሰብ፣ ክልላዊ ሀገራዊና ዓለምአቀፋዊ ደረጃዎች አሉት፡፡ ምደባውን[4] በተመለከተ ዝቅተኛና ከፍተኛ ሙስና አለ፡፡

### 3.2.1 ፖለቲካዊ እና ቢሮክራሲያዊ ሙስና

ፖለቲካዊ ሙስና ወይም ትልቁ ሙስና (Grand Corruption) እየተባለ የሚጠራው ሙስና የሚከሰተው የውሳኔ ሰጪ አካላት ስልጣናቸውን፣ ሀብታቸውን እና ክብራቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ የፖለቲካ ኃይላቸውን ሲጠቀሙ ነው፡፡ የሚከናወነውም

[4] categories

በከፍተኛ ደረጃ ባሉት የፖለቲካ ስልቶች ነው፡፡ ይህም የሙስና አይነት በሚከተሉት ባህርያቱ ይገለጣል::

- በከፍተኛ የሕዝብ ባለስልጠናት ይፈጸማል፡፡ እነዚህም ባለስልጣናት ወንጀሉን የሚፈጽሙት ያለመከሰስ መብታቸውን ተገን በማድረግ ነው፡፡
- በጉዳዩ የተለያዩ ተቋማት፣ ቢሮዎች እና ልዩ ልዩ ክፍሎች የተጠናከረ መረብና ተሳታፊ ኃይላት ይገኙበታል፡፡
- የሚከናወነውም በከፍተኛ ምሥጢር እና የግልጽነት እና ተጠያቂነት (Transparency and Accountability) ተቋማት መረጃ እዳይደርስ በማድረግ ነው፡፡
- ክንውኑ የሚፈጸመው ባልተለመደ ፍጥነት እና ከጉዳዩ ጋር ተሳታፊ የሆኑትን ጥቅም ለማፋጠን ሲባል የግዴታ ስርዓት የለውም፡፡
- ከፍተኛ ባለሥልጣናቱ በጉዳዩ የሚገቡት ጉዳዩ ቢጋለጥ የሚመጣው መዘዝ እንዳይደርስባቸው እንደተለመደው መከላከያ በመፍጠር ነው፡፡
- ይኸ የሙስና (Grand Corruption) ቅሌት ሲጋለጥ የበታቾቻቸውን ባለስልጣናት ወይም ወኪሎቻቸውን ተጠያቂ ያደርጋሉ እነርሱ በኢህጋዊ ሂደት አቀነባባሪነት ዋናዎች ሁነው ሳለ፡፡
- ማስረጃዎች እንዲጠፉ ምርመራዎችን ያዘገያሉ ወይም መርማሪው አካል ስራውን በሚገባ እንዳያከናውን በነርሱ ተጽዕኖ ስር እንዲውል ያደርጋሉ፡፡
- ብዙ ምርመራዎች አንደሚያሳዩት እና እንደሚያሳስቡት ሪፖርቶች ጁደበቃሉ በይፋም አይጋለጡም ወይም አይወጡም፡፡

እንዲሁም AYT (2009:8) እንደሚያመለክተው የፖለቲካ ሙስና ወይም "ትልቁ ሙስና" የሚከተሉትን ምሳሌዎችንም ያካትታል፡፡

- ጨረታ አውጪዎችን እና ብዙ ትርፍ ሊያስገኙ የሚችሉትን ዕቃ አቅራቢዎች በእነሱ ተፅዕኖ ስር ለማድረግ ጉቦ መስጠት ወይም ማባበል፡፡
- ቀረጥ (tax) ሳይከፈልባቸው ሸቀጦች ከውጭ እንዲገቡ ማድረግ ወይም የቀረጥ ማድበስበስ (tax evasion)
- የህዝብ መሬቶችን እና የመንግስት ቤቶችን መንጠቅ (መውሰድ)፡፡
- ሊሰሩ የማይችሉ ታላላቅ ዕቅዶችን ማቀድ እና በዚህም ሰበብ ከፍተኛ ክፍያ መጠየቅ እንዲሁም በስራ ላይ ያልዋሉ አገልግሎቶችን (የመንገድ ስራን የመሰለ) እንደተሰሩ በማስመሰል ክፍያ ማግኘት ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ቢሮክራሲያዊ ሙስና ወይም ጥቃቅን ሙስና ተብሎ የሚጠራው ሙስና በሕዝብ አስተዳደር ውስጥ የሚከሰት ነው፡፡ ጥቃቅን ሙስና በጥቅሉ እንደ ቀላል ወይም እንደ ትንሽ ነገር ይታያል፡፡ ነገር ግን በህብረተሰቡ ግንኙነት ወይም ተግባቦት ውስጥ ቀን ተቀን እንደ መደበኛ ስራ ይደረጋል፣ ይከናወናል፡፡ ይኸም ትናንሽ እጅ መንሻዎችን፣ ውለታን እና ጉቦን ያጠቃልላል፡፡ ይህ ሙስና ከላይ ሲያዩት እንደስሙ ቀላል ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ትልቁ ሙስና እጅግ ጥፋት የሚያደርስ እና የሚጎዳ ነው፡፡ በተለይ በህብረተሰቡ ስለተስፋፋ እና ጉዳት የለሽ መስሎ ስለሚታይ ነው ጉዳቱ የከፋ የሚሆነው (AYT, 2009:6) ቢሮክራሲያዊ ሙስና አንድ አንድ ጊዜ እንደ ትልቅ ሙስና ይቆጠራል፡፡ ይህ የሚወሰነውም እንደ ባለስልጣናቱ ብዛት እና እንደ ንብረቱ መጠን ነው፡፡ ፖለቲካዊ እና ቢሮክራሲያዊ ሙስና አንድ ላይ ሲፈጸም በዘዴ የተከናወነ ሙስና ይባላል፡፡ ብዙ ጊዜም የሚፈጸመው በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ነው፡፡ ፖለቲካዊ እና ቢሮክራሲያዊ ሙስና እርስ በርሳቸው ይደጋገፋሉ (Uganda: The Fight against corruption, 2003, ቅ.6)

### 3.2.2 ሊቆጣጠሩት የሚቻልና የማይቻል ሙስና

ሊቆጣጠሩት የሚቻል ሙስና ማለት በሂደቱ ላይ ሙሉ የቁጥጥር መመሪያ ማውጣት እና ህዝባዊ እርምጃ መውሰድ ማለት ነው፡፡ በዚህም ሁኔታ ቢሮክራሲያዊ ሙስናን

መቀነስ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሊቆጣጠሩት የማይቻል ሙስና ማለት ቅንጅት የጎደለው ሙስና ማለት ነው፡፡ ማለትም ለምሳሌ ጉቦ መስጠት ወዲያውኑ የተፈለገውን ግልጋሎት ለማግኘት ዋስትና አይሰጥም ወይም ያ ጉቦ በቂ ሊሆን ይችላል፡፡ (Uganda: The fight against corruption, 2003:7). እንደ ዲሞክራሲ እና አስተዳደር ማዕከል ገለጻ (2009) ሙስና ወደ ላይ ወይም አግድም ሊዋቀር ይችላል፡፡ በላዕላይ መዋቅር የሙስና ዘዴ ታችኛው አካል ከላይኛው አካል ጋር በጥቅም የተያያዘ ሲሆን በአግድም መዋቅር የሙስና ዘዴ ግን የተለያዩ የመንግስት ቅርንጫፎች ወይም ወኪሎች እርስ በርሳቸው የመጠቃቀም መረብ ይዘረጋሉ፡፡

ከላይ ስለሙስና የተገለጹት መጠኖች እና ዘርፎች የሚያመለክቱት ሙስና ምን ያህል ውስብስብ እንደሆነ ነው፡፡ ሙስናን ከህብረተሰብ ጉዳይ ነጥሎ ማየት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱን አካል ስለሚነካ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ሙስናን ለመዋጋትና ለማቆም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መስራት ያስፈልጋል፡፡

ሙስና የተለያዩ መልኮች እና አይነቶች አሉት፡፡ ከእነዚህም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው (AYT, 2009; Uganda, The Fight against corruption, 2003)፡፡

- ጉቦኛነት፡- ይኽ የሙስና አይነት የሚከናወነው ገንዘብ ወይም ሌላ ስጦታ በማበርከት ሲሆን አላማውም ሰዎች የተለየ ጥቅም እንዲያደርጉላቸው ለማግባባት ነው፡፡ ጉቦ መስጠትም ሆነ መቀበል ሁለቱም ሙስናዎች ናቸው፡፡ ጉቦ የተለያዩ ስሞች አሉት ከእነዚህም መካከል እጅ መንሻ (kick back)፣ መማለጃ መላሾ እና ማለስለሻ ይባላል፡፡

- አደራ በልነት፡- የዚህ ሙስና ዓይነት ደግሞ የህዝብ ንብረት በህዝብ ባለስልጣናት ሲመዘበር የሚያሳይ የሙስና ዓይነት ነው፡፡ በህግ አኳያ ሲታይ አደራበልነት ሙስና ላይሆን ይችላል፡፡ ብዙውን ጊዜ ሙስና የሚከናወነው በህዝብ እና በመንግስት ወኪሎች ነው፡፡ በዚህ ዓይነት አደራ በልነት እንደ ስርቆት ሊታይ ይችላል፡፡

- ማጭበርበር፡- ይህ የሙስና ዓይነት ጉቦኛነትን እና አደራ በልነትን ያካትታል፡፡ ኢኮኖሚያዊ ወንጀል እና የማታለል ተግባርም ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ራስን ማበልፀግ ከማጭበርበር ጋር ይያዛል፡፡ በግለሰብ ደረጃ ብቻም ሳይሆን በቡድን ሊሰራ ይችላል፡፡ የቡድን ማጭበርበር አንድ ነገር ለማግኘት የሚሰራ ሙስና ሲሆን የሚከናወነውም በገዢ ቡድን ሆኖ እነሱን ጥቅም ለመጨመር ነው፡፡
- ዛቻ ወይም ማስፈራራት (Extortion)፡- ይህ የሙስና ዓይነት በማስፈራራት እና በዛቻ ገንዘብን መቀማት ነው፡፡ ከጉቦ ጋርም በጣም ይመሳሰላል፡፡ ምክንያቱም ድርጊቱ ከገንዘብ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው፡፡
- አድሎአዊነት፡- ይህ ሙስና ዘመድን መጥቀም ተብሎም ይጠራል፡፡ ሂደቱም የስራ ችሎታን ትኩረት ሳይሰጥ ለዘመድ ወዳጅ እና ለጓደኞች ጥቅሞችን ወይም የስራ ዋስትና የመስጠት የሙስና ዘርፍ ነው፡፡ አድሎአዊነት እንደ ሙስና ሊቆጠር ይችላል ምክንቱም በስልጣን መባለግ ስለሆነ ነው፡፡ ሌላው የዚህ ሙስና ገፅታ ደግሞ የስራ ምደባን ይመለከታል ይህ ማለት ባለስልጣኑ የስራ ኃላፊ ከሆነ ዘመዶቹን እና ቤተሰቦቹን ጿቀጥራል፡፡ ጥቅም ባለው ቦታም ይሾማቸዋል፡፡
- ማታለል፡- ብዙ ጊዜ ይህ የሙስና አይነት የሚፈጸመው በግለሰቦች ወይም በቡድን ሲሆን አላማውም ለራስ ፍላጎት ወይም ጥቅም ሲባል ዕውነትን ማዛባት እና መጥፎ ተፅዕኖ መፍጠር ነው፡፡
- ሥልታዊ ሙስና፡- ሙስና ለረዥም ጊዜ በተደጋጋሚ ሲከወን ተቋማዊ ይሆናል፣ እንደ ስርዓትም ተቀባይነት ያገኛል፡፡ ለግልም ሆነ ለህዝብ ወይም ለአንድ የግል ድርጅት ጉዳዮችም ሆነ ለሰፊው ህብረተሰብ ለስርዓቱ ማስኬጃ እንደ ሽፋን ያገለግላል፡፡

- ዕከክልኝ - ልከክልህ ዓይነት ሙስና፡- ይህ ሙስና የሚከናወነው ቢያንስ በሁለት ግለሰቦች ወይም አካላት መካከል ነው፡፡ የጥቅም ቅብብሎሽ የሚደረገው ሕቶ ወዓ ወይም ኢ-ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ሲሆን ክንውኑ አንደኛው አካል ሌላኛውን አካል ብዙ ወጪ ያወጣ በማስመሰል ጥቅም ለማግኘት ሲፈልግ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰ መምህር ከተማሪዎች የደንብ ልብስ አቅራቢ ድርጅት ጋር በምስጢር ይዋዋልና ድርጅቱ የደንብ ልብሱን በወረደ ጥራት ሰርቶ ግን በከፍተኛ ዋጋ ለት/ቤቱ ያቀርባል፡፡ የሚገኘውን ትርፍ ለሁለት ይካፈላሉ፡፡ ተማሪዎች ግን ደረጃውን ያልጠበቀ የደንብ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ እንዲህ ሲሆን ዕከክልኝ -ልከክልህ አይነት ሙስና ተፈፀመ ይባላል፡፡

- በራስ ፈቃድ ንብረትን ያለአግባብ መጠቀም፤ አንዳንድ ግለሰቦች የመንግስት ንብረት በኃላፊነት ሲሰጣቸው በራሳቸው ፈቃድ ለግል ጥቅማቸው ያለ አግባብ ይጠቀማሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ የመንግስት ውል የወሰደ/ች ባለስልጣን ለሚሰራው ስራ የወረዱ ወይም ደረጃቸውን ያልጠበቁ ዕቃዎችን በመግዛት ከዚጸ የሚገኘውን ትርፍ ለራሱ/ሷ ሊያደርግ /ልታደርግ ትችላለች/ ይችላል፡፡ ይህ በራስ ፈቃድ ንብረትን □መቷቀም የሙስና አይነት ይባላል፡፡

- የምርጫ ጊዜ ሙስና፡- ይህ የሙስና ዓይነት የሚፈጸመው ምርጫዎችን በማቀናጀት፣ በመምራትና በመቀስቀስ ሲሆን በተለያየ ደረጃ እና ጊዜ ለድርጅታዊ፣ ለህዝባዊ፣ ፓርላሜንታዊ እና ሀገር አቀፋዊ ምርጫዎች ላይ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም የምርጫ ቁጥጥር ተብሎ ይጠራል፡፡

- ፆታዊ ሙስና፡- ይህ የሙስና ዘርፍ ደግሞ ፆታን መሰረት ያደረገ አድሎአዊ አሰራር ነው፡፡ በግልም ሆነ በህዝብ ተቋማት ውስጥ ግለሰቦችን በፆታቸው ላይ ተመርኩዞ የተለየ ጥቅም ማለትም

አገልግሎት፣ ሥራ፣ ንብረት እና ሌሎች ዕድሎችንም እንዲያገኙ ወይ እንዲያጡ ማድረግ ነው፡፡

### 3.3 ሙስናን ለመዋጋት የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርትና ሥልጠና ያለው ሚና

በአንድ ህብረተሰብ፣ ተቋማት እና ድርጅቶች ዘንድ የሙስና ዋና ምንጩ ከታወቀ ችግሩን ከስሩ ነቅሎ ለመጣል ውጤታማ ሊሆን የሚችል ዘዴ መተግበር አለበት፡፡ ከላይ እንደተገለጠው የሙስና መነሻው ከመንግስታዊ ተቋማት እና ማህበረሰባዊ ባህርያት መደበኛ የፖለቲካ ሂደት ነው[5]፡፡ ከላይ በተገለፀው ሰነድ መረጃ መሰረት ስለ ሙስና የሚሰሩ ስራዎች ወደ ተቋማዊ እና ማህበረሰባዊ ለውጥ ማተኮር አለባቸው፡፡ ተቋማትን በተመለከተ ሙስና የሚመነጨው የመንግስት ባለ ስልጣናት ሰፊ ስልጣን፣ ትንሽ ተጠያቂነት እና ምክንያታዊ ያልሆነ ማበራታቻ (አድናቆት) ሲያገኙ ነው፡፡ ይህ ማለት ብዙውን እንቅስቃሴ የመንግስት ባለስልጣናት ከተቆጣጠሩት ብዙ ሙስና የመፈፀም ዕድሎች ያገኛሉ ማለት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ዝቅተኛ ምርመራ እና ቅጣት በፈጻሚዎቹ ላይ ከተካሄደ ትልቅ የሙስና አደጋ ይከሰታል፡፡ ከዚህም ይበልጥ ደግሞ ለሰራተኛ ዝቅተኛ ደሞዝ፣ ለጥሩ ስራ ዝቅተኛ ምስጋና፣ የስራ ዋስትና አለመኖር እና በህዝብ አገልግሎት ውስጥ የባለሙያ ክብር አለመስጠት፣ ለመንግስት ባለስልጣናት ለራሳቸው ጥቅም ላደረጉት ስራ ከፍተኛ ማበረታቻ /ሽልማት/ መስጠት እና ሕዝብን ከማገልገል ይልቅ ራሳቸውን ሲያገለግሉ ይህን እና ይህን የመሰለ ሙስና ሲፈጸም ሙስና ስር እየሰደደ ይሄዳል፡፡ ይህን የመሰለ ተቋማዊ ሙስናን ለመዋጋት የሚከተሉትን ሃሳቦች ማካተት ያስፈልጋል፡፡

- በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመንግስትን ሚና መቀነስ (የስልጣን ገደብ ማድረግ)
- ግልፅነትን፣ ኃላፊነትን እና ዕቀባን ማጠናከር (ተጠያቂነትን ከፍ ማድረግ)

[5] Center for Democracy and Governance, 1999)

- ○ በህዝብ አገልግሎት ውስጥ የስራ ቅጥር ሂደትን እንደገና መቅረፅ (ማበረታቻዎችን ማሻሻል)

በተጨማሪም ከላይ የተጠቀሰው መረጃ እንደሚያመለክተው ማህበረሰቡን በተመለከተ ሙስናን ለመታገል በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ፀረ-ሙስና ጥረቶች መደረግ አለባቸው፡፡ እንደነዚህ ያሉ ጥረቶች ሙስና በአንድ ሀገር ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ የሚያስከትለውን ኪሳራ ህዝቦች /ዜጎች እንዲጸውቁ ያደርጋሉ፡፡፡ ይህ ማለት ሙስና አጥፊ ክስተት መሆኑን ለህዝብ ማሳመን ማለት ነው፡፡ ትምህርት በአንድ ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ የለውጥ ሚና እንደሚጫወት ሁላችንም እናውቃለን፡፡ የማህበረሰብ ባህርይን አስመልክቶ ቆስጣንጢኖስ (2008:1) የሚከተለውን አስቀምጧል፡፡

ሙስና ብቻውን ተነጥሎ የሚታይ ጉዳይ አይደለም፡፡ በውጤቱም ሙስና ማህበረሰቡን ሊያበረታታ ወይም ሊከለክል ይችላል፡፡ ያለ ማህበረሰብ ንቁ ተሳትፎ ሙስናን መዋጋት የሚታሰብ አይደለም፡፡ የሙያ ማህበራት፣ የሲቪል ማህበራት፣ የሰባዊ መብት ተከራካሪ አካላት፣ የማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የተጠቃሚዎች ህብረት እና የሃይማኖት መሪዎች ሙስናን ለመዋጋትና ከፍተኛ የመንግስትን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ሕብረት ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ሙስና የሚያስከትለውን ሰፊ ጥፋት በማሳወቅ እና በማንቃት ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ሙስና የብዙ ምክንያቶች (factors) ውጤት ነው፡፡ እንደ AYT (2009:16) ገለጻ በኬንያ ብሔራዊ የሙስና ግንዛቤ ጥናት ያሳየው የሙስና ዋናዎቹ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው ብሏል፡፡

- ስግብግብነት ወይም እራስ ወዳድነት
- ድህነት

ስግብግብነት/ራስ ወዳድነት፣ ድህነት፣ ዝቅተኛ የስራ ክፍያ፣ ሥራ አጥነት፣ የኑሮ ውድነት፣ ደካማ አመራር፣ የሞራል ውድቀት፣ ዝቅተኛ የህግ ከለላ፣ ባህላዊ አስተሳሰቦች፣ የቁጥጥር እና የተጠያቂነት ማነስ፣ ተስማሚ ሪፖርት አለመኖር፣ የስራ

ዋስትና አለመኖር፣ ነጻ እና አስተማማኝ የፍትሕ ስርዓት ማጣት የሙስና ዋና ምክንያቶች ናቸው፡፡

በተቋማዊም ሆነ ማህበረሰባዊ ደረጃ ስለ ሙስና ከተሰጡት ማጠቃለያ መንስኤዎች እና መፍትሂዎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው (ሠንጠረዥ2ን ይመልከቱ)፡፡

**ሠንጠረዥ 2 ጥቂት የሙስና መንስኤዎችና መፍትሔዎች**

| | |
|---|---|
| ተቋማዊ መንስኤዎች<br>• ሰፊ ስልጣን መስጠት<br>• ዝቅተኛ ተጠያቂነት<br>• ምክንያታዊ ያልሆነ ማበረታቻ /ሙገሳ/<br><br>ማህበረሰባዊ መንስኤዎች<br>• ፀረ-ህግ ልማዶች | ተቋማዊ መፍትሂዎች<br>• ስልጣንን መገደብ (የግለሰብ ነጻነትን ከፖለቲካ ነጻ ማድረግ)<br>• ተጠያቂነትን፣ ግልፅነትን፣ ኃላፊነትን፣ እና ማዕቀቦችን ማበልፀግ<br>• የስጦታ ልውውጦችን ማድረግ፣ የስራ ውጤትን መሰረት ያደረገ ማበረታቻዎችን እና ጥሩ ክፍያ መስጠት<br><br>ማህበረሰባዊ መፍትሂዎች<br>• ስለ ሙስና ጎጂነት ግንዛቤ መፍጠር ወ.ዘ.ተ.. |

**ምንጭ:-** Center for Democracy and Governance: A hand book on fighting corruption (1999).

ስለ ሙስና ግንዛቤ መፍጠር ስራ በተለያዩ ቦታዎች ቢካሄድም በብዙ ታዳጊ ሀገሮች ግን የሙስና ጎጅነት በስራዐተ ትምህርታቸው ውስጥ ቀርፀው ወጣቱን እያስተማሩ ይገኛሉ፡፡ በነዚህ ሀገራት ውስጥ አብዛኛው እና ወደፊት ተረካቢው ወጣቱ እንደመሆኑ መጠን በዚህ አኳያ ት/ቤቶች በአሁኑ ወቅት ሙስና

የሚያደርሰውን ጥፋት ለማሳወቅ የመሪነት ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡ ሙስና ከሚያመጣቸው አፍራሽ ተፅዕኖዎች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ዕድገትን ይገድባል ወይንም ያቀረቁዛል
- ዲሞክራሲን እና መልካም አስተዳደርን ይሸረሽራል/ ያደክማል
- ዲሞክራሲን እና ጤናማ ውድድርን ያጠፋል፡፡
- ግልፅነት እና ተጠያቂነት እንዳይኖሩ ያደርጋል፡፡
- በሕግ ስርዓት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡
- በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ አላስፈላጊ ወጪን ያስከትላል፡፡
- ስራቸውን በሚገባ እንቴያከናውኑ የግለሰቦችን ችሎታ ያኮስሳል፡፡ (AYT,2009)

ይህን የሙስና መጥፎ ተፅዕኖ ለመቀልበስ በብዙ አገሮች የስነምግባር ትምህርቶች በት/ቤቶች እየተሰጡ ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት ሙስናን ለመታገል ከሚደረጉ ዋና ዋና የዕቅድ አካላት ውስጥ ፀባይን ማሻሻል እና የስነምግባር ዕሴቶችን መማር ማስተማር አንዱ እና ዋነኛው ነው (Hallak and Poisson, 2000)፡፡

በተጨማሪም ሙስና የሚያስከትለውን ጉዳት በጠቅላላ ለህዝቡ ማስተማር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ይኸም በብዙ የአፍሪካ ሀገራት ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ (AYT 2009) እንዲህ ይላል፡፡

ለህብረተሰቡ ስለ ሙስና ማስተማር አስፈላጊ ነው፡፡ ህዝቦች የሙስናን ምንነት አስረግጠው ከተረዱ ለይቶ ማውጣት እና መናገር ያስችላቸዋል፡፡ እንዲሁም ትምህርት የህዝቡን ንቃተ ህሊና ያዳብራል የሙስናን መንስኤ እና ውጤትም ለይተው እንዲረዱ እና በተለያዩ ተቋማት የሚደረገውን ፀረ-ሙስና ዘመቻ በህግ ማዕቀፍ ስር ሆነው እንዲታገሉ አቅም ይፈጥርላቸዋል፡፡ ዜጎች ስለ ሙስና በቂ ዕውቀት ካላቸው ሙስናን ለመዋጋት በከፍተኛ ጉጉት ይነሳሳሉ በስኬትም ያጠናቅቃሉ፡፡

በብዙ የአፍሪካ ሃገራት ውስጥ የወጣቱ ቁጥር አብዛኛውን □ሕዌብ ቁጥር ይሸፍናል፡፡ እናም ሙስናን ለመታገል የሚደረገው እቅድ ወይም ፖሊሲ ለወጣቱ ትኩረት መስጠትና ወደ ትግሉ ጎራ ለመቀላቀል የተለያዩ የመሳቢያ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ የሚከተለው በኬንያ እየተደረገ ያለው የመሳቢያ ዘዴ ትንሽ ፍንጭ ይሰጣል፡፡ በዚሁም በሰፊው ይታመንበታል፡፡

ትልቁ ሙስና በዋናነት የሚፈፀሙ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ባያዘውና በቀደመው ትውልድ ሲሆን ይህ ትውልድም በቆየ የሙስና መረብ የተተበተበ ነው እንዲህ ከሆነ ዘንድ አሮጌውን ትውልድ በአዲሱ ትውልድ ለመተካት ወጣቱን ነፃ ውድድር መስጠትና ወደ ስልጣን ወይንም አመራር ማምጣት ተገቢ ነው፡፡ ይህም በፀረ-ሙስና ትግሉ አጀንዳ ላይ አዲስ ሃሳብና መነቃቃት ይፈጥራል (AYT,2009)፡፡

በዚህም ምክንያት የኬንያ መንግስት □ና አንድ አንድ መንግሥ□ዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በዚህ መንገድ ሙስናን ለመዋጋት እና ልዩ ትኩረት በመስጠት ጥረት እያደረጉ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ውጤቱን ለመሳብ እና በፀረ-ሙስናው ዘመቻ ለማቀናጀት የሚከተሉት የመሳቢያ ዘዴዎች በተግባር ላይ እየዋሉ ናቸው፡፡

1. ትምህርት (Education)፡ የኬንያ መንግስት ለዜጎቹ በተለይም ለወጣቱ ከሙስና እና ከመልካም አስተዳደር ጋር በተያያዘ ጉዳይ ትክክለኛ መረጃ መስጠት አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ስለሆነም ሙስናን አላማው ያደረገ ትምህርት መስጠት ወጣቱን ለመልካም አስተዳደር ጉጉት እና ዝግጁነት እንዲኖረው አዲስ አቅጣጫ ያስይዛል ተብሎ በጥብቅ ይታመናል፡፡ ይህን ተከትሎ በመልካም አስተዳደር ላይ ያተኮሩ ኮርሶች ለ2ኛ ደረጃ እና ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እየተሰጡ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ስለ ሙስና አስከፊነት ለማሳወቅ ወጣትመር የሆኑ የግንዛቤ ማሰጨበጫ ዘመቻዎች እንደ አማራጭ የትምህርት መንገዶች እየተወሰዱ ናቸው፡፡

2. አዳዲስ ሀሳብ የመፍጠር ዘመቻዎች፡- ከትምህርት በተጨማሪ ወጣቱን አላማ ያደረጉ እና የተቀናጁ አዳዲስ የውድድር ስራዎችን በማድረግ በተለያዩ ደረጃዎች እርምጃዎችን መውሰድም ሙስናን ለመዋጋት ከሚደረጉት ጥረቶች

ወጣቱን በማነሳሳት እና በማስረፅ ሰፊ ሚና ይጫወታሉ፡፡ አዎንታዊ ሚና ያለው የመገናኛ ብዙኃንም (Media) ከአዳዲስ ፈጠራዎች ዘመቻ እንደ አንዱ መወሰድ አለበት፡፡

3. ከወጣቱ ቡድኖች /ድርጅቶች ጋር ሽርክና መፍጠር፡- ሙስና በጥቂት ወገኖች ወይም ድርጅቶች ብቻ ሊታገሉት የሚቻል አይደለም፡፡ ሙስናን ለመዋጋት ከተለያዩ ወገኖች ጋር ሽርክና መፍጠር /በጋራ መስራት/ ወደ ሰፊው የህብረተሰብ ክፍል ለመድረስ ስኬታማ መንገድ ነው፡፡

4. የተለያዩ አውታሮችን መዘርጋት (Networking)፡- በኬንያ መንግስት እና ሌሎች የማህበረሰብ ድርጅቶች የተለያዩ የወጣት ባለሙያዎችን እና ሌሎችን በመንግስትም ሆነ በግል ማህበራት በአመራር ሰጭነት ያሉ ወጣቶችን በመደገፍ ሙስናን ለመዋጋት እና መልካም አስተዳደርን ለማምጣት ይመለከታቸዋል ተብሎ ስለሚታሰብ ስብሰባዎችን በማዘጋጀት እና በውይይት ለመፍታት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

5. በአስተዳደር ተቋማት ውስጥ ምርጫ እና ሹመት መስጠት፡- ወጣቶች የነገ መሪዎችን ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ እነሱን ወደ ስልጣን እና አመራር ሰጭነት ደረጃ ለማምጣት ጠንካራ እርምጃ እየተወሰደ እንዳለ ምልክቶች/ማሳያዎች አሉ፡፡ ስለሆነም ወጣቶቹ በዚህ አኳያ ያለውን ዕድል ተጠቅመው ችሎታቸወን/ተሰጧቸውን በማሳየት በተለያዩ ደረጃዎች ሙስናን መዋጋት ይችላሉ፡፡ እንዲህ ከሆነ ዘንድ ሙስናን ለመዋጋት የሚሳተፉ ቀደም ያሉ ግለሰቦች በአመራር ሰጭነት ያሉ ወጣቶችን መምከር እና መልካም ምሳሌ መሆን ይጠበቅባቸዋል (AYT, 2009)፡፡

ከላይ የቀረበው ፅሑፍ እንደሚያሳየው ሙስና ምን ያህል ውስብስብ ጉዳይ እንደሆነ እና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማንኛውንም አካል እንደሚጎዳ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 3 የአካባቢያዊ ደረጃን መሰረት ያደረገ የICVS የጥናት ዳሰሳ

| የተለያዩ የዓለም ክፍሎች | ጉቦ እንዲሰጡ የተጠየቁ ዜጎች በመቶኛ |
|---|---|
| ሰሜን አሜሪካ አውስትራልያንና ጃፓን | 0.3 |
| ምዕራብ አውሮፓ | 0.8 |
| ኤስ ኤ ዲ ሲ (SADC) | 9.0 |
| አፍሪካ ሳድክን ጨምሮ (Africa including SADC) | 14.7 |
| እስያ | 13.8 |
| ማዕከላዊ እና ምስራቃዊ አውሮፓ | 14.5 |
| ላቲን አሜሪካ | 18.2 |
| መካከለኛው ምስራቅ እና ሰሜን አፍሪቃ | 27.9 |

ምንጭ፡- ሙስና እና ፀረ-ሙስና በደቡባዊ አፍሪቃ (Corruption and Anti-corroption is southern Africa (2002).

ለምሳሌ፡- በሰንጠረዥ 4 ላይ እንደሚታየው ሙስና አለም አቀፋዊ ይዘት ያለው እስከሆነ ድረስ ሙስናን ለመዋጋት አንድ አይነት የስልጠና እና አንድ አይነት የትምህርት ዘዴ ሊኖር አይችልም፡፡ እያንዳንዱ ሀገር፣ እያንዳንዱ ድርጅት ወይም ተቋም (ባህል፣ ልምድ፣ ወዘተ መሠረት) ሙስናን ለመዋጋት በሚያደርገው ዕቅድ ላይ ልዩ ትኩረት እና አቅጣጫ መያዝ ያስፈልገዋል፡፡ ከተለያዩ ሀገራት ተሞክሮዎች አንጻር በተለይም በአፍሪካ ሀገራት ጥናቱ የሚያሳየው ይኸንኑ ነው፡፡

## 3.4 የፀረ- ሙስና እንቅስቃሴዎች (ጅምሮች) በኢትዮጵያ

ሙስና አዲስ ክስተት አይደለም፡፡ እናም እያንዳንዱ ሀገር የራሱ የሆነ ተሞክሮ አለው፡፡ ኢትዮጵያም የራሷ የሆነ ልምድ አላት፡፡ ኢትዮጵያ ሙስናን ለመዋጋት በ2001 □ኤ.አ. የኢትዮጵያ የፌደራል □ስነምግባር እና □ፀረ-ሙስና ኮሚሽን (FEACC) የሚባል ተቋም አቋቁማለች፡፡ ተቋሙ (FEACC) ከሚያተኩርባቸው ጉዳዮችም መከላከል፣ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርትና ሥልጠና፣ የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድ ሙስናና ብልሹ አሠራርን መከላከል እና የሙስና ወንጀልን መመርመር፣ ማጋለጥና ለሕግ ማቅረብ ናቸው፡፡ ተቋሙ ከተመሰረተ ጀምሮ

ለትምህርትና ለስልጠና ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው በተቋሙ በሚታተም ጽሑፍ ተደጋግሞ እንደተገለፀው በተለያዩ ሚድያዎች አማካኝነት (በህትመት፣ በራዲዮ፣ በቴሌቭዥን) በውይይት እና በትምህርታዊ ጉባኤ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ እየሠራ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ተቋሙ የአሰልጣኞች ስልጠና ጀምሯል፡፡ ከዚህ መረጃ በመነሳት ተቋሙ ቀደም ሲል የግንዛቤ ፈጠራ መርሐ ግብር እያለ ሲአካሂድ በቆየው ምትክ በ2000 ዓ.ም እ.ኤ.አ የስነ-ምግባር እና የፀረ- ሙስና ትምህርትን ለማስፋፋትና የአሰልጣኞች ስልጠና መርሐግብር የሚል የማስፋፊያ ዘዴ ቀይሶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል (Ethics, 2000 E.c)::

እንደ FEACC ገለጻ ከላይ የተጠቀሱት ዘዴዎች በሀገሪቱ ውስጥ ብዙ ሕዝብን ተደራሽ ያደርጋሉ፡፡ በተጨማሪም FEACC ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በመደበኛ ትምህርት ውስጥ የስነ-ምግባር እና ስነ-ዜጋ ሥርዓተ-ትምህርት በመቅረጽ እና በማስተዋወቅ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ በብዙ መንግስታዊ ተቋማት በመላ ሀገሪቱ ውስጥ ሙስናን ለመዋጋት የስነ-ምግባር እና ፀረ ሙስና ቢሮዎች ተከፍተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ሙስናን ለመዋጋት በሚደረገው ጥረት አንጻር ብዙ ርቀት መሄድ ያስፈልጋል፡፡

እንደ ተስፋዬ (2007፡13) አባባል በኢትዮጵያ ዋና ዋና የሙስና ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፡፡ ደካማ አስተዳደራዊ ስርዓት፣ ግልፅነት እና ተጠያቂነት አለመኖር፣ ዝቅተኛ ደረጃ ያለው ዲሞክራሲያዊ ባህል እና ልምድ፣ የዜጎች ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፣ ግልፅ የሆነ ደንብ እና መብት አለመኖር፣ ዝቅተኛ ተቋማዊ ቁጥጥር፣ ከመጠን ያለፈ ድህነት እና ፍትሕ ማጣት፣ ጎጂ ልማዳዊ ተግባራት እና የተማከለ ስልጣን እና ሀብትን መጠቀም ናቸው፡፡

በመሰረቱ ሙስና የሚመነጨው ከመንግስታዊ ተቋማት ባህርያት እና ከማህበራዊ ባህርያት ለመደበኛ ፖለቲካዊ ሂደት ካላቸው ግንዛቤ ነው፡፡ ለነዚህ መሰረታዊ የሆኑ ምክንያቶች ምላሽ ወይም መፍትሄ ማምጣት የሚቻለው ለስልጣን ገደብ እንዲሰጡ ተቋማትን እንደገና ማቋቋም፣ ተጠያቂነትን ማስረጽ እና ማበረታቻዎችን ለለውጥ መመደብ አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም ፖለቲካዊ ፈቃደኝነት እና ቀጣይነት ያለው

የፀረ-ሙስና ጣልቃ ገብነት እንቅስቃሴ እንዲኖር ማህበራዊ ለውጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል (Center for Democracy and Governance, 2009):: ስለዚህ ማንኛውም የትምህርት እና ስልጠና መርሀ-ግብር ሙስናን ለመዋጋት በሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉ ከላይ የተጠቀሱትን የሙስና ምንጮች ትኩረት መስጠት ይገባዋል፡፡ ይህም ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ የተወሰደ ነው፡፡

በሳድክ (SADC 2002) ጥናት መሰረት የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴዎች ዋና የመሰረት ድንጋዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፖለቲካ ፈቃደኝነት፡፡
- አስተማማኝ የፀረ-ሙስና ህግ፡፡
- በቂ የህግ ማስፈጸሚያ መሳሪያ አቅርቦት፡፡
- ተመጣጣኝ የሆነ ሰባዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ተፈጥሮአዊ ሀብት (rsources) ክፍፍል፡፡
- ምንም ያህል ጊዜ ይውሰድ በፀረ ሙስና ዘመቻው ለመቀጠል መወሰን፡፡
- ነጻ፣ የሰለጠነ፣ አስተማማኝ እና ከሙስና የጸዳ የፍትሕ አካል፡፡
- በሚከተሉት መስኮች የሰለጠነ የሰው ኃይል፡፡
- በምርመራ
- ወደ ፍትህ በማቅረብ
- በተጠያቂነት
- በህዝብ ትምህርት
- ሙስናን በመከላከል
- ውጤታማ በሆነ የህዝብ ማስተማር ዘመቻ/ትግል፡፡
- ነጻ፣ ጠንካራ እና በሰለጠነ መገናኛ ብዙኃን
- ቀጣይነት ባለው የህዝብ ድጋፍ

# 4. ሙስና እና ሕግ

## 4.1 መግቢያ

ሙስና እና ሕግ እጅግ የተቆራኘ ግንኙነት አላቸው፡፡ ግንኙነታቸው ግን በተለይ በተሟላ ሁኔታ የወጣና በአግባቡ የሚተገበር ሕግን በተመለከተ የተፃራሪነትና የአጥፊና ጠፊ ዓይነት እንጅ የተጣጣመ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የሙስናን ምንነት ሁሉንም ሰዎች በቀላሉ በሚያግባባ ሁኔታ መተርጐም አስቸጋሪ ቢሆንም በኰሚሽኑ ረቂቅ የፀረ ሙስና ፖሊሲም እንደተጠቀሰው ሙስና ራስን ለመጥቀም ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት ሲባል አንድ ነገር በማግባቢያነት ማቅረብ፣ መስጠት፣ ማመቻቸት ወይም መቀበል፣ ቃል መግባት፣ ገፀበረከት ማቅረብ፣ አለዚያም በቃላት ወይም በተግባር ማስፈራራት፣ ዛቻ መፈፀም፣ ሥልጣንን ያለ አግባብ በመጠቀም ወይም ወጥነት በሌለው ሁኔታ አሠራሮችን በመተግበር ተጽዕኖ አሳድሮ በሠራተኞቹ ወይም በኃላፊዎቹ የሚወሰዱት እርምጃዎች ወይም የማይወሰዱት እርምጃዎች ያለአግባብ እንዲዛቡ ማድረግ ማለት ነው፡፡ ሕግ ደግሞ በአንድ አገር ባለው ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት አካል የማህበረሰቡን አጠቃላይ ግንኙነትና የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ለመምራትና ለመቆጣጠር የወጣ ደንብ ማለት ነው፡፡

ይህ ማለት ደግሞ በሌላ አባባል ሕግ በይፋ የወጣ የሕብረተሰብ ግንኙነት መቆጣጠሪያ አስገዳጅ መሣሪያ ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ሕግ ሙስናን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ዓይነተኛ መሣሪያ በመሆን ያገለግላል፡፡ ይህም በመሆኑ ሙስና አለ የሚባለው ሰዎች ለግል ጥቅም ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት ሥልጣንን ወይም ሌላ የግል ቀረቤታን መሣሪያ በማድረግ ማህበራዊ ግንኙነቱን ተገቢ ባልሆነ መንገድ በመቆጣጠር የጋራ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የፈፀሙት ተግባር የማህበረሰቡን ግንኙነት ለመቆጣጠር የወጣውን ሕግ በመጻጸር የተፈፀመ ሲሆን ነው፡፡ ባጭሩ ሙስና ሕግ የደነገገውን በመተላለፍ ለልዩ ልዩ ጥቅም ወይም የመንግሥት ሥልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም ተገቢ ያልሆነ ድርጊት መፈፀም ማለት ነው፡፡ ይህን መሠረት በማድረግም ሙስናን ለመቆጣጠርና መልካም ሥነምግባርን ለማዳበር የወጡትን የኢትዮጵያ ሕጐች ይዘትና ዓላማ ባጭሩ ከዚህ በታች እንመለከታለን፡፡

### 4.1.1 የፀረ-ሙስና ሕግን ማውጣት አስፈላጊ ያደረጉ ምክንያቶች፣

በኢትዮጵያ አሁን እየተደረጉ ላሉት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች የሕግ መሠረቱ ነሐሴ 15 ቀን 1987 ዓ.ም የወጣው የኢፌዲሪ ሕገመንግሥት ነው፡፡ የሥርጭቱ መጠንና ደረጃ በጥናት በግልጽ የታወቀ ባይሆንም በ1987 ዓ.ም ሕገመንግሥቱ ከመውጣቱ በፊትም ሙስና በኢትዮጵያ የማይናቅ ክስተት እንደነበር የሚያከራክር አይደለም፡፡

ሕገመንግሥቱ ከግብ ለማድረስ በመግቢያው ያስቀመጣቸው መሠረታዊ ዓላማዎች ደግሞ ዲሞክራሲን ማስፈን፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገትን ማፋጠን እና በሕግ የበላይነት ላይ የተመሠረተ ማህበረሰብ መገንባት የሚሉ ናቸው፡፡ ዲሞክራሲን ለማስከበርና ለማዳበርም የሰው ልጆችን መብት ማስከበር ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ይህን እውን ለማድረግም ሆነ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገትን እግቡ ለማድረስ፣ እንዲሁም የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ መልካም አስተዳደርን መገንባትም አስፈላጊ ነው፡፡ ሙስና ደግሞ መልካም አስተዳደርን ለመገንባት የሚደረግ ጥረት ትልቅ እንቅፋት ነው፡፡ ስለዚህም ሙስናን በመዋጋት ሳይቆጣጠሩ መልካም አስተዳደርን እገነባለሁ ማለት ውጤት አልባ ድካም መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡

መልካም አስተዳደር ማለትም የአገርን ሃብት፣ አገራዊ ጉዳዮችን፣ የሕብረተሰብ ጉዳዮችንና አገልግሎቶችን ግልጽነት በሰፈነበት፣ ተጠያቂነት ባለበትና በፍትሐዊነት ማስተዳደር ማለት ነው፡፡ ይህን በሂደት ለመገንባት ደግሞ ሰዎች ሙስናን በተደራጀና በተቀናጀ መልክ መዋጋት እንዲችሉ የሚያደርግ የተመቻቸ ሁኔታ እንዲኖር ለማድረግ ተገቢ ተቋማትን መመሥረትና ለአሠራር መሠረት የሆኑ ሕጐችን ማውጣት የግድ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ከላይ ካነሳናቸው ነጥቦች የምንገነዘበውም ዲሞክራሲን መገንባት፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገትን ማፋጠን፣ የሕግ የበላይነትንና ፍትሕን ማስፈን፣ የሰው ልጅ መብቶችን ማስከበር፣ መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥና በመልካም ሥነምግባር የታነጸ ሕብረተሰብ መገንባት የተጣጣሙና ተደጋጋፊ ሲሆኑ ሙስና ግን የእነዚህ

ተግባራዊነት መሰናክል መሆኑን ነው፡፡ ይህ ሆኖ እያለ ግን ሙስናን ለመዋጋት የፖለቲካ ቁርጠኝነትን መሠረት አድርጐ ድርጊቱን ለመዋጋት የሚያስችል ኃላፊነት የተሰጠው ተቋምም ሆነ ይህን የዕድገት ጸር የሆነ አስነዋሪ ተግባር ለመዋጋት የሚረዱ ግልጽና ዝርዝር ሕግ እስከ 1993 ዓ.ም አልነበረም፡፡ ይህ በሕገ መንግሥቱ የሰፈረው ዲሞክራሲን የማስፈን፣ እድገትን የማፋጠን፣ የሕግ የበላይነትን የማረጋገዓ ዓላማና በአገሪቱ የታየው አጠቃላይ ለውጥና የተከሰተው አግባብ ያለው ሕግና ኃላፊነት የተሰጠው ተቋም አለመኖር ክፍተት የፀረ-ሙስና ሕጐችን ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ መውጣት አስፈላጊ እንዳደረገው ከጠቀስነው አጠቃላይ ሁኔታ መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 4.1.2 የሕጐቹ አጠቃላይ ዓላማ፣

ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ ሙስናን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚረዱ የተለያዩ ሕጐች የወጡ ቢሆንም[6] መሠረታዊ ዓላማቸው የተደነገገው ግን በኰሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ነው፡፡ በመጀመሪያ በአዋጅ ቁጥር 235/1993 ቀጥሎም ይህን አዋጅ ባሻሻለው አዋጅ ቁጥር 433/1997 እንደተደነገገው ዓላማዎቹ አጠቃላይና ዝርዝር ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ አጠቃላይ አላማዎች ሶስት ሲሆኑ የተደነገጉትም በአዋጁ መግቢያ ላይ ነው፡፡

እነርሱም፡-

1. ሙስና እና ብልሹ አሠራር የአገሪቱን ማህበራዊ፣ ኢኰኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት እንዳይገታ መከላከልና መቆጣጠር፣
2. አገሪቱ የጀመረችው የዕድገትና የዲሞክራሲ ግንባታ የተፋጠነና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን ለማስቻል ሙስናና ብልሹ አሠራርን በቁጥጥር ሥር ማዋል፣
3. ሙስናን እና ብልሹ አሠራርን ለመሸከም የማይፈልግና በብቃት ለመዋጋት ዝገጁ የሆነ ሕብረተሰብ መፍጠር፣

[6] የወንጀል ሕግ፣ የንብረት ምዝገባ አዋጅ፣ የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነሥርዓትና የማስረጃ ሕግ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

ዝርዝር ዓላማዎቹም እንደዚሁ ሶስት ሲሆኑ የተደነገጉትም በአዋጁ አንቀጽ 6 ነው፡፡ እነርሱም፡-

1. የሥነምግባርና የፀረሙስና ትምህርቶችን በማስፋፋት የነቃና ሙስናን ሊሸከም የማይችል ሕብረተሰብ እንዲፈጠር ጥረት ማድረግ፣
2. የሙስና ወንጀልንና ብልሹ አሠራርን በመከላከል፣ በማጋለጥ፣ በመመርመርና በመክሰስ በአገሪቱ ውስጥ ሐቀኛ የሕዝብ አገልግሎት እንዲሰፍን ጥረት ማድረግ፣
3. ለመንግሥት ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች የሚያገለግሉ የሥነ ምግባር ደንቦች እንዲዘጋጁ ማድረግ፣ ተፈፃሚነታቸውን መከታተልና ሌሎች አካላት ለሚያዘጋጃቸው የሥነምግባር ደንቦች ድጋፍ ማድረግ፤

   የሚሉ ናቸው፡፡

እነዚህ ዓላማዎች በኰሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቢደነገጉም ተግባራዊነታቸው የሚረጋገጠው ግን በወንጀል ሕጉ፣ በንብረት ምዝገባ አዋጁ፣ በፀረ-ሙስና ልዩ የሥነሥርዓትና የማስረጃ ሕጉና በሌሎች ሙስናን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ግንኙነት ባላቸው ሕጐችና በኰሚሽኑ መመሪያዎች ዝርዝር ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡

## 4.2 የሕጐቹ አጠቃላይ ይዘትና ሙስናን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚኖራቸው ፋይዳ

### 4.2.1 የተሻሻለው የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97

ይህ አዋጅ ሙስናን ለመዋጋት ለሚደረገው ጥረት መሠረት ነው፡፡ እዚህ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የሚያበቁ ደግሞ ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም ምክንያቶች አንዱ ሙስናን የመከላከልና የመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጠው ራሱን የቻለ የፌዴራል ተቋም ማቋቋሙ ነው፡፡ ይህም ለፀረ-ሙስና ትግሉ

አስፈላጊ የሆነውን ቀደም ብሎ የነበረውን  የተቋም አለመኖር የክፍተት ችግር እንዲፈታ አድርጎታል፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በሕጉ የተቋቋመውን የፀረ-ሙስና እና የሥነ ምግባር ኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባሮች በመለየት በዝርዝር ማስቀመጡ ነው፡፡

በተሻሻለው የማቋቋሚያ አዋጅ ለኮሚሽኑ የተሰጠው አጠቃላይ ሥልጣንና ተግባር ሙስናንና ብልሹ አሠራርን መከላከልና መቆጣጠር ሲሆን ይህን ሥልጣንና ተግባሩን ተፈፃሚ በማድረግ በሕጉ የተፈለገው ግብ ላይ ለመድረስም ሶስት ዋና ዋና ኃላፊነቶች ተሰጥተውታል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 7 እንደተደነገገው የመጀመሪያው ኃላፊነት ሙስና ለህብረተሰብ ሁለንተናዊ እድገት ጎጂ ስለመሆኑ ሕዝቡን ማስተማርና በሕዝብ አገልግሎቶችና በሕብረተሰቡ ውስጥ እንዲስፋፋ ዓረት ማድረግ ነው፡፡

ይህ ደግሞ ለሙስና መስፋፋት ምክንያቶቹ የተወሰኑ የህብረሰቡ ክፍሎች መሆናቸውንና በሙስና ተጎጂውም ህብረተሰቡ ራሱና አገር በአጠቃላይ መሆኑን አምኖ በመነሳት ስለሙስና በማስተማር ሙስና ሊፈጽሙ የሚችሉ ሰዎችም በእውቀት ላይ በመመስረት ከድርጊቱ እንዲቆጠቡ ለማድረግ፣ ህብረተሰቡ በአጠቃላይም ሙስናን ለመዋጋት የሚያስችል እውቀቱን እንዲያዳብርና እምነቱን እንዲያጠናክር የሚያደርግና የኮሚሽኑን ትግል ከሕዝቡ ትግል ጋር የሚያስተሣሥር ተመራጭ የሙስና መዋጊያ ስልት ነው፡፡

ሁለተኛው የኮሚሽኑ ኃላፊነት ደግሞ በመንግሥት ተቋማት ውስጥ ለሙስናና ለብልሹ አሠራር መስፋፋት አመቺ የሆኑ የአሠራር ሥርዓቶች በጥናት ተለይተው እንዲታወቁ ማድረግና ችግሮች መሻሻላቸውን መከታተልና ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አግባብ ላለው አካል ማሳወቅ ነው፡፡ የአሠራሮች የተዛባ መሆን ሙስናን ለመከላከልና ለመቆጣጠርም ሁኔታዎችን አስቸጋሪ ስለሚያደርግ አሠራሮችን የተስተካከሉ ማድረግ ሙስናን ለመዋጋት ግማሽ መንገድ እንደመሄድ ያህል ነው፡፡ ምክንያቱም ቤትን ከስርቆት ለመከላከል ሌባ ሊገባባቸው የሚችል በሮችን ሁሉ

አጥብቆ መዝጋት ለጥበቃው ከፍተኛ አጋዥነት እንዳለው ሁሉ ሙስናን ለመከላከልና ለመቆጣጠርም የአሠራር ሥርዓቶችን ግልጽ፣ ተጠያቂነት ያለበት፣ ለቁጥጥርና ለክትትል የተመቻቸና በሕግ ላይ የተመሠረተ ማድረግም ሁለት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

አንደኛው ጠቀሜታ አሠራሩን ማስተካከል የአሠራር ችግር ባለባቸው ተቋማት ውስጥ የሚሠሩት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሳያውቁና ሳያስቡት በሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ለማድረግ ከፍተኛ እገዛ የሚሰጥ መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው ጠቀሜታ ደግሞ በተቋሙ ኃላፊዎችና ሠራተኞች እንዲሁም በኮሚሽኑ ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት ለሚደረገው ጥረት ውጤታማነት የአሠራር ችግር ካለበት ተቋም ይልቅ የተስተካከለ የአሠራር ሥርዓት ያለበት ተቋም ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአሠራር ችግሮችን አስቀድሞ በጥናት በመለየት እንዲስተካከሉ መምከርና ማሳሰብ በሙስና ብዙ ንብረት ሳይባክን ችግርን በቀላሉ መግታት ከመሆኑም በላይ የሙስና ችግሩ ከተፈጠረ በኋላ መፍትሄ ለመፈለግ የሚያስፈልገውን የሰው ጉልበት፣ ጊዜና ወጭን የሚያስቀር የሙስና መታገያ መንገድ በመሆኑ ኮሚሽኑ አጠንክሮ ሊሠራበት የሚገባ የመከላከያ ስልት ነው፡፡

ሶስተኛው የኮሚሽኑ ኃላፊነት ደግሞ የሙስና ወንጀል መፈፀሙን መመርመርና መክሰስ እንዲሁም ከባድ የሥነምግባር መጣስ መፈፀሙን ማጣራትና እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ነው፡፡ ይህ ኃላፊነትም ከላይ እንደተጠቀሱት ሁለት የኮሚሽኑ ኃላፊነቶች ሙስናን የመከላከያና የመቆጣጠሪያ መንገድ ቢሆንም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ የሚወሰድ እርምጃ በመሆኑ የተለየ ባህሪ ያለውና ከኮሚሽኑ ጥንካሬ በተጨማሪ እንደ ፖሊሲና ፍ/ቤት ያሉ ተቋማትንም ጥንካሬና ከሙስና የፀዱ መሆን የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡

የኮሚሽኑ የሙስና ወንጀል መፈፀሙን የመመርመርና የመክሰስ ዓላማ ጥፋቱ መፈፀሙን ማረጋገጥና በጥፋተኛው ላይ በፍ/ቤት ቅጣት እንዲወሰን ማድረግ ነው፡፡ የሙስና ድርጊት የመፈፀም ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠ ሰው ላይ ፍ/ቤት ቅጣት መወሰኑ

የባከነ ንብረትን ለማስመለስም ሆነ ጥፋት ፈፃሚው ለወደፊት ተመሳሳይ ጥፋት እንዳይፈጸም እሥራትን በመሰለ ቅጣት ለመግታት የሚያስችል ቢሆንም ከዚህ በበለጠ ግን ሌሎች ሰዎች ለወደፊቱ የሙስና ተግባር ቢፈጽሙ ሊወሰድባቸው የሚችለውን የሕግ እርምጃ በማሳወቅ የማስተማርና የማስጠንቀቅ ውጤት ስላለው ሙስናን ለመከላከል ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡

የሥነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን በዚህ በሕጉ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ቅድሚያ የሰጠው በአገሪቱ ያለው የሙስና ሁኔታ ምን እንደሚመስል የዳሰሰ ጥናት እንዲካሄድ ማድረግ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ጥናቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እንዲካሄድ ተደርጓል፡፡ የጥናቱ ውጤትም ጥናቱ በተካሄደበት ጊዜ ሙስና ከዋና ዋና የአገሪቱ ችግሮች አንዱ ወደሚሆንበት ደረጃ እየደረሰ መሆኑን ጠቁሟል፡፡ (IER/AAU,2001)፡፡

ይህን መሠረት በማድረግም ኮሚሽኑ ላለፉት ዘጠኝ አመታት የሙስናን አስከፊነት፣ መልካም ሥነምግባር ሙስናን ለመዋጋት ስላለው አስተዋጽኦ በተለያዩ መንገዶችና ዘዴዎች ሲያስተምር፣ ለሙስና የተጋለጡ የአሠራር ሥርዓቶች እንዲስተካከሉ ሲመክርና መፍትሄዎች ሲጠቁም፣ በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎችን በመመርመርና በመክሰስ ሙስናን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን ያወጣቸው የተለያዩ ጽሑፎች ይጠቁማሉ፡፡ በተለይ መልካም ሥነምግባርን ለመገንባትና የሙስናን አስከፊነት ለህብረተሰቡ በማስገንዘብ በኩል የመገናኛ ብዙሃንን፣ የሕትመት ውጤቶችንና የፊት ለፊት ውይይት ዘዴን በመጠቀም ሰፊ ሥራ መከናዎኑን የኮሚሽኑ የተለያዩ ሰነዶች ይጠቁማሉ (FEACC,2009)፡፡

ለሙስና የሚያጋልጡ አሠራሮችን ማስተካከልን በተመለከተም 160 በሚሆኑ የመንግሥት ተቋማት ጥናት በማድረግ ማስተካከያ እንዲደረግ እርምጃ መወሰዱን በ2003 □ም. መጀመሪያ ከወጣው የኮሚሽኑ ፕሮፋይል መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚሁ በጥናቱ በተሸፈነው ከ1993 ጀምሮ ባለው የዘጠኝ አመታት ጊዜ ኮሚሽኑ 1500

የሚሆኑ የሙስና ወንጀሎችን በማጣራትና በመመርመር በአብዛኛዎች ላይ በፍ/ቤት ክሰ መስርቶ 520 ገደማ በሚሆኑ ተከሣሾች ላይ የሙስና ወንጀል በመፈፀም ጥፋት ከ3-21 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ማድረጉንም ከሰነዶች መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኰሚሽኑ ባካሄደው የሙስና ወንጀልን የማጣራትና ክስ መስርቶ የማስወሰን ሥራ በከፍተኛ የገንዘብ መጠን የሚገመት ንብረት ለመንግሥት መመለሱንና ከዚህም ውስጥ ከ1639116.24 ካሬ ሜትር በላይ ስፋት ያለው የከተማ መሬት እንደሚገኝበት የኮሚሽኑ ሪፖርቶች ይጠቁማሉ፡፡

ከላይ የተመለከትነው የተሻሻለው የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ የኮሚሽኑን ዓላማዎችና ሥልጣንና ተግባሮች በግልጽና በዝርዝር በማስቀመጥ የሙስናን መከላከያና መቆጣጠሪያ እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ መልካም ስነምግባር እንዲዳብር ማድረጊያ ስልቶችንና ዘዴዎችን የደነገገ ቢሆንም ለአንዳንድ ጽንሰ ሃሳቦች የሰጠው ትርጉም የተሟላ ሆኖ አይታይም፡፡ ሕጉን በማስፈፀም በኩል ከፍተኛ ጠቀሜታ ላላቸው ጽንሰ ሃሳቦች ግልጽ ትርጉም አለመስጠት ደግሞ አንድም ጥፋት ፈጽመዋል የተባሉ ሰዎችን የሕግ አስፈፃሚው ክፍል በሚሰጠው ሰፊ ትርጉም ምክንያት ያለአግባብ በጥፋተኝነት ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ በሌላም በኩል ሙስናን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጠውን አካልም ሆነ በሚቀርቡላቸው ክሶች ላይ ውሳኔ ለመስጠት ሥልጣን የተሰጣቸውን ፍ/ቤቶች ተፈፀመ የተባለው ድርጊት ትርጉም በተሰጠው ጽንሰ ሃሳብ ውስጥ የሚካተት መሆኑን ለመገንዘብ ችግር በመፍጠር ትክክለኛ ፍትህ እንዳይሰጥ ያደርጋል፡፡

እነዚህ በሕጉ ግልጽ ትርጉም ካልተሰጣቸው ጽንሰ ሃሳቦች መካከልም "ከባድ የሥነምግባር መጣስ" እና "ከባድ የሙስና ወንጀል" ተብለው በአዋጁ አንቀጽ 2(8) እና 2(9) የተደነገጉት ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ምክንያቱም "ከባድ የሥነምግባር መጣስ" ማለት ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል የሥነምግባር ጥፋት ነው በሚል የተሰጠው ትርጉም የጽንሰ ሃሳቡን ምንነት በግልጽ ከማስቀመጥ ይልቅ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል የሥነምግባር ጥፋት ምን ዓይነት ጥፋት ነው የሚል ተከታይ ጥያቄ አንስቶ መልስ ማግኘትን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው፡፡ "ከባድ የሙስና ወንጀል ማለትም

ሀ. ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈፀሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም

ለ. የመንግሥት ባለሥልጣንን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች፣ ወይም

ሐ. በአገር ሉአላዊነት፣ ኢኮኖሚ፣ ጸጥታ እንዲሁም በህብረተሰቡ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ የሚችሉ የሙስና ወንጀሎች፣ ናቸው የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

ከእነዚህ ሶስት አማራጭ ትርጓሜዎች ግልጽ የሆነው በፊደል ለ የተሰጠው ትርጉም ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ የሙስና ወንጀል በመንግሥት ባለሥልጣን ከተፈፀመ ደረጃውም ሆነ ዓይነቱ ምንም ይሁን ምን ከባድ የሙስና ወንጀል ተብሎ የሚፈረጅ መሆኑን ስለሚያስገነዝበ ነው፡፡ በዚህ ትርጉም ውስጥ የግልጽነት ችግር ሊያስነሳ ይችል የነበረው ለመሆኑ የመንግሥት ባለሥልጣን የሚባለው ከየትኛው ኃላፊነት ጀምሮ ያለው ነው የሚለው ቢሆንም የመንግሥት ባለሥለጣን ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 2 (5) ግልጽና ዝርዝር ትርጉም የተሰጠው በመሆኑ ትርጉሙን መሠረት አድርጐ ሕጉን ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያጋጥም ችግር አይኖርም፡፡

በፊደል "ሀ" የተሰጠውን ትርጉም ስንመለከት ግን ለመሆኑ ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ አላቸው ተብለው የሚፈረጁት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች የትኞቹ ናቸው? ከፍተኛ የገንዘብ መጠን የሚባለውስ ከስንት ብር ጀምሮ ነው? የሚሉ ተከታይ ጥያቄዎችን የሚያስነሳ በመሆኑ ከባድ የሙስና ወንጀል ምን እንደሆነ በግልጽ ለመረዳት አያስችልም፡፡

በፊደል "ሐ" የተሰጠውን ትርጉም ስንመለከትም አንድ የሙስና ወንጀል በኢኮኖሚ ወይም በጸጥታ ወይም በሕብረተሰብ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል የሚባለው በምን መለኪያ ነው? ከፍተኛ ጉዳት ማለትስ መጠኑ ምን ያህል ነው? የሚሉ ተከታይ ጥያቄዎችን አንስቶ መልስ ማግኘትን የሚፈልግ በመሆኑ ከባድ

የሙስና ወንጀል ከዚህ ትርጉም አንፃር ምን እንደሆነ በግልጽ ለመረዳት አያስችልም፡፡

በሕጉ ውስጥ የእነዚህ አስፈላጊ ጽንሰ ሃሳቦች የትርጉም ግልጽነት አለመኖር የሕጉን አተገባበር አስቸጋሪ ሊያደርግ የሚችል ከመሆኑም በላይ ሕግ አስፈፃሚ ሆኑ ግለሰቦች ለሕጉ እጅግ የተለጠጠ ሰፊ ትርጉም እንዲሰጡት በር በመክፈት የሕጉን አተገባበር ወጥነት የጐደለውና ኢፍትሐዊ እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡

### 4.2.2 የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ቁ.434/97

*ይህ ሕግ በ1993 ዓ.ም የወጣውን የፀረሙስና እና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/93 በመሻር የወጣ ሕግ ነው፡፡ ቀደም ብሎ የተመለከትነው የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ የተቋሙ ማቋቋሚያ፣ ሥልጣንና ተግባሩን መወሰኛና ሙስናን ለመከላከልና ለመቆጣጠር መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች የሚደነግግ ሕግ ሲሆን የፀረሙስና እና የማስረጃ ሕግ አዋጁ ግን አንድ የሙስና ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ የወንጀሉን መፈፀምና አፈፃፀሙን ለማጣራት፣ ለመመርመር፣ ክስ ለመመሥረት፣ ማስረጃ ለማሰማትና ውሳኔ ለማስጠት መከተል የሚያስፈልጉትን መንገዶችና ተፈፃሚ የሚደረጉትን ሥርዓቶች የሚደነግግ ሕግ ነው፡፡ በአጭሩ ይህ ሕግ የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባር ተፈፃሚ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ስልቶችንና መንግዶችን የሚደነግግና ሥርዓቶችን የሚዘረጋ ሕግ ነው፡፡*

*ይህ ሕግ አንድን የሙስና ወንጀል ፍ/ቤት አቅርቦ ውሳኔ ለማሰጠት ኮሚሽኑ ሊፈጽማቸው የሚገባ ተግባሮችንና መከተል ያለበትን መንገዶች ዘርዘር አድርጐ የሚደነግግ ቢሆንም ተቋሙ ሊከላከለውና ሊቆጣጠረው የተቋቋመበትና የመክሰሻና የማስወሰኛ ሥርዓቱ በዝርዝር የተደነገገለትን የሙስና ወንጀል ምንነት በተመለከተ በአንቀጽ 2(1) የሰጠው ትርጉም ግን የሙስና ወንጀል ማለት በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ የተመለከቱት የሙስና ወንጀሎች ናቸው የሚልና ሌላ ሕግን የሚጠቁም ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም የሙስና ወንጀል የሚባሉት ምን ዓይነት ወንጀሎች እንደሆኑ*

ለመገንዘብ የወንጀል ሕጉን አግባብነት ያላቸው አንቀጾች መመልከት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

### 4.2.3 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ

የኢ.ፌዲሪ የወንጀል ሕግ ኰሚሽኑ ከተቋቋመ ከአራት ዓመት ገደማ በኋላ የወጣ በመሆኑ የኰሚሽኑን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ በርካታ የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎችን አካትቶ ለመውጣቱ የኰሚሽኑም አስተዋጽኦ አለበት ብሎ ለመገመት ያስችላል፡፡ ሙስናን መከላከልና መቆጣጠርን በተመለከተ የወንጀል ሕጉ በመነሻነት በአንቀጽ 404 (4) በግልጽ የደነገገው የሙስና ወንጀል ምንድን ነው የሚለው ሲሆን ይህም በሕጉ በየትኞቹ አንቀጾች የሰፈሩት ጥፋቶች የሙስና ወንጀል እንደሆኑ ያስረዳል፡፡ በዚሁ ለሙስና ወንጀል ምንነት በተሰጠው ትርጉም ላይ በመመሥረት የሕጉን ድንጋጌዎች ስንመለከትም የሙስና ወንጀልን የሚመለከቱ ወደ 28 አንቀጾች መካተታቸውን እንገነዘባለን፡፡ ይህን ለመረዳትም ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሚሰጠውን አንቀጽ 404 (4) መመልከቱ በቂ ይሆናል፡፡ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሙስና ወንጀል የሚባሉት በሕጉ ርዕስ ሶስት ምዕራፍ ሁለት በክፍል አንድና በምዕራፍ ሶስት ክፍል አንድ ሥር የተደነገጉት ወንጀሎችና በሌሎች ክፍሎች በሚገኙ ሌሎች አምስት አንቀጾች ሥር የተደነገጉ ወንጀሎች ናቸው፡፡ እነዚህም ድንጋጌዎች ከአንቀጽ 407-420፣ ከአንቀጽ 427-431 ያሉትና አንቀጽ 397፣466፣676(1)፣684፣696(ሀ) ናቸው፡፡

የሙስና ወንጀል የሚባሉት የትኞቹ ወንጀሎች እንደሆኑ ተለይቶ መደንገጉና ለወንጀሉ ተፈፃሚ የሚሆኑት ድንጋጌዎች ተከታታይ ሆነው መቀመጣቸው ግለሰቦች የትኛው ድርጊታቸው በሕጉ የሙስና ወንጀል ተብሎ በመፈረጅ ሊያስጠይቃቸው እንደሚችል በቅድሚያ እንዲያውቁ በማድረግ ወንጀል ላለመፈፀም እንዲጠነቀቁ ይረዳቸዋል፡፡ ከዚህ በበለጠ ደግሞ የሙስና ወንጀል ተፈጽሟል በሚባል ጊዜ የትኛው ጥፋት በየትኛው ድንጋጌ ሥር እንደሚወድቅና በጥፋተኛው ላይ ምን ቅጣት ሊወሰንበት እንደሚገባ ለይቶ በማወቅ የተሟላ ክስ ለፍ/ቤት ለማቅረብ

ለኮሚሽኑ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ የሕጉ በዝርዝርና በግልጽ መቀመጥ ፍ/ቤቶች የሙስና ወንጀልን በተመለከተ ዳኝነት በሚያዩበት ጊዜ ተመሳሳይነትና ወጥነት ያለው ፍትሃዊ ውሳኔ ተቀባይነት ባለው የጊዜ ወሰን ውስጥ ለመስጠት ያስችላቸዋል፡፡

በአጠቃላይ የወንጀል ሕጉ የሙስና ወንጀልን በተመለከተ ኮሚሽኑ የተሰጠውን የሙስና ወንጀሎችን በተመለከተ በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ጥፋተኞችን የማስቀጣት ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን ያካተተ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለዚህ ዓላማም ሕጉ የሙስና ወንጀል ጉቦ መስጠትን፣ ጉቦ መቀበልን፣ በሥልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀትን ወይም ወደ ሃሰት መለወጥን፣ የሌላ ሰውን ዕቃ ወይም ንብረት መውሰድን፣ ያለአግባብ የሌላ ሰው ጉዳይ ማጓተትን፣ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘትን እንደሚያካትት ያስገነዝባል፡፡

በሕጉ በሙስና ወንጀልነት ለተፈረጁ ጥፋቶች የሚወሰነው ቅጣትም እሥራት ወይም የገንዘብ ቅጣት ወይም ሁለቱም በአንድ ላይ ሊሆን እንደሚችልም ከድንጋጌዎቹ መረዳት ይቻላል፡፡ የቅጣቶቹ መጠን እንደ ጥፋቶቹ ደረጃ የተለያየ ቢሆንም በእሥራቱም ሆነ በገንዘብ ቅጣቱ በፍ/ቤት ሊወሰን የሚችለው ከፍተኛ መጠን ግን በሕጉ ተደንግጐ እናገኛለን፡፡ በዚህም መሠረት በአንድ የሙስና ወንጀል የተከሰሰና ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠ ሰው ላይ ሊወሰን የሚችለው ከፍተኛው የእሥራት ቅጣት መጠን ጣሪያው እድሜ ልክ ድረስ መሆኑን ከሕጉ አንቀጽ 379 (2) እና አንቀጽ 108(1) መገንዘብ እንችላለን፡፡

የገንዘብ ቅጣትን በተመለከተ ሊወሰን የሚችለው የቅጣት መጠንም ጣሪያው ብር 500000 መሆኑን በሕጉ አንቀጽ 90 (1) (3) ተደንግጐ እናገኛለን፡፡ በእሥራትም ሆነ በገንዘብ መልክ በሕጉ የተደነገገው ከፍተኛ የቅጣት መጠን ከባድ መሆኑን መገንዘብ

የሚቻል ቢሆንም ወንጀል ፈፃሚዎችን በዘላቂነት በማስፈራራት ወንጀል ከመፈፀም ገቺ መሆን የሚችለው ግን በኮሚሽኑ ወንጀሎችን በማጣራት፣ በመመርመርና በአግባቡ የመክሰስ ብቃትና በፍ/ቤቶች ፍትህን በተቀላጠፈና በጥራት የመስራት ጥንካሬ ላይ በእጅጉ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ለመሆኑ ኮሚሽኑ ባለፋት ዘጠኝ አመታት 1500 ገደማ የሚሆኑ የሙስና ወንጀሎችን መርምሮ ክስ ማቅረቡ በቂ ነው ወይ? በፍ/ቤት በኩልስ ባለፋት ዘጠኝ አመታት ከቀረቡለት ክሶች 520 በሚሆኑት ላይ ውሳኔ መስጠቱ በቂ ነው ወይ የሚለው ቢሆንም ይህን ጥያቄ መመለስ ከዚህ ምርምር ወሰን ውጭ በመሆኑ ሁለተኛውን ጥያቄ ለመመለስ በአገሪቱ ውስጥ ሙስና በአሁኑ ጊዜ ያለበትን ደረጃ በጥናት ማወቅና ፍ/ቤቶች የቀረቡላቸውን ክሶች በምን ያህል ጊዜ ውሳኔ እንደሰጡባቸውና የውሳኔዎቹን ይዘት በዝርዝር መረዳት ስለሚጠይቅ እዚህ ላይ መልሱን መስጠት የሚቻል አይሆንም፡፡

### 4.2.4 የሃብት ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 468/2002

ይህ አዋጅ በፌዴራል መንግሥቱ፣ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በድሬዳዋ ከተማ ተሿሚዎች፣ ተመራጮችና ሠራተኞች የሆኑ ሰዎች ያላቸውን የግል ሀብት ለኮሚሽኑ እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ ግዴታ የሚጥል ሕግ ነው፡፡ አዋጁ ይህን ህግ ማውጣት በአገሪቱ ሙስናን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለማስረዳትም ሀብትን ኃላፊነት ለተሰጠው ተቋም ማሳወቅና ማስመዝገብ የመንግሥት አሠራርን በግልጽነትና በተጠያቂነት ላይ የተመሠረተ ለማድረግና ሙስና እና ብልሹ አሠራርን ለመከላከልና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው በማለት በመግቢያው ላይ ደንግጓል፡፡

የግል ሀብትን ማሳወቅና ማስመዝገብ በመጀመሪያ በከፍተኛው የመንግሥት አካል ሙስናን ለመዋጋት የፖለቲካ ፈቃደኝነት ለመኖሩ በአመላካችነት ያገለግላል፡፡ በሁለተኛ ደረጃም በእርግጥም ሀብት የማሳወቁና የማስመዝገቡ ሥራ የኮሚሽኑን ነፃነት በጠበቀ፣ ግልጽ በሆነ፣ ከፍተኛ የሙስና ወንጀሎችን ለመፈፀም እድሉ፣

ሥልጣኑና ቅርበቱ ባላቸው ሰዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ፣ ቀጣይነት ያለው ጠንካራ የመከታተያ ስልትና የመቆጣጠሪያ ዘዴ ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ ሙስና እንዳይፈፀም ማስጠንቀቂያ ሰጭ በመሆንም ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ከዚህም አልፎ ሙስና ተፈጽሟል የሚል ጥርጣሬ ሲኖር የድርጊቱን መፈፀም ለማረጋገጥ በሚደረገው የማጣራትና የመመርመር ሂደት ፍንጭ ሰጭ በመሆን የማይናቅ አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችል ከመሆኑም በላይ በተለይ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 419(1) የመንግሥት ሰራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ማንም ሰው፡-

ሀ. የኑሮ ደረጃው አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግሥት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤ ወይም

ለ. ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀደሞ በነበረበት የመንግሥት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ፤

የዚህ ዓይነቱ የኑሮ ደረጃ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ወይም ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ በእጁ እንዴት ሊገባ እንደቻለ ለፍርድ ቤት ማስረዳት ካልቻለ በጥፋተኝነት እሥራት ወይም መቀጫ ወይም ሁለቱም በአንድ ላይ ሊወሰንበት እንደሚችል የተደነገገውን ተፈፃሚ ለማድረግ የመንግስት ሠራተኛውን የመነሻ የገንዘብና የንብረት መጠን ማረጋገጫ በመሆን ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል፡፡

ስለዚህ የንብረት ምዝገባው ለወደፊቱ ሙስና እንዳይፈፀም ለመግታት እንዲያገለግል ብቻ ሳይሆን ንብረት በሚያስመዘግብበት ጊዜ የሚመዘገበው ንብረት መጠን ካስመዘጋቢው ያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን ከሆነም በሙስና የተገኘ ለመሆኑ ጠቋሚ በመሆን ማገልገል ይኖርበ□ል።

## 4.3 የሙስና ችግሮች እና የመከላከልና የመቆጣጠሩ አስፈላጊነት

ሙስና ከብዙ ዘመናት በፊት ጀምሮ በአጠቃላይ የዓለም ችግር ሆኖ የቆየ ቢሆንም በተለይ እንደ ኢተዮጵያ ባሉ ታዳጊ አገሮች ግን ከባድ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የፖለቲካና የሥነምግባር ጠንቆች መሠረት እየሆነ ይገኛል፡፡ አንድ ተመራማሪ እንዳለውም ሙስና በችግርነቱ፣ በይዘቱና ችግር በማስከተሉ ዓለማቀፋዊ ክስተት እየሆነ የመጣ ሲሆን ልዩ ልዩ ገጽታዎቹም ከአንዱ አገር እየተቀዱ ወደ ሌላው አገር የሚዛመት ድርጊት ነው፡፡[7]

አፍሪካን በተመለከተም የችግሮቹ ምንጭ ዘርፈ ብዙና የተወሳሰበ ቢሆንም ሙስና አንዱ ሥር የሰደደ የእድገት ፈተና መሆኑ ግን ብዙ ክርክር የሚነሳበት ጉዳይ አይደለም፡፡[8] ከደቡብ አፍሪካ ሁኔታ ጋር በማያያዝ የእኛ የራሳችን ሕዝቦችም እድሉን ካገኙ ከአፓርታይድ ሥርዓት ባልተናነሰ ሙሰኞች ይሆናሉና፡፡[9] በማለት ታዋቂው አፍሪካዊ ታጋይ ኔልሰን ማንዴላ የተናገሩት ይህንኑ ሙስና ለየአገሮቹ ያለውን አስቸጋሪነት የሚያጠናክር ነው፡፡ ቀደም ብሎም እንደጠቀስነው የሙስና ጉዳቶች የተለያዩ ገጽታዎች ያሉት ሲሆን በኢኮኖሚው በኩል አባካኝ የሆነ የሃብት አጠቃቀምን ያስከትላል፡፡ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ኢንቨስትመንትን ይገታል፡፡ ፍትሐዊ ውድድር የሰፈነበት የገበያ ሥርዓት እንዳይዳብርም ይገታል፡፡ ስለዚህም

> "ሙስና ነገሮችን ያጓትታል፡፡ በዓለም ባንክና በዓለም የገንዘብ ድርጅት በአምሳ ስምንት አገሮች በሚገኙ 2400 ኩባንያዎች ላይ በተደረገው ሰፊ ጥናት መሠረት ኩባንያዎች ለሰዎች የሚሰጡት ማባበያ በጨመረ ቁጥር ከቢሮክራቶች ጋር በሚደረገው ድርድር ምክንያት ጉዳዮች ተቆልፈው እየተያዙ የበለጠ ብዙ ጊዜ እንዲፈጁ ይደረጋል፡፡---- ስለዚህም ሙስናን መዋጋት የኢኮኖሚ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሥነምግባርም ጉዳይ ነው፡፡[10]

---

[7] Antonio Argandona, The UN, Convention Against Corruption and its Impact. On International Companies, 2006,

[8] Thomas R. Snider and Won Kid, Combating Corruption through Internal Law in Africa, Cornel Int'l Law J.2007,pp.691-747

[9] ዘኒ ከማሁ

[10] BT Costantinos, Collateral Damage Priming Counter Corruption Cultures that Elevate Good Governance 2007 P.2

ከዚህም በተጨማሪ የኢኮኖሚ እድገትን በመግታት የህበረተሰቡ የኑሮ ሆኔታ እንዲያሽቆለቁል ያደርጋል፡፡ የአገር ሃብትና ገቢም ድሆችን በእጅጉ በሚጐዳና ኢፍትሐዊ በሆነ ሁኔታ ለተወሰኑ ሰዎች እንዲከፋፈል ያደርጋል፡፡ ከማህበራዊውና ከፖለቲካው አንፃርም ሙስና የህግ የበላይነትንና ዴሞክራሲን በማዳከም መልካም አስተዳደርን አደጋ ላይ ይጥላል፡፡ መሠረታዊ የሰው ልጅ መብቶችንም ስጋት ላይ እንዲወድቁ ያደርጋል፡፡[11]

ከሥነምግባር አንፃርም ሙስና የህብረተሰብን መሠረታዊ ማህበራዊ እሴቶች በመሸርሸር የሕብረተሰቡን አጠቃላይ ሕይወት ለሙሰኞች የተመቻቸ ያደርገዋል፡፡ ጠንካራ ፀረ-ሙስና አመለካከትና ሥነምግባር ያለው ህብረተሰብ ባልተገነባበት ሁኔታ ደግሞ ሙስናን መዋጋትም ሆነ መከላከል ውጤት ሊያመጣ አይችልም፡፡

እንደዚህ ያሉ የአገር እድገት ጠንቆችን ማስወገድ የመንግሥትንና የሕብረተሰብን የተባበረ ጥረት የሚጠይቅ መሆኑ ደግም አከራካሪ አይደለም፡፡ የመንግሥት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ቀደም ብሎ በነበረው ሁኔታ ለግለሰቦች የሃብት ማከማቻና የልዩ መብት ማስገኛ የተመቻቸ መንገድ ፈጣሪዎች የነበሩ ቢሆንም የመንግሥት ሥልጣን በሕዝብ ድምጽ በምርጫ በሚያዝበትና የመንግሥት አስተዳደር ተግባራትም በሕዝብ ተሳትፍ ላይ እየተመሠረቱ በመጡበት አሁን ባለንበት ዘመን መንግሥታት ሕብረተሰቡን ሙስናን ከመሳሰሉ ጐጂ ድርጊቶች የመጠበቅ ኃላፊነት ከዋና ተግባሮቻቸው አንዱ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይህን ለማሳካትም ለአጠቃላይ የአገር እድገትና የህብረተሰብ ኑሮ መሻሻል ሁኔታዎችን አመቺ የሚያደርግ የሕግ መሠረት መጣልና ከሙስና የፀዳ ተቋማዊ አሠራር መመሥረት እጅግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የንግድ እንቅስቃሴዎችም ሆነ የመንግሥታት ተግባሮች ዓለም አቀፍ ይዘት እየያዙ በመምጣታቸው ሙስናም ዓለም አቀፍ እየሆነ መጥቷል፡፡ በዚህ የሙስና አለምአቀፋዊ፣ አህጉራዊና አገራዊ ጐጂነት ግንዛቤ እያገኘ መምጣትና የመንግሥታት ሙስናን የመከላከልና የመቆጣጠር ኃላፊነት እየጨመረ መምጣት

[11] Antonio Argandona, ከላይ በቁጥር 1 እንደተጠቀሰው

ምክንያትም የሕግ መሠረቶችን ከመጣል እስከ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የደረሰ ሙስናን በመከላከልና በመቆጣጠር ችግሮቹን ለማስወገድ የሚረዳ የተባበረ ዓለምአቀፍ ጥረት እየዳበረ መጥቷል፡፡

የዚህ ዓለምአቀፍ የፀረ-ሙስና ጥረት መገለጫ ከሆኑት መካከል አንዱ እ.ኤ.አ በ2003 የተፈረመውና ዲሴምበር 2005 ሥራ ላይ የዋለው የተባበሩት መንግሥታት የፀረሙስና ኰንቬንሽን ነው፡፡ በተለይ በአፍሪካ ደግሞ አብዛኛዎቹ አገሮች የሙስና ወረራ የተሠራጨባቸውና ለእድገታቸው ስር የሰደደ ፈተና የሆነባቸው ናቸው፡፡ ስለዚህም የፀረሙስና ትግሉ እጅግ አስፈላጊም ከባድም የሆነበት አህጉር ነው፡፡ ስለዚህም አገራት በየግላቸው የሚያደርጉት ትግል ዋናውን ሚና የሚጫወት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የጋራ ትግሉን ለማመቻቸትም የአፍሪካ ሕብረት እ.ኤ.አ በ2003 የፀረሙስና ኰንቬንሽን በአባል አገራት ተፈርሞ በ2006 በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

ይህ የሙስና አጠቃላይ ችግር እየሆነ መምጣትና የጠቀስናቸው የፀረሙስና ስምምነቶች ኢትዮጵያን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ሆነ በአፍሪካ ሕብረት አባልነቷና በፈራሚነቷ ትግሉን እንድትቀላቀል የሕግም ሆነ የሞራል ግዴታ የሚጥልባት መሆኑ አከራካሪ ባይሆንም ከዚህ የበለጠ ግን የራስዋ የውስጥ ጉዳይ ግንባር ቀደም ተዋናይ እንድትሆን ያስገድዳታል ምክንያቱም ኢትዮጵያ ሙስና በከፍተኛ ደረጃ ከሰፈነባቸው አገሮች አንዷ ተደርጋ የምትፈረጅ መሆኗን የሚጠቁሙ መረጃዎች ባይኖሩም የሙስና ችግር ያለባት አገር መሆኗን የሚጠቁሙ ግን በርካታ መረጃዎች ያሉ ሲሆን ከነዚህም አንዱ በ1993 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተካሄደው ጥናት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ያልዳበረባት፣ በኢኰኖሚዋ ኃላቀር የሆነች፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች ዝቅተኛ የሆኑባት፣ በመንግሥት አሠራር የሕዝብ ተሳትፎ ያላደገባት፣ የፍትሕ ሥርዓቱ በተቋምም ሆነ በሰው ኃይልና ጥራት ያልተሟላባትና የመልካም አስተዳደር ሥርዓት ያልሰፈነባት በእድገት ኋላቀር ከሆኑ

አገሮች አንዱ ናት፡፡ እነዚህ ውስብስብ ችግሮች በራሳቸው አሠራሮችን ለሙስና የተመቻቹ የሚያደርጉ ሲሆኑ ሙስናም በበኩሉ አገሪቱ ከእነዚህ ችግሮች እንዳትወጣና የህብረተሰቡ ሁለንተናዊ እድገት እንዳይረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ስለዚህም በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት፣ የዴሞክራሲና የማህበራዊ እድገት ግንባታ ጥረቶች ጅምር በመሆናቸውና በዓለምም ሆነ በአፍሪካ የሚታየው የሙስና እድገት በኢትዮጵያም ላይ የፈጠነ እንዲሆን ስለሚያደርገው የመከላከልና የመቆጣጠር ትግሉን እጅግ አስፈላጊ፣ መዘግየት የማይችል ነገር ግን ቀላል የማይሆን ያደርገዋል፡፡ የፀረሙስና ትግሉ ቀላል የማይሆንባቸው ምክንያቶች ደግሞ በርካታ ሲሆኑ አብዛኛዎቹም ከላይ የጠቀስናቸው ከእድገታችን ኋላቀር መሆንና ከድህነታችን ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ተቋማዊ አሠራራችን ግልጽ፣ አሳታፊና ተጠያቂነት የሰፈነበት፣ መልካም አስተዳደር የዳበረበት አለመሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ሕግ የማስፈፀም ተቋማዊም ሆነ ግለሰባዊ አቅማችን ዝቅተኛ መሆን ነው፡፡ ሶስተኛው ምክንያት ድህነትና የወደፊት ኑሮም ለአብዛኛው ህብረተሰብ አስተማማኝ አለመሆን ነው፡፡ አራተኛው ምክንያት ብዙውን ጊዜ በተቋሞቻችን ጉዳይ ለማስፈፀም በህጋዊው መንገድ ከመሄድ ይልቅ ህገወጡ መንገድ የፈጠነ ሕጋዊ መብትንም እንኳ ለማግኘት የተሻለ አስተማማኝ መሆን ነው፡፡ አምስተኛው ምክንያት የውጭ ገበያ ትሥሥራችን እየሰፋ መምጣትና የውጭ ኢንቨስትመንት በአገራችን እየጨመረ ሲመጣ ከእነዚህ ተግባሮች ጋር አብሮ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ የተወሳሰበ ሙስና ወደ አገር ውስጥ ተቋማትና የተቋሙ ሠራተኞች እየዘለቀ የሚገባበት ሁኔታ መፈጠሩ ነው፡፡

ይህ ሁኔታ ደግሞ የሙስና ጊዜ ሳይወሰድ አለመገታት ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ እድገት ፈታኝ ችግሮችን ሊያስከትል እንደሚችል የሚጠቁም ሲሆን ኮሚሽኑ የሚያደርገውን የፀረሙስና ትግል ለአገሪቱ አጠቃላይ እድገት ስኬት ከፍተኛ

አስተዋጽኦ እንደሚኖረውና የትግሉንም ውስብስብነት የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ የኮሚሽኑ የፀረሙስና ትግል ለሕግ ልዕልና መስፈንና ለሕጋዊ አሠራር መረጋገጥ የሚደረግ በመሆኑ ለትግሉ ሕግ የሚኖረው አስፈላጊነትና የሚያበረክተው አስተዋጽኦም የሚያከራክር አይደለም፡፡

ሙስናን የመከላከልና የመቆጣጠር ጥረቱን ስኬት አስተማማኝ ደረጃ ላይ ለማድረስ የሚቻለው በረጅም ሂደት ቢሆንም የሥነምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽኑ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ያደረጋቸው አጠቃላይ ጥረቶችና ስለሙስና ጎጂነት የሕብረተሰቡን የዕውቀት ደረጃ ከፍ ለማድረግ ያከናወናቸው የማስተማር ተግባሮች፣ በተለያዩ የመንግሥት ተቋማት አሠራሮች እንዲስተካከሉ ያደረጋቸው ጥረቶች፣ የሙስና ወንጀል በፈፀሙ ሰዎች ላይ በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ የተለያዩ ቅጣቶች ማስወሰኑ ሙስናን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ምን ውጤት እንዳስገኙ መገንዘብ የሚያስችል ጥናት ማድረግ ግን አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የዚህ ጥናት መሠረታዊ ዓላማም ኮሚሽኑ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ያከናወናቸው ተግባራት ሙስናን በመከላከልና በመቆጣጠርም ሆነ የሕብረተሰቡን ሥነምግባር በመገንባት ያስከተለውን ተጽዕኖ መገምገም ነው፡፡

## 4.4 □ሙስና ወንጀልንና ብልሹ አሠራርን የመከላከል ምንነት

መከላከል ማለት አንድ ሁኔታ ወይም ድርጊት ወይም ችግር ከመድረሱና መጠነ ሰፊ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ እንዳይከሰት ማድረግ ወይም ተከስቶ ከሆነ በመከሰቱ ምክንያት ይደርስ የነበረውን የጉዳት መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡[12]

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሙስናና ብልሹ አሠራር በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ በፖለቲካዊና አካባቢያዊ ሁኔታ ላይ ከሚያስከትለው ከፍተኛ ቀውስ አንጻር ከታላላቅ ዓለም አቀፍ ችግሮች መካከል አንዱ ሆኖ ይታያል፡፡ የሙስና ወንጀል አብዛኛውን

[12] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ አቅም ግንባታ ሚኒስቴር የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ጥራዝ 1 እና 2፣ ታህሳስ 1994

ህብረተሰብ በተለይም በማደግ ላይ ያሉ አገራት ህዝብን ለከፋ ድህነት ከመዳረግ አልፎ የሰውን ልጅ ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል ማህበራዊ ጠንቅ መሆኑን የተለያዩ የጥናትና ምርምር ግኝቶች አረጋግጠዋል፡፡

የሙስና ወንጀል እና ብልሹ አሠራር መከላከል እንደማንኛውም ወንጀል መከላከል ተግባር ሆኖ ነገር ግን ሙስና ካለው ልዩ ባህሪይና ከሚያስከትለው ከፍተኛ ጉዳት አንጻር በጥናት ላይ ተመስርቶ የሙስና ወንጀል ተከስቶ ወይም ተስፋፍቶ የሚያስከትለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ከባቢያዊና ፖለቲካዊ ኪሳራን ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የሚከናወን የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡

### 4.4.1 የአሠራር ሥርዓት ጥናት ምንነት

የአሠራር ሥርዓት መነሻው "System" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ሲሆን ሰፊና የተለያዩ ትርጉሞች ያሉት ቢሆንም ለተያዘው ርዕስ ከቢዝነስ ዲክሽነሪ የተወሰደው ትርጉም እንደሚከተለው ቀርቧል፤

> **System-** Set of detailed methods, procedures, and routines established or formulated to carry out a specific activity, perform a duty, or solve a problem.[13]

ከላይ ከተገለጸው ትርጉም አንጻር የአሠራር ሥርዓት፣ አንድን ተግባር ለማከናወን ያሉ ህጋዊ መሠረቶች ማለት አዋጆች፣ ደንቦች፣ የአፈጻጸም መመሪያዎች፣ የአሠራር ማንዋሎች፣ በሥራው የሚሣተፉ ሠራተኞች፣ የሥራ ክፍሎችና የቅንጅታቸው ድምር ውጤት የሚያሳይ ሥርዓት ነው ለማለት ያስችላል፡፡

የአሰራር ስርአት ጥናት ደግሞ ይህን ሥርዓት ለማወቅ፣ ለመመርመር ለማሻሻል ወይም ለመቀየር የሚካሄድ ጥናት ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

[13] Microsoft® Encarta® 2009. © 1993-2008 Microsoft Corporation.

ከዚህ በመነሳት በሙስናና ብልሹ አሰራር ላይ የሚካሄደዉ የአሰራር ስርአት ጥናት እንደማንኛውም የምርምርና የጥናት ዘዴዎችን የሚጠቀም ሆኖ ከሌሎች የጥናትና ምርምር ጥናቶች የሚለይበት በሙስና ወንጀልና በብልሹ አሠራር ላይ ብቻ የሚያተኩር መሆኑ ነው፡፡

ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚካሄድ የአሠራር ሥርዓት ጥናት በተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር የሚዳረጉ ክፍተቶችን ብቻ ለመለየትና እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚያግዙ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማፍለቅ የሚረዳ ጥናት ሲሆን ተቋሙ ካለበት ወይም ሊያጋጥመው ከሚችል የሙስና ወንጀልና ብልሹ አሠራር ሥጋት በመታደግ ውጤቱን የማሻሻል ጥናት ይሆናል፡፡

### 4.4.2 የሙስና ወንጀልና ብልሹ አሠራርን መከላከል የሚያስገኘው ጠቀሜታ

የሙስና ወንጀል እጅግ በጣም ከባድ የሆኑ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ማህበራዊና ከባቢያዊ ጉዳቶችና ቀውሶችን የሚያስከትል ስለመሆኑ በርካ□ □ጥናትና ምርምር ግኝቶች ያረጋገጡ ሲሆን የሙስና ወንጀል መከላከል ስራ በዋነኝነት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩ□ል፤

1. በሙስና ምክንያት ይባክን የነበረዉን የህዝብ ገንዘብና ሀብት በመ□□ፅ ያለዉን ሀገራዊ ሀብት ለታለመለት ሥራ ለማዋል ከማስቻሉም በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገትን ያፋጥናል፣
2. በሙስና ምክንያት ሊፈጠር የሚችል ማህበራዊ አለመረጋጋትን በማስቀረት የህዝብን ሰላማዊ ሕይወት አደጋ ላይ ከመውደቅ ይታደጋል፣
3. በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎችን በመከላከል የተፈጥሮ ሚዛን እንዳይዛባ ለመከላከል ያስችላል፣
4. የሙስና ወንጀል ከተከሰተ በኋላ የወንጀሉን ፈጻሚ እና የባከነውን የህዝብ ገንዘብና ሀብት ለማፈላለግ፣ ለማግኘትና ለማስመለስ የሚባክነውን ተጨማሪ የገንዘብና የሰው ኃይል ብክነትን ያስቀራል፣

5. መንግሥት የሙስና ፈጻሚ ወንጀለኞችን ለማስተዳደር የሚያወጣውን ወቸ ይቀንሳል፣
6. በቀላሉ ተምረዉና ተስተካክለዉ ለሃገር ጠቃሚ በሆነ ተግባር ላይ ሊሰማሩ የሚችሉ ዜጎችን በችግሩ □ስዓ ተ□አቀ□ እንዲባክኑ ከማድረግ ያድናል፣
7. በችግሩ ምክንያት በወንጀለኞች ቤተሰብ ላይ ሊደርስ የሚችለዉን ማህበራዊ ቀ□ስ እንዳይደርስ ይታደጋል፡፡

### 4.4.3 ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚካሄድ የአሠራር ሥርዓት ጥናት የሚያስገኘው ጠቀሜታ፤

- የአሠራር ሥርዓት ጥናት ሙስናና ብልሹ አሠራር ተከስተው ከፍተኛ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ለችግሩ ክፍተት የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን (አሠራሮችን) በመፈተሸ፣ በማጥናትና በመለየት ክፍተቶችን ለመዝጋት የሚያስችሉ የመፍትሔ ሀሳቦችን በማቅረብና ተግባራዊ እንዲደረጉ በማሰብ ችግሮች ከወዲሁ እንዲቀረፉ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ፣
- በጥናቱ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት የሚፈጠሩ ወይም ሊፈጠሩ የሚችሉ የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮች በቀላሉ እንዲጋለጡ ለማድረግ ማስቻሉ፣
- ሌሎች የሙስናና ብልሹ አሠራር መከላከያ ዘዴዎችን እንደ ሥነምግባር ትምህርት የመሳሰሉ የሚያተኩሩባቸው የሥራ አካባቢዎችን ለመለየትና ለመወሰን እገዛ ማድረጉ፣
- የአሠራር ሥርዓት ጥናት የተቋማት መደበኛ የሥራ እንቅስቃሴ ሳይስተጓጎል የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮች እንዳይከሰቱ ለማድረግ የሚካሄድ ጥናት መሆኑ፡፡

### 4.4.4 □ሙስና ወንጀልና ብልሹ አሠራርን የመከላከያ ስልቶች

የሙስና ወንጀል ካለው ውስብስብ ባህሪይና ከሚያስከትለው ከፍተኛ ጉዳት አንጻር የሙስና ወንጀልና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል አገራት በጋራና በተናጠል የመታገያ ስልቶችን በመቀየስ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

ሙስናን በመታገልና የመከላከያ ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ በማድረግ ከሚታወቁት ዓለም አቀፍ ተቋማትና ሕግጋት መካከል፤

1. **አለም አቀፉ ገጽታ**

- የተባበሩት መንግሥታት የፀረ-ሙስና የቃል ኪዳን ስምምነት (United Nations Convention against Corruption, 31 October. 2003)፣
- የአፍሪካ ሕብረት የሙስና መከላከልና መዋጋት የቃል ኪዳን ስምምነት (African Union Convention on Preventing and Combating Corruption, 11 July 2003)፣
- የአውሮፓ ህብረት ካውንስል ሙስናን የመታገል የቃል ኪዳን ስምምነት (Council of European Convention on Corruption, 1997-1999)
- የዓለም የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት የቃል ኪዳን ስምምነት (Organization for Economic Co-operation and Development Convention on Combating Bribery of Foreign Public Officials in International Business Transactions, 21 November 1997)
- የአሜርካን የጋራ የፀረ-ሙስና የቃል ኪዳን ስምምነት (The Inter-America Convention Against Corruption, 29 March 1996)

የመሳሰሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በዓለማችን ላይ ሙስናና ብልሹ አሠራርን እንደ አገራት ተጨባጭ ሁኔታ ዘርፈ ብዙ የመከላከያ ስልቶችን በመቀየስ ተግባራዊ ካደረጉ አገሮች፤ መካከል ጥቂቶቹን እንጠቅሳለን፡፡

2. **አፍሪካዊ ገጽታ**

- **ታንዛኒያ**[14]፦ አገሪቱ ከቅኝ ግዛት ነፃ ከወጣችበት እ.ኤ.አ 1965 ጀምሮ የፀረ-ሙስና ትግል እያካሄደች ሲሆን እ.ኤ.አ 1999 አጠቃላይ ሆነ የፀረ-ሙስና ስልትና የትግበራ መርሀ ግብር ተግባራዊ አድርጋለች፡፡ ይህንንም ብሔራዊ

[14] U4 Anti-corruption Resource Center. (May 2007). National Anti-corruption Strategy in Tanzania.

ስልት ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ለማጠናከርም እ.ኤ.አ ዲሴምበር 2006 የሦስትዮሽ ጥምረት ፕሮግራም (Triangular Partnership Program) ተግባራዊ በማድረግ እየሠራች ትገኛለች፡፡

**ኡጋንዳ**[15]፦ እ.ኤ.አ 1970 ጀምሮ ሙስናን ለመታገል ጥረት ከሚያደርጉ የአፍሪካ አገሮች መካከል አንዷ ስትሆን ከመታገያ ስልቶቿ መካከል፤

- የሙስናን አደገኛነት ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በማስጨበጥ ህብረተሰቡ በመንግሥት ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ያለምንም ጉቦ ክፍያ ማግኘት የሚገባቸውን አገልግሎቶች ምንም ዓይነት ጉቦ ወይም መማለጃ ሳይከፍሉ ማግኘት መብታቸው መሆኑን ማሳወቅና የመንግሥት ተሿሚዎች ግዴታቸውን እንዲወጡ የማስገንዘብ ሥራ መሥራት፣
- ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል በመንግሥት አሠራር ያሉትን ክፍተቶች በመፈተሽ እንዲሻሻሉ ማድረግ፣
- የሙስና ወንጀል ጥቆማን መቀበል፣ መመርመርና መክሰስ እና
- ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ሀብታቸውን እንዲያሳውቁ ማድረግ፣ ወ□ተ ናቸው::

**ቦትስዋና**[16]፦ እ.ኤ.አ 1994 የሙስናና የኢኮኖሚ ወንጀል ድንጋጌን በማውጣትና ይህን ድንጋጌ የሚያስፈጽም ዳይሬክቶሬት በማቋቋም ሦስት ዋና ዋና ተግባራትን □ከናውናለች ማለትም፤

1. ኦፐሬሽን በሥሩ፤
   - የሙስና ወንጀል መመርመር፣
   - መክሰስና
   - የኢንተለጀንስ ተግባራት
2. ህብረተሰቡን ማስተማር

---

[15] 1st annual report on Corruption trends in Uganda, November 2010

[16] Combating Corruption & Economic Crime in Africa, The international journal of Public Sector Management, 1999

3. በተለየ ሁኔታ በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ዙሪያ የናረ ሙስና ተግባራትን ማከናወን፡፡

## 3. ከእስያ አህጉር ገጽታ

- **ሆንግ ኮንግ**[17]፡- የሙያ ነጻነቱ የተጠበቀ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እ.ኤ.አ 1974 ጀምሮ በማቋቋም አመርቂ የፀረ-ሙስና ትግል የምታካሂድ አገር መሆኗ የሚነገርላት አገር ስትሆን ከመታገያ ስልቶቿ መካከል ዋና ዋናዎቹ፤
  1. ሙስና ከፍተኛ ሥጋት ያለው ወንጀል በመሆኑ የሕግ አስገዳጅነት እንዲኖረው ማድረግ፣
  2. የመንግሥት ተቋማትን አሠራር በመፈተሸና ለሙስና የተጋለጡትን በመለየት ሙስና ሊከሰት የሚችልበትን አጋጣሚ መዝጋት እንዲሁም በግሉ የንግድ ዘርፍ ሙስና የመከላከል ተግባርን ማስፋፋትና
  3. ህብረተሰቡን ስለሙስና አስከፊነት በስፋት ማስተማርና በሙስና ላይ በሚደረግ ትግል የህብረተሰቡ ድጋፍ የሚገኝበት ሁኔታን ማመቻቸት፡፡

- **አውስትራሊያ**[18]፡- የሙያ ነጻነቱ የተጠበቀ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እ.ኤ.አ 1988 በማቋቋም ትግሉን ከግቡ ለማድረስ አገሪቱ ከምትከተላቸው ስልቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤

  1. የሙስና ወንጀል ሪፖርት የሚደረግበት ሥርዓት በመዘርጋት
  2. የሙስና ወንጀልን ለመከላከል የሚያስችል የሥራ ባህልና እሴት የሚዳብርበት እንዲሁም የአሠራር ሥርዓት ጥናት የሚካሄድበት ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ፣
  3. የሙስና ወንጀልን በመመርመርና በመክሰስ፣
  4. በማስተማርና በማሰልጠን

[17] HONG KONG Policy Initiative Against Corruption: By Bertand de Speville, Development Centre, of the Organization For Economic Co-operation and Development, France 1997

[18] Preventing Corruption-Independent Commission Against Corruption Website: (http//www.icac.nsw.gov.au/)

## 4. በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ

አገራችን ኢትዮጵያ የምታካሂደው የልማትና የዲሞክራሲ ግንባታ በሙስና እንዳይደናቀፍና የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማሳካት በግንቦት ወር 1993 ዓ.ም የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተቋቁሟል፡፡ ዝርዝር ሁኔ□ዉ ቀ□ም ሲል ተገልጾአል፡፡

ኮሚሽኑ ከላይ የተገለጹ ዓላማዎቹን ከግቡ ለማድረስ እየተከተለ ያለው ስልት፤

1. አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ስለሙስና ጎጂነት የህዝቡ ንቃተ ህሊና እንዲጎለብት በማስተማር መልካም ሥነምግባር በህዝብ አገልግሎትና በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲስፋፋ ማድረግ፣
2. ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል በመንግሥት መ/ቤቶችና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሠራር እንዲኖር የአሠራር ሥርዓት ጥናት ማካሄድ፣
3. የሙስና ወንጀል ለመከሰቱ ጥርጣሬ ሲኖር በጥልቀት መመርመር፣ መክሰስና በሙስና የተገኘ ሀብትን ማስመለስ፣
4. የሥነምግባር አውታሮች ማደራጀትና እንዲጠናከሩ ማድረግ
5. የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግሥት ተሿሚዎችና ሌሎች የሚመለከተቸው የመንግሥት ሠራተኞች ሀብታቸውን የሚያሳውቁበትና የሚያስመዘግቡበት ሥርዓት መዘርጋት፣
6. የዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ትግል አጋር መሆን ወዘተ ናቸው፡፡

ባለፉት ሁለት ምዕራፎች ተዛማጅ ጽሑፎች ሙስናን የመታገል ጥቅሞች፣ ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ያለችበት ሁኔታ ወዘተ በሰፊው የተዳሰሰ ሲሆን ቀጥሎ የጥናቱ ግኝቶች ጄቀርባሉ፡፡

# 5. የጥናቱ ግኝቶች

## 5.1 መዕቢጸ

ቀደም ሲል በጥናቱ ዘዴ ክፍል እንደተገለፀው በአጠቃላይ 2996 የተለያዩ የፌደራል የመንግስት መስሪያቤቶችና የልማት ድርጅቶች ሠራተኞች እና ኃላፊዎች በጥናቱ የተካፈሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 72.9 በመቶ ወንዶች ቀሪዎቹ ሴቶች ናቸው፡፡ ፆታውን ስብጥር በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ይመልከቱ::

ሠንጠረዥ 4 የጥናቱ ተሳታፊዎች ብዛት በፆታ

| ፆታ | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|
| ወንድ | 2093 | 72.9 |
| ሴት | 777 | 27.1 |
| ድምር | 2870 | 100.0 |
| የተዘለለ | 126 | |
| ጠቅላላ ድምር | 2996 | |

አብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች ከ 20 - 50 ባለው ዕድሜ ክልል የሚገኙ ሲሆኑ በሦስቱም ዕድሜ ክልሎች ማለትም ከ20-30፣ 31-40 እና 41-50 የተካተቱትና ቃለ መጠይቁን የሞሉት ሰዎች ከሞላ ጎደል ተቀራራቢ የሆነ ከመቶ ቁጥር ድርሻ ይዘዋል፡፡ በቅደም ተከተል 29.8፣ 26.4 እና 28.0 በመቶ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 5 ተሳታፊዎች ብዛት በዕድሜ

| ዕድሜ | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|
| ከ 20 ዓመት በታች | 28 | .9 |
| 20 -30 ዓመት | 880 | 29.8 |
| 31 – 40 ዓመት | 779 | 26.4 |
| 41 – 50 ዓመት | 827 | 28.0 |
| 50 ዓመት በላይ | 441 | 14.9 |
| ድምር | 2955 | 100.0 |
| የተዘለለ | 41 | |
| ጠቅላላ ድምር | 2996 | |

ስለጋብቻ ሁኔታ ሲነሣ 60 በመቶ የሚሆኑት ተጠያቂዎች ያገቡ ሲሆኑ 34 በመቶ የሚሆኑት ያላገቡ ናቸው፡፡ የተጠያቂዎችን የትምህርት ደረጃ በተመለከተ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን ዲፕሎማ ያላቸው 27 ከመቶ እና ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው 11.6 በመቶ መሆኑን በጥናቱ የተገኘው ውጤት ያመለክታል፡፡ አብዛኛዎቹ ዲፕሎማ ያላቸው በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶችና በፌደራል መ/ቤቶች የሚሠሩ ናቸው፡፡ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የፌደራል መ/ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች የተሻለ የሠው ኃብት ልማት ሊኖራቸው እንደሚችል በጥናቱ የተገኘው ውጤት ይጠቁማል፡፡

ሠንጠረዥ 6 □ተሳታፊዎች ብዛት በጋብቻ ሁኔታ

| የጋብቻ ሁኔታ | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|
| ያገባ (ች) | 1809 | 61.2 |
| ያላገባ (ች) | 1004 | 34.0 |
| የፈታ (ች) | 70 | 2.4 |
| የሞተበት (ባት) | 71 | 2.4 |
| ድምር | 2954 | 100.0 |
| የተዘለለ | 42 | |
| ጠቅላላ ድምር | 2996 | |

ቃለመጠይቁን ከሞሉት ውስጥ 51 በመቶ የሚሆኑት በኃላፊነት ከ1-3 ዓመት የሠሩ ሲሆን 49 በመቶ የሚሆኑት ሠራተኛ በመሆን የሠሩ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የሥራ ልምዳቸውን በተመለከተ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው 23.6 በመቶ ከ6ዓመት በታች ሲሆን 36.3 በመቶ ከሃያ ዓመት በላይ ናቸው፡፡ የተቀሩት ከ 6 - 20 ዓመት በተለያዩ መ/ቤቶች የሥራ ልምድ ያላቸው ናቸው፡፡

## 5.2 መረጃ ለመሰብሰብ ሥራ ላይ የዋሉ መሣሪያዎችና የተገኙ ምላሾች

የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በሥራ ላይ ከዋሉ በኋላ ከየዘርፉ የተገኙ ምላሾች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ 7 መረጃ ለመሰብሰብ ሥራ ላይ የዋሉ መሣሪያዎች

| ተ.ቁ. | መረጽ መሰብሰቢጸዉ ዓይነት | የተሰራጨ/የታቀደ | የተመለሰ/ የተከናወነ | ምላሽ/ክንውን በመቶኛ (%) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መጠይቅ | 3100 | 2996 | 96 |
| 2 | ቡድን ተኮር ውይይት | 1* | 1 | 100 |
| 3 | ቃለ መጠይቅ | 42 | 35 | 83.33 |
| 4 | ሰነድ** | | | |

* የነዋሪዎች ፎረም ቡድን ተኮር ውይይት አባላት ብዛት 10 ነው፡፡
** በቁጥር ለመግለጽ አስቸጋሪ በመሆኑ በሠንጠረዡ ላይ ለማመላከት አልተቻለም፡፡

መረጃዎቹ ከተሰበሰቡና እንደየዓይነቶቹ ከተመረመሩ በኋላ በባለሙያዎቹ ስታትስቲካዊ ትንተና ተደርጐ በጥናቱ ዓላማ ላጁ ተመርኩዘው ለተዘረዘሩ ጥያቄዎች ሰፊ መልስ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## 5.3 የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርትና ሥልጠናን በተመለከተ

የፌደራል ሥነምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን ላለፉት 9 ዓመታት ካከናወናቸው ተግባራት አንዱና ዋነኛው ሥነምግባርና ፀረ - ሙስና ተኮር ትምህርት ለሥራ ኃላፊዎች፣ በተለያዩ ደረጃ ለሚሠሩ የፌደራል መ/ቤቶች ሠራተኞችና ለልማት ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎች መስጠት ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት ሰዎች የተለያዩ ጥያቄዎችን ተጠይቀው የመለሱ ሲሆን ውጤቱም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 8 የአጭር ጊዜ ስልጠና ስለመስጠቱ መላሾች ያላቸው እውቀት ከፆታ አንፃር

| ፆ□ | አዎ | አልተሰጠም | መወሰን አልችልም | ትምር | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|---|---|
| ወንድ | 868 (42.6%) | 901 (44.3%) | 267 (13.1%) | 2036 (100%) | 17.46* |
| ሴት | 263 (34.6%) | 401 (52.7%) | 97 (12.7%) | 761 (100%) | |
| ትምር | 1131 (40.4%) | 1302 (46.5%) | 364 (13%) | 2797 (100%) | |

* P< .01

ይኽ ሠንጠረዥ እንደሚያሳየው ከግማሽ በላይ ሴቶች ሥልጠና መሰጠት አለመሰጠቱን አያውቁም:: ከወንዶች አንፃር የጎላ ልዩነት እንዳለም ካይ ስኴር ($\chi^2$= 17.46, P< .01) አሳይቷል:: ይህም የሚያመላክተው ሴቶች ኮሚሽኑ በሚሰጠው ስልጠና ተሳትፎ ዌቅተኛ መሆኑንና ኮሚሽኑ በዚህ በኩል ሰፋ ያለ ሴቶችን ያሳተፈ የሰልጠና ሰራ መስራት እንዳለበት ነው::

ኮሚሽኑ በአካል በመገኘት ወይም የሚመለከታቸውን መ/ቤቶች/ድርጅቶች በመጋበዝ የሥነምግባርና ፀረ - ሙስና ትምህርት ሠጥቷል ወይ ለሚለው ጥያቄ 40 በመቶ የሚሆኑት ብቻ አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ወደ 13 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ገልፀዋል፡፡ ይህ ማለት ሥነምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን ባለፉት 9 ዓመታት የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርት ለመስጠት ባደረገው እንቅስቃሴ ጥያቄውን ከመለሱት 40 በመቶ የሚሆኑት ስልጠና አግኝተዋል ወይም ለመ/ቤታቸው ሠራተኞች ስልጠና መሰጠቱን ያውቃሉ ማለት ነው፡፡ ይህ በ9 ዓመት ውስጥ የተከናወነ ሲሆን በዓመት እስከ 5 በመቶ የሚሆኑትና ጥናቱ በተካሄደባቸው መ/ቤቶች የሚሠሩ ሠራተኞች በሥነምግባርና ፀረ - ሙስና ትምህርት ተካተዋል ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ጥረት ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም::

ይህን ውጤት ጥናቱ በተካሄደባቸው መ/ቤቶች ዘርዘር አትርገን ስናየው የትምህርት አሰጣጡ ሁኔታ ከመስሪያ ቤት መስሪያ ቤት እንደሚለጸይ እንረዳለን፡፡ በዚህም መሠረት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ፀረ-ሙስና ትምህርት በማዳረስ ግምባር ቀደም ሲሆኑ ት/ቤቶች በዝቅተኛ ደረጃ ይገኛሉ፡፡ ይህም የሥነምግባርና የፀረ - ሙስና ትምህርት ትኩረት ንብረትና ሃብት በሚገኝበት አካባቢና ምዝበራ ሊኖር ይችላል ተብሎ በሚገመትበት አካባቢ መሆኑን ነው የምንረዳው፡፡ ይሁን እንጂ በት/ቤቶች አካባቢ የሥነምግባር ትምህርት ቢሰጥ ት/ቤቶች ከብዙ የህብረተሰብ ክፍል ጋር ግንኙነታቸው የሠፋ ስለሆነ ሙስናን የሚጠየፍ ትውልድ ከመገንባት አንፃር ሚናቸው የጎላ ይሆናል፡፡ በተለይ ወደ ት/ቤት እየታተሙ የሚላኩ ፅሑፎች፣ ፖስተሮች ሊበረታቱ ይገባል፣ በሰልፍ ላይ በስነምግባር መኮንኖችና በስነ-ዜጋ ክበብ አስተማሪዎች ትምህርት ይሰጣል ያሉት ደግሞ የግንቦት 20 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተሳታፊ ናቸው፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች በኮሚሽኑ ትምህርት አሰጣጥ ዙሪያ አሉ ያሏቸውን ችግሮች ብዛት ያላቸው ተሳታፊዎች ከጠቀሷቸው ወደ ጥቂት ተሳታፊዎች የጠቀሷቸው በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ኮሚሽኑ የሚሰጠው ትምህርት ተከታታይነት እና ዘላቂነት የለውም፡፡ ይጀምራል፣ ያቋርጣል፣ ቆይቶ እንደገና ይጀምራል፡፡ እንደ ምሳሌ በብዛት የተነሱት በሬዲዮና በቴሌቪዥን የሚቀርቡ ማስታወቂያዎች ናቸው፡፡ ይህንንም በተመለከተ አንድ ተሳታፊ ሲገልፁ:

  "አንድ ሰሞን በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በጋዜጦች ዋና መነጋገሪያ እና ሞቅ ሞቅ ካለ በኋላ ወዲያው ደብዛው ጁቷኛል ብለዋል፡፡"

- ሌሎች በርከት ያሉ የጥናቱ ተሳታፊዎችም በበኩላቸው የሚከተሉትን ሀሳቦች ቶል□ኸል፡፡
- የትምህርቱ አቀራረብ ደረቅ እና ሳቢ አለመሆኑ ሌላው በተደጋጋሚ የተነሳ ችግር ነው፡፡ ትምህርቱ ኬዞችን በማቅረብ፣ ተግባራዊ ልምዶችንና ችግሮችን በማያያዝ እና የመርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም አይሰጥም፡፡

"የተለመደና የተደጋገመ መንገድ በመከተል ከማሰልቸት ይልቅ ከወቅቱ የቴክኖሎጂና ውስብስብ የአሰራር መንገዶች አንፃርም የዘመነ መንገድ መከተልና መተግበር አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡"

"በአብዛኛው በትምህርት ቤቶችና በሃይማኖት ማራመጃ ቦታዎች ማለትም ብዙ ሰው ሊገኝ በሚችልበት ቦታ ትምህርቱ መሰጠት ይኖርበታል፡፡"

"ኮሚሽኑ በሬዲዮና በቴሌቪዥን በሚያስተላልፋቸው ትምህርቶች በተቻለ መጠን ለአዋቂዎች፣ ለሕፃናት፤ እንዲሁም □ተማሩና ጸልተማሩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ አለመሆኑ ይታያል፡፡"

- በሬዲዮና በቴሌቪዥን ብቻ ትምህርት መስጠት ወይም ትምህርቱን በአካል ወደ ሕብረተሰቡ ወርዶ አለመስጠት፡፡ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ከተሰጡት አስተያየቶች ውስጥ አንዱ እንዲህ ይላል፡፡

"እኔ በቴሌቪዥን ማስታወቂያ ነው ያየሁት፡፡ ያ ደግሞ ትምህርት ነው ብዬ ለመቀበል ይከብደኛል፡፡ ይልቁንም ኮሚሽኑ ወደ ሕዝቡ በአካል እየቀረበ ሕዝቡ ያያቸውን የሙስና አደጋዎችን እንዲጠቁም እያደረገ እና በሙስና የባከነውን የሀገሪቱን ሀብት ከነሙሰኞቹ ይፋ እያደረገ ቢያስተምር የተሻለ ይሆን ነበር፡፡"

"የኮሚሽኑ ትምህርት አሰጣጥ ተደራሽነት እና ቀጣይነት ይጎድለዋል ብዬ አስባለሁ፡፡ ሁሉንም መስሪያ ቤቶችና አካላትን ማዕቀፍ ያደረገና በጥናት ላይ የተደገፈ ትምህርት አልተቀረፀም፡፡"

- በቴሌቪዥን የሚተላለፉት ትምህርቶች አንዳንዶቹ ሙስናን እንዴት መፈፀምና ማምለጥ እንደሚቻል የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ ይህንን ጉዳይ

በተመለከተ አንድ ተሳታፊ እንዲህ ብለዋል፡፡ "የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች አስተማሪ ቢሆኑም አንዳንድ ጊዜ የሚታዩት ማስታዎቂያዎች ሙስናን ለማስፋፋት በር ይከፍታሉ፡፡ ለምሳሌ እንዴት ሙስና እንደሚሰራ የሚያሳዩ (የሚያስተምሩ) ማስታዎቂያዎች አሉ፡፡ ሌላ ተሳታፊም እንዲህ ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ በሚዲያ ከሚተላለፉት የሙስናና የስነ-ምግባር ትምህርቶች መካከል አብዛኞቹ ከማስፈራራት ያለፈ እምብዛም የአመለካከት ለውጥ አያመጡም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወንጀለኞች ወንጀሉን ከሠሩ በኃላ እንዴት እንደሚያዙ ስለሚያስተምራቸው በቀላሉ እንዴት እንደሚሰወሩም ትምህርት የሚሰጡ ናቸው፡፡"

ከዚህ ጋር በተገናኘ ከተሰጡ ተጨማሪ አስተያየቶች የሚከተሉት ይገኙበ□ል፡፡

"በማስታወቂያ መልክ የሚተላለፉት ትምህርቶች የእድሜ ገደብ ስለማይቀመጥላቸው ልጆች ሙስናን እንዲማሩ በር የሚከፍት መሆኑና በቴሌቪዥን መልዕክቶች በድራማ መልክ ሲተላለፉ የሙስና ዘዴዎችም አብረው እየተላለፉ ስለሆነ ሙስና የበለጠ እየረቀቀ እንዲሄድ ያደርገዋል፡፡"

"በቴሌቪዥን የሚሰጡ የፀረ-ሙስናና የስነ-ምግባር ትምህርቶች ለሕፃናት ስርቆትንና ውሸትን እንዲሁም ለአዋቂ ሰዎች ደግሞ ሙስናን እንዴት አድርገው መስራት እንደሚችሉ ዘዴ ማስተማሪያ መስለው ይታ□ኛል፡፡"

- ብቃት ያላቸውና በሙያው የሰለጠኑ እንዲሁም የማስተማር ክህሎት ያላቸው ሰዎች ስልጠናውን እንዲሰጡ አይደረግም፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ አንዳንድ ተሳታፊዎች አሠልጣኞች ሰልጣኞች ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች መልስ መስጠት አይችሉም፤ በቂ ዝግጅትም አድርገው አይመጡም ብለዋል፡፡

- የተሰጠው ትምህርት ምን ውጤት እንዳስገኘና በሰራተኛው ዘንድ እንደሰረፀ ክትትል አለማድረግን በተመለከተም አንድ ተሳታፊ ሲገልፁ የሚሰጠው

ስልጠና ውጤት ማስገኘቱን ክትትል የማድረግ የኮሚሽኑ አቅም አናሳ ነው ብለዋል፡፡

- በሚዲያ የሚተላለፉት ትምህርቶች በማይደርሱበት የገጠር አካባቢዎች ኮሚሽኑ ባለሙያ እየላከ አያስተምርም፡፡

"የትምህርት አሰጣጡ በተማረው ክፍልና በከተማ ብቻ ሳይወሰን በገጠሩና በዝቅተኛው የሕብረተሰብ ክፍልም መዳረስ አለበት፡፡ እስከአሁን ግን ይህ ጐልቶ አይታይም፡፡"

- በተጨማሪም የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች የሚከተለውን ብለዋል፡፡ ከችግሩ ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም አስከፊነት አኳያ የሚሰጠው ትምህርት በጣም ትንሽ ነው፡፡ ስልጠናው የሚሰጠው ለአጭር ጊዜና ከላይ ከላይ ነካ ነካ በማድረግ ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ አንድ ተሳታፊ በአጭሩ እንዲህ ገልፀውታል፡፡ "ለትምህርቱ የሚሰጠው ጊዜ አጭር በመሆኑ ተግባራዊ ጉዳዮችን በስፋት እና በጥልቀት ማንሳትና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን መጠቆም አልተቻለም፡፡" ሰውን ሊለውጥ በሚችል መልኩ በስፋትና በጥልቀት አልተዳረሰም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ያማከለ ትምህርት ኮሚሽኑ አይሰጥም የሚል አስተያየት ተሰንዝሯል፡፡ ይህም ማለት በሁሉም የትምህርት ደረጃና የዕድሜ ክልል ላሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች ትምህርቱን ኮሚሽኑ አላዳረሰም፡፡ "በኃላፊነት ደረጃ ላይ ያሉ ብቻ አይደሉም ይህንን የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ትምህርት መማር ወይም መሰልጠን ያለባቸው፡፡ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ሊማረውና ሊገነዘበው ይገባል ብለዋል፡፡" "ኃላፊዎችን ብቻ እየጠሩ በቢሮ ስልጠና ከመስጠት ወደ ሰፊው ሕዝብ ቀረብ በማለት ብዙሃኑን ሕብረተሰብ ማስተማር በተለይ ለሕብረተሰቡ ወገንተኝነትን የሚያሳዩ አርዓያ ሰዎችን ከጎናችሁ አድርጋችሁ ማስተማር፡፡ ለምሳሌ እንደ አበበች ጎበና እና የመሳሰሉ አርዓያዎችን መጠቀም ያለመቻል ችግር ተጠቁሟል፡፡"

ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው (ሠንጠረዥ 9) ስልጠናው ያተኮረው በተለያዩ ነጥቦች ዙሪያ ሆኖ በተለይም የሥነ ምግባር ፅንሰ ሃሳብ፣ የሥነ ምግባር መርሆዎች፣ በሙስና ፅንሰ ሃሳብና ሙስና ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን በመከላከል ዙሪያ ነው፡፡ እነዚህ የትኩረት አቅጣጫዎች ለየብቻቸው የተሰጣቸው ትኩረት እንዳለ ሆኖ እርስ በርሳቸውም እየተደባለቁ እንደሚሰጡ መረጃው ያሳያል፡፡ ስልጠናው ለሠራተኞችና ለመስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ለአጫጭር ቀናት የተሰጠ ሲሆን (ማለትም ከ1-6 ቀናት) በቂ እንዳልሆነ የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡

ሠንጠረዥ 9 የስልጠናው የትኩረት መስኮች በመቶኛ

| የሥልጠናው ዓይነት | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|
| በስነምግባር ፅንሠ ሐሳብ (1) | 140 | 11.8 |
| በስነምግባር መርሆ- ች (2) | 101 | 8.5 |
| በሙስና ፅንሠ ሐሳብ (3) | 77 | 6.5 |
| በሙስና ወንጀሎች መከላከያ (4) | 94 | 7.9 |
| ሌላ ካለ | 209 | 26.1 |
| 1 እና 2 | 75 | 6.3 |
| 1=2 እና 3 | 101 | 8.5 |
| 1=2=3 እና 4 | 288 | 24.3 |
| ድምር | 1085 | 100.0 |
| የተዘለለ | 1911 | |
| **ጠቅላላ ድምር** | 2996 | |

በተለይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኃላፊዎችና ሠራተኞች እንዲሁም የፌዴራል መ/ቤቶች ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሆኑት ለስልጠና የተሰጠው ጊዜ በቂ ነው ብለው እንደማያምኑ ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሠራተኞችና የበላይ ኃላፊዎች ለስልጠና የተሰጠው ጊዜ በቂ ነው በማለት የተሻለ ቁጥር አስመዝግበዋል፡፡ ይህም ቀደም ሲል እንዳየነው በመንግስት ልማት ድርጅቶች የተሻለ ፀረ-ሙስና ትምህርት ሽፋን ከመኖሩ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 10 የስልጠናው ጊዜ መጠን በተመለከተ

| **የተሠጠበት የጊዜ መጠን** | **በቁጥር** | **በመቶኛ** | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|
| በቂ ወጅም በጣም በቂ | 496 | 26% | 49.65* |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መወሰን ያስቸግራል | **737** | 39% | |
| በቂ ወይም በጣም በቂ ያልሆነ | **679** | 35% | |
| ድምር | **1912** | 100% | |

* P< .01

ከተጠኝዎች (መላሾች) መካከል 26% ብቻ የሆኑት በሥልጠና ጊዜ በቂነት ተስማምተዃል:: □ተቀሩት ግን በቂ አለመሆኑን (35%) ወይም መወሰን እንደሚቸገሩ (38%) ገልፀዋል:: ይኸ ልዩነት በ $X^2$ ተረፋፅ□ል:: መወሰን ያልቻሉትን አውጥተን ሁለቱን ስናወዳድርም በቂ አይደለም የሚሉት በጎላ ሁኔ□ ($\chi^2$ =28.50, P<.01) ጁበል□ሉ::

ጁህ ቁዓር ከሠንጠረዥ 8 አንፃር ከፍተኛ ነው:: ማለትም በዚያ ሠንጠረዥ /በመጠይቅ ቁጥር 12/ የሥነ- ምግባር ትምህርት በመ/ቤቱ ስለመስጠቱ ተጠይቀው አዎ ያሉት 40% ሆነው እዚህ ላይ ግን መላሾች ከዚያ ቁጥር በላይ ናቸው:: ይህ የሆነው በቁጥር ወይም በመረጃ አገባብ ስህተት ሳይሆን መላሾች ሲመልሱ ከተለያዩ ሰዎች ባገኙት መረጃ የሰጡት ምላሽ ሊሆን ስለሚችል ነው::

የተሰጠው ትምህርት በመሥሪያ ቤታቸው ውስጥ መልካም ሥነምግባርን ለማስረፅ ረድቷል ወይ ለሚለው ጥያቄ 44 በመቶ የሚሆኑት አ- ንታዊ መልስ የሰጡ ሲሆን 41 በመቶ የሚሆኑት ተጠያቂዎች ትምህርቱ ስለአመጣው ተጨባጭ ለውጥ በተመለከተ እርግጠኛ መሆን እንደማይችሉ ገልፀዋል፡፡ አሁንም በመንግስት ልማት ድርጅቶች ሥር የሚሠሩ ሠራተኞች እና ሃላፊዎች ሥልጠናው በሠራተኞች ሥነምግባር ላይ የተሻለ ለውጥ አምጥቷል በማለት ከፍተኛ ቁጥር ይዘዋል፡፡

ኮሚሽኑ በማስተማር መልካም ሥነምግባር በማስፈን ረገድ ውጤታማ መሆኑን "አምንበታለሁ" ያሉ የጥናቱ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ምክንያቶች አስቀምጠዋል፡፡

- ትምህርት ከተሰጠው ህብረተሰቡ የአመለካከት ለውጥ የማያመጣበት ምክንያት የለም /በርካታ መላሾች ጠቅሰውታል/፡፡
- በትክክልና በግልጽ ማስተማር ከተቻለ በህብረተሰቡ ውስጥ ሙስናን መቀነስ ስለሚቻል

- ማስተማር ሙስና ከመከሰቱ በፊት የቅድመ ጥንቃቄ መሠረት ስለሚሆን፣ ወ□ተ ብለዃል፡፡

ከዚህ በላይ የሰፈሩት ምክንያቶች መላሾቹ በትምህርት ላይ ያላቸውን ጠንካራ እምነት የሚገልፅ ነው፡፡ ሌሎች ተሳታፊዎች ደግሞ የኮሚሽኑን የትምህርት ሥራ ውጤታማነት ታይተዋል ብለው ከሚያስቧቸው ለውጦች ጋር ያዛምዱቸዋል፡፡ በዚህ አንፃር የተሰጡት ምላሾች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ኮሚሽኑ ከተቋቋመ በኋላ በህብረተሰቡ ዘንድ የአመለካከት ለውጥ በመታየቱ /በርካታ መላሾች የሰጡት/
- ህብረተሰቡ በሙስና ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ አግኝቷል
- ሙስናን በመከላከል ረገድ የተሻለ ውጤት እየታየ ነው
- በሚዲያ የሚተላለፈው ትምህርት የአዲሱን ትውልድ አስተሳሰብ እየቀረፀ በመሆኑ
- በአንዳንድ መ/ቤቶች እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች አስተማሪ በመሆናቸው ወ□ተ ናቸው፡፡

ከዚህ በተቃራኒ የኮሚሽኑን ውጤታማነት "ፈፅሞ አላምንም" ወይም "አላምንም" በማለት ምላሽ የሰጡ ሰዎች ያስቀመጧቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ስለመልካም ስነምግባር ከወሬ የዘለለ ተግባራዊ ለውጥ አልታየም፣ ኮሚሽኑ እራሱ ከሙስና የፀዳ አይደለም
- ማስተማር ብቻ ውጤት አያመጣም
- የሚሰጠው ትምህርት ተከታታይነትና ወጥነት ስለሚጎድለው
- ስለ ስነምግባር የሚሰብኩ በርካታ ሰዎች ዋነኛ የሙስና ወንጀል ተዋናዮች ስለሆኑ

በሌላ በኩል ለጥያቄው መወሰን አልችልም በማለት ምላሽ የሰጡት የጥናቱ ተሳታፊዎች የኮሚሽኑን ውጤታማነት ለመወሰን የሚያስችል መረጃ እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡

ተሳታፊዎች ያስቀመጧቸው እየተስተዋሉ ያሉ የሰነ-ምግባርና □ሙስና ችግሮች እንደሚከተለው በደረጃ ተቀምጠዋል፡፡

- የጊዜ አጠቃቀም ችግርን ብዛት ያላቸው ተሳታፊዎች እንደ ዋና የሙስና ችግር አስቀምጠዋል፡፡ ይህም ማለት አርፍዶ ስራ መግባት፣ የሥራ ሰዓት ሳይጠናቀቅ ቀድሞ መውጣት፣ ያለምክንያት ከስራ ገበታ መቅረትና ጊዜን በአግባቡ ለሥራ አለማዋል፡፡
- በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሰው ችግር የሥነ-ምግባር መርሆች አለመጠበቅ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ሐቀኝነት፣ ግልፅነት፣ ተጠያቂነት፣ ቅንነት፣ የስራ ተነሳሽነት አለመኖርና አድሏዊነት ማለትም በዘር፣ በጎሳ እና በዘመድ አዝማድ መስራት ወዘተ፡፡
- የመንግስትን ንብረት አለዓግባብ ማባከን እና እንደ ራስ ንብረት አለማየት
- ከግዥ ጋር የተያያዙ ጉድለቶች (የግዢ ስርዓቱ ግልፅነት የጎደለው መሆን፣ ጊዜው ያለፈበት ዕቃ መግዛት)
- ስርቆት
- ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም
- የመልካም አስተዳደር ጉድለቶች
- ሰነድ ማጭበርበርና ለማጥፋት መሞከር
- ግልፅነት የጎደለው አሠራር መኖር
- የሚተላለፉ የመንግስት መመሪያዎችንና ደንቦችን ተግባራዊ አለማድረግ
- አያገባኝም (ምንቸገረኝ) ባይነት

- ኪራይ ሰብሳቢነት (ያለአግባብ ጥቅም መፈለግ)
- የተዝረከረከ የሐብት አስተዳደር
- የተንዛዛ የአሠራር ስርዓት መኖር ወዘተ ናቸው

ሠንጠረዥ 11 የስነምግባርና ፀረ ሙስና ትምህርት መስጠት ሙስናን ስለመግታት

| መልስ | በቁጥር | በመቶኛ | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|
| በ□ም አምናለሁ | 1261 | 44.0% | 2476.90* |
| አምናለሁ | 1185 | 41.4% | |
| መወሰን አልችልም | 196 | 6.8% | |
| አላምንም | 152 | 5.3% | |
| በፍፁም አላምንና | 71 | 2.5% | |
| ድምር | 2865 | 100% | |

* P< .01

በሰንጠረዡ ላይ የቀረበው አኃዛዊ መረጃ እንደሚያሳየው የተለያዩ አማራጮችን የመለሱት ሰዎች ብዛት የጎላ ልዩነት እንደሌለው በግልጽ የሚታይ ሲሆን ይህ በስታትስቲክስ ($\chi^2$=2476.90, df=4, P<.01) □ሁ□ቱ□ ነው፡፡ ዋናውና አበራታች ግኝት ግን ከአጠቃላይ መላሾች 85 በመቶው ስልጠናው ሙስናን ለማስቆም እንደረዳ እምነታቸውን የገለጹበትና ወደ ስምንት በመቶ የሚጠጉ መላሾች ብቻ እምነት እንደሌላቸው መግለጻቸው ነው፡፡ ከዚህ በመነሣትም ስልጠናው በብዙዎች ዘንድ ተአማኒነት ያለው የሙስና ማቆሚያ ወይም መቀነሻ ዘዴ እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡

አሁንም በመንግስት ልማት ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ስልጠናው በስነምግባር ላይ የተሻለ ለውጥ አምጥቷል በማለት ከፍተኛውን ቁጥር ይዘዋል (ሠንጠረዥ 12) ምንም እንኳ አጠቃላይ የሥነምግባርና ፀረ - ሙስና ትምህርት በተለያዩ ማሰራጫ ዘዴዎች የሚተላለፉ ቢሆንም 44 በመቶ የሚሆኑት ሬዲዮና ቴሌቪዥን በዋነኛነት የሚጠቀሱ ይሆናል ብለዋል (ሠንጠረዥ 13ን ይመልከቱ)፡፡

ሠንጠረዥ 12 ሥልጠናው የሥነ ምግባር ለውጥ ስለማምጣቱ

| አስተያየት | በቁጥር | በመቶኛ | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|
| □ስማማለሁ/ በ□ም □ስማማለሁ | 958 | 44.2 | |
| መወሰን አልችልም | 881 | 40.7 | 327.01* |
| አልስማማም/በጣም አልስማማም | 328 | 15.1 | |
| ድምር | 2167 | 100 | |

* P< .01

ከዚህ ጥያቄ አንፃር አነስተኛ ቁጥር ያላቸው (15%) ስልጠናው በሥነምግባር ረገድ ለውጥ አላመጣም ሲሉ የነዚህ ሶስት እጥፍ የሚሆን (44%) ግን ለውጥ አምጥቷል ብለዋል። መወሰን አልችልም ያሉት በዛ (40.7%) ያሉ ናቸው። የተስማሙትንና ያልተስማሙትን መላሾች ብቻ ስናይ ውጤቱ አበረታች ነው።

ሠንጠረዥ 13 **የፀረ ሙስና ትምህርት ያገኙበት ዘዴ በቁጥርና በመቶኛ**

| የፀረ ሙስናን ትምህርት ያገኙበት ዘዴ | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|
| በሬድዮና በቴሌቭዥን (1) | 1231 | 45.4 |
| በጋዜጦች፣ መፅሔቶችና በራሪ ወረቀቶች (2) | 226 | 8.3 |
| የኮሚሽኑ ባለሞያዎች በአካል ተገኝተው በሰጡት ስልጠና (3) | 134 | 4.9 |
| ትምህርቱን አላገኘሁም (4) | 110 | 4.1 |
| 1 እና 2 | 682 | 25.1 |
| 1 እና 3 | 68 | 2.5 |
| 2 እና 3 | 42 | 1.5 |
| 1፣2 እና 3 | 221 | 8.1 |
| ድምር | 2714 | 100.00 |
| የተዘለለ | 282 | |
| ጠቅላላ ድምር | 2996 | |

* P< .01

ይህም የሚያመለክተው እነዚህ ሁለቱ የሥነምግባርና ፀረ - ሙስና ትምህርት ማስተላለፊያ ዘዴዎች ህብረተሰቡን ስለ ሥነምግባርና ፀረ - ሙስና ትምህርት ለመስተማር ለሚደረገው እንቅስቃሴ ሚናቸው የጎላ መሆኑን ነው፡፡ በተለይም በትምህርት ቤቶች አካባቢ ሚናቸው የጎላ ሊሆን እንደሚችል ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ምን አልባትም ኮሚሽኑ ወደፊት በዚህ ትምህርት ማስተላለፊያ

ዘዴዎች ላይ ቢያተኩር ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል የዚህ ጥናት ውጤት ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ □ሥነምግባርና □ፀረ - ሙስና ትምህርት ለእነሱም ሆነ በመ/ቤታቸው ውስጥ ለሚገኙ ሠራተኞች አለመሰጠቱን የገለፁት ተጠያቂዎች ትምህርቱ ለምን እንዳልተሰጠ ሲጠየቁ አብዛኛዎቹ በኮሚሽኑ በኩል ጥሪ እንዳልተላለፈና አልፎ አልፎም ለጥቂት የበላይ ኃላፊዎች ብቻ ትምህርቱ እንደተሰጠ አመልክተዋል፡፡

በቡድን ውይይት ለተሳተፉ ትምህርቱ ለወደፊት እንዴትና በምን ርዕስ ላይ ቢሰጥ ይሻላል ለሚለው ጥያቄ የተሰጡ ምላሾች ቀዓሎ ተ□ርዌረኸል፡፡

- ከታች ከሕፃናት ጀምሮ በስነ-ምግባር ማነፅ፡፡ ለተማሪዎች ከስር ጀምሮ የሐገር ወዳድነት ስሜት እንዲኖራቸው ትምህርት ቢሰጥ፡፡ ሰዎች እንደ ሰው እንዲያስቡ ከ(humanity) ጋር የተያያዙ ስልጠናዎች ቢሰጡ፡፡
- ስነ-ምግባር ላይ ቢተኮር ሙስናንም መቀነስ ይቻላል፡፡
- ሁሉንም ዜጐች ማዳረስ፡፡ በተለይ በፋይናንስ አስተዳደርና በዕቃ ግዥ፣ በሰው ኃይል አስተዳደርና በመሳሰሉት ጉዳዮች ለሰራተኞች ስልጠና መሰጠት ይኖርበታል፡፡
- በግዥ አካባቢ ትልቅ ችግርና መጓተት፣ እና ብልሹ አሰራር አለ፡፡ ስለዚህ በመንግስት የግዥ ሁኔታ ላይ ስልጠና መስጠት አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡
- ለወደፊቱ ትምህርቱ በስርዓት (system) ላይ ያተኮረ ቢሆን ጠቃሚ ነው፡፡ የእያንዳንዱን መስሪያ ቤት የአሰራር ሂደት ለሙስና ያጋልጣል ወይ ወይስ አያጋልጥም የሚለው መታየት አለበት፡፡
- በትምህርት ቤትም ሆነ በሃገር ደረጃ በፍትሃዊነት ዙሪያ ስልጠና/ትምህርት ቢሰጥ፡፡ ሁሉም ነገር ያለው በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ስለሆነ፡፡
- ፍትሃዊነትን አማክሎ ከዖታ ጋር በተያያዘ፣ ዲሞክራሲያዊ ግንኙነትና አሰራር፣ ጥገኛ ያልሆነ አመለካከት፣ የተማሪዎች ፓርላማ እና የመሳሰሉት

- በሃብትና ንብረት ተቆርቋሪነት፣ ግልፅነት፣ ፍትሐዊነት፣ እኩልነት፣ የሰራተኛን ችግር የማዳመጥ ባሕል፣ ጊዜ ብክነትን እና የአሰራር ደንቦችና መመሪያዎችን በተመለከተ ትምህርቱ ቢሰጥ፡፡
- አሁንም ሚዲያ የተሻለ ነው፡፡ ጥሩ የሚሆነው የስነ-ምግባር መኮንኖችን ማትጋት እና አመዳደብ ላይም እነሱ እራሳቸው የፀዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡
- ስልጠናው በድርጅቱ በራሱ ቢሰጥ
- የሙስና ፅንሰ ሃሳብና የሙስና ህግን በተመለከተ ትምህርቱ ለህብረተሰቡ ቢሰርፅ
- ትምህርቱ መከላከልን መሰረት አድርጎ በስፋት ቢሰጥ ግን በሙስና ወንጀል የተዘፈቁትን የቅጣት ትምህርት በግልፅ ለህብረተሰቡ ይፋ ቢያደርግ፡፡
- ለሙስና የበለጠ የተጋለጡ ናቸው በሚባሉ የስራ ዘርፎች ለምሳሌ እንደ ፋይናንስ ባሉት ላይ ቢተኮር
- በተለጁም አንድ  ተሳታፊ የሚከተሉትን ዝርዝር ሃሳቦች ሰጥተዋል፡፡
    1. ለስልጠና የሚመረጡ ርዕሶች በጥንቃቄ ቢመረጡ፣
    2. በአንድ ፅንሰ ሃሳብ ላይ ተደጋጋሚ ስልጠና ባይሰጥ፣
    3. በድራማ፣ በጭውውት፣ በዝማሬ፣ በዶክመንተሪ ፊልም እና በመሳሰሉት ፍላጐት በሚስቡ መንገዶች ቢሰጥ፣
    4. ሙስና በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በተቋማት እና በሃገር ደረጃ የሚያስከትለው የከፋ ጉዳት በትምህርቱ ቢካተት እና
    5. በተለይ ከፍተኛ ባለስልጣናት ላይ ትኩረት ቢሰጥ፡፡

- ኮሚሽኑ ማትኮር ያለበት አስፈላጊ የስልጠና ማቴሪያሎች በማዘጋጀት ላይ ነው፡፡ ስልጠናው በዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡
- ተሿሚዎች መሾም ያለባቸው በችሎታና በስነ-ምግባር መሆን አለበት፡፡ በሙሰኞች ላይ የማያዳግም እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡ ይህ ለህዝብ በይፋ መገለጽና መታየት አለበት፡፡ ያለችሎታቸው እየተሾሙ በስራቸው

መሰሎቻቸውን በማሰባሰብ ሙስናውን ያጧጡፋሉ፡፡ እነዚህን ማጋለጥ ላይ መሰራት አለበት፡፡ ዛሬ አንዳንዶች እንዲሚሉት ስልጣን ባገኝ የድርሻየን እቦጭቅ ነበር የሚሉትን ማጋለጡ ቢጠናከር ይህ አባባል ፀያፍ ይሆን ነበር፡፡ የሙስና ፀያፍነትና መጥፎ ገፅታ በትምህርት ቤት በስርዓተ ትምህርት ተካቶ ተማሪዎች እየተማሩት ቢያድጉ፡፡

- በአጠቃላይ ግብረ-ገብነት (Morality) ላይ ቢተኮር፡፡ በተጨማሪ ህጉንም ማስተማር መልካም ነው፡፡ ሰዎች ለራሳቸው የሚያደርጉትን ለሌላው ሰው እንዲያደርጉ ቢደረግ ጥሩ ነው፡፡
- ከመንግስት መስሪያ ቤቶች በተጨማሪ ለማህበራት እና ለግል ድርጅቶችም ኮሚሽኑ ትምህርቱን ቢያዳርስ
- ሌላ ተሳታፊ የሚከተለውን ዝርዝር ሐሳብ ሰጥተዋል
    1. በመሰረቱ የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርት ከላይ ሳይሆን ከታች ከመዋዕለ ህፃናት ጀምሮ ቢያድግ፡፡
    2. የፀረ-ሙስናና ስነ-ምግባር ትምህርት ስርዓተ ትምህርት ተቀርፆለት እንደ አንድ ትምህርት በት/ቤቶች ቢሰጥ፡፡
    3. የአሁኑ ትውልድ ትምህርቱን ሲጨርስ/ሲመረቅ/ ሰርቶ ለመበልፀግ ሳይሆን ከዚያም ከዚህም ቦጫጭቆ ለመበልፀግ ስለሚፈልግ ስራ ላይ ከመሰማራታቸው በፊት የስነ-ምግባር ትምህርት በሴሚናር መልክ ለተወሰኑ ወራት ቢሰጣቸው፡፡
- በህብረተሰብ ተቋማት/ዕድር፣ ማህበር/ትምህርቱ ቢሰጥና ሙስናን አለማጋለጥ የተግባሩ ተባባሪነት መሆኑን ማስተማር
- ኮሚሽኑ እየጣረ ቢሆንም የሙስናው ክስተት ግን ባስደንጋጭ ሁኔታ እየጨመረ ነው፡፡ የሙስናው አይነቶችም በፍጥነት እየተቀያየሩ ናቸው፡፡ ከታች ባለው ባህል ላይ ካልተሰራ ችግሩ አይፈታም፡፡ ዘላቂ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት በህፃናትና ወጣቶች ላይ እንዲሁም በህብረተሰብ ውይይት ማለትም በዕድር በቀበሌ ደረጃ ተከታታይነት ባለው መልኩ መሰራት አለበት፡፡

- ኮሚሽኑ በዓይነትም በመጠንም የሰው ኃይል እጥረት ስላለበት በስነ-ምግባርና ሙስና ሙያ እስከ MA ደረጃ ስልጠና መስጠት አለበት፡፡ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ሙስናን የመከላከል ሥራ ቢሰራ ለምሳሌ በኛ መስሪያ ቤት (ጉምሩክ) በላብራቶሪና በባለሙያ ማስደገፍ ይቻላል፡፡
- ትምህርቱ በዩኒቨርሲቲው የአሰራር ስርዓት ጥራት መጠናከር ላይ ቢያተኩር፡፡ ለተመራቂ ተማሪዎች ከስራ ስምሪት በፊት የተጠናከረ የስነ-ምግባር ትምህርት ቢሰጥ፡፡ ወጥ የሆነ ዩኒቨርሲቲዎችን ሊያሰሩ የሚችሉ ደንቦችና መመሪያዎች ቢወጡ
- ትምህርቱ ላይ አጥፊዎች ሲያጠፉ ብቻ ሳይሆን በህግ ሲጠየቁና ሲቀጡም ቢቀርብ፡፡ እንደገቢዎች ሚኒስቴር የተሟላ ጊዜ ኖሮት (በቴሌቪዥንና በሬዴዮ) ክሶችንና ፍርዶችን ቢያቀርብ፣ በህትመትም ቢያወጣ፡፡ ስልጠናውም እንደየመስሪያ ቤቱ እንጂ አንድ ዓይነት ባይሆን፣
- ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ትምህርቱ ቢሰጥ ተማሪዎች እንደ ባህል ይዘውት ያድጋሉ፣ ሙስናንም የሚፀየፍ ትውልድ ይፈጠራል፡፡
- ትምህርቱ እንደ አንድ ፓኬጅ ቢሰጥ የሚለው በብዙ ተሳታፊዎች ጉልቶ ወጥቷል፡፡

## 5.4 የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በማቋቋምና በማገዝ ኮሚሽኑ የተጫወተውን ሚና በተመለከተ

የሥነምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን ከሚያከናውናቸው ተግባራት ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በማገዝ እንዲሁም በሥነምግባር መመሪያ ዝግጅት የሚከናወኑ ተግባራት ሙስናን ለመከላከል በዋነኛነት ከሚጠቀሱ ተግባራት መካከል ናቸው፡፡ በዚህም ዙሪያ በጥናቱ ለተሣተፉ ሃላፊዎችና ሠራተኞች ጥያቄዎች ቀርበው ውጤቱም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በመጀመሪያ የቀረበው ጥያቄ ኮሚሽኑ በተለያዩ የፌደራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሥር የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን

አሠራር ለመወሰን በወጣው ሚኒስቴሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 144/2000 መሠረት ኮሚሽኑ እነዚህን የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በማቋቋምና ከተቋቋሙም በኋላ በእንቅስቃሴያቸው ዙሪያ ለማገዝ በተደረገው እንቅስቃሴ የተጫወተው ሚና እንዴት ነበር የሚል ሲሆን ከመቶ 37 የሚሆኑት ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተ የገለፁ ሲሆን 28 በመቶ የሚሆኑት ሚናው ዝቅተኛና በጣም አነስተኛ እንደነበር ገልፀዋል (ሠንጠረዥ 14 ይመልከቱ)፡፡

ሠንጠረዥ 14 የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በማቋቋምና በማገዝ ኮሚሽኑ ያደረገው አስተዋጽኦ

| የኮሚሽኑ ሚናው | በቁጥር | በመቶኛ | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|
| በጣም ከፍተኛ ነው | 287 | 10.5 | |
| ከፍተኛ ነው | 730 | 26.7 | |
| መወሰን አልችልም | 938 | 34.3 | |
| ዝቅተኛ ነው | 476 | 17.4 | 579.27* |
| በጣም ዝቅተኛ ነው | 306 | 11.2 | |
| ድምር | 2737 | 100.0 | |
| በመልስ ያልተካተተ | 259 | | |
| ጠቅላላ ድምር | 2996 | 1000 | |

* $P< .01$

ይሁን እንጂ ከአሀዛዊ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ኮሚሽኑ በአንዳንድ መ/ቤቶች በተለይም የመንግስት ልማት ድርጅቶችና ፌደራል የመንግሥት መ/ቤቶች የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በማቋቋምና በማገዝ የተሻለ ሥራ እንደሠራ ድርጅቶችን ወክለው በጥናቱ የተሳተፉት ግለሰቦች አመልክተዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው የኮሚሽኑ የትኩረት አቅጣጫ በመንግስት የልማት ድርጅቶችና ፌደራል መስሪያ ቤቶች ሙስና እንዳይፈፀም በመከላከል ዙሪያ ያተኮረ መሆኑን ነው፡፡

ይሁን እንጂ ስለ ሥነምግባር ማስተማር ያለብን ግዴታ ሙስና በሚፈፀምበት ቦታ መሆን የለበትም:: ስለ ሥነምግባርና ስለ ሙስና አደገኛነት በሁሉም ሥፍራ ትምህርት መሰጠት አለበት፡፡ በተለይም ሰው በብዛት የሚገኝባቸው ቦ□ዎች ማለትም ትምህርት ቤትና የሃይማኖት ተቋማት አካባቢ ብልሹ አሠራርን አስወግዶ የተሻለ አሠራር ለመዘርጋት የሚደረገውን ጥረት ወጣቶችና ሌላው የህብረተሰብ ክፍል □ንዲያውቅ ማድረግና የተሻለ ሥርዓት እንዲተገበር ግፊት እንዲያደርግ ያስፈልጋል:: ይህንንም በተመለከተ በቡድን ውይይት የተሳተፉት የሥራ ኃላፊዎችና የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሠራተኞች አበክረው ገልፀዋል::

በሌላ በኩል ደግሞ ድርጅትዎ የሥነምግባር መመሪያ/ደንብ በማውጣት ተፈፃሚ እያደረገ ነው ወይ ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ 46 ከመቶ የሚሆኑት በአዎንታ □መለሱ ሲሆን 23 በመቶ የሚሆኑት መመሪያ አለመኖሩን አመልክተዋል፡፡ የዚህ ልዩነት የጎላ መሆኑ በካይ እስኬር ስታትስቲክስ ተረፉፅ□ል ($\chi^2$=236.97, P<01) (ሠንጠረዥ 15ን ይመልከቱ):: በትምህርት ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶችና በፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሚሠሩ □ላፊዎችና ሠራተኞች የሥነምግባር መመሪጸ ስለመኖሩ የተሻለ ግንዛቤ እንዳላቸው ጥናቱ ጁቷቁማል::

**ሠንጠረዥ 15 በመስሪጸ ቤታቸው የሥነምግባር መመሪያ ስለመኖሩ**

| በመ/ቤትዎ የሥነ ምግባር መመሪያ አለ ወይ? | በቁጥር | በመቶኛ | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|
| አዎ | 1312 | 45.8 | |
| የለም | 646 | 22.6 | 236.97* |
| መረጃው የለኝም | 901 | 31.5 | |
| ድምር | 2859 | 100.0 | |
| የተዘለለ | 137 | | |
| **ጠቅላላ ድምር** | 2996 | | |

* P< .01

አነስተኛ ቁጥር የማይባል ተጠያቂዎች የሥነምግባር መመሪያ ስለመኖሩ የሚያውቁት እንደሌለ ገልፀዋል፡፡ ይህም የሚያስገነዝበው በርካ□ ቁጥር ያላቸው ተጠያቂዎች የሥነምግባር መመሪያ በድርጅታቸው ውስጥ አለመኖሩን ቢኖርም

እንኳ ሠራተኛው እንዲያውቀው ለማድረግ □ተካሄ□ዉ እንቅስቃሴ አነስተኛ መሆኑን እንዲሁም የሥነምግባር መመሪያ ቢኖርም እንኳ ሙስናን ለመከላከል ያደረገው አስተዋፅኦ ይህን ያክል የጎላ ነው ብለው እንደማያምኑ ከሰጡት መልስ ለመረዳት ይቻላል፡፡ የሥነምግባር መመሪጸ ረቂቅ በተቋማት ተዘጋጅቶ በኮሚሽኑ አስተያየት የመስጠትና የማዳበሩ ሥራ □ንዳለ ሆኖ ሠራተኛዉ እንዲያውቀው በማትረፅ በሥራ ላይ አለመዋሉ በአብዛኛዉ ሠራተኛና በፀረ-ሙስና ትግሉ መካከል ያለውን ክፍተት ያሣያል። በዚህም በኩል ኮሚሽኑን ብ□ ሥራ □ንደሚጠብቀው ያሣያል። መመሪያ ማውጣት ብቻ በቂ እንዳልሆነ ተከታትሎ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ □ንደሚያስፈልግ ያስገነዝበናል።

## 5.5 የአሠራር ሥርዓት ጥናትን በተመለከተ

ኮሚሽኑ ብልሹ አሠራሮችንና ሙስናን የሚከላከልበት አንዱ ዘዴ በተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማድረግ የተሻለ አሠራር የሚዘረጋበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው፡፡ ይህን በተመለከተ የተለያዩ ጥያቄዎች በጥናቱ ለተሣተፉ የፌደራል መ/ቤቶች ሠራተኞችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎች ቀርቦላቸው ነበር፡፡

የመጀመሪያው ጥያቄ ያተኮረው ኮሚሽኑ በአካል በመገኘት በመ/ቤትዎ/በድርጅትዎ የተለያዩ የሥራ ዘርፎች አሠራር ላይ ጥናት አድርጓል ወይ የሚል ነው፡፡ ይህን ጥያቄ 1066 ሰዎች የመለሱት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 35 በመቶ የሚሆኑት ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት የተለያዩ ጥናቶች በኮሚሽኑ መከናወናቸውን አመልክተዋል፡፡ ጥናቶቹም ያተኮሩት በዕቃ ግዥ፣ በፋይናንስ፣ ሠራተኛ አስተዳደር፣ የንብረት አጠቃቀምና ደንበኞች መስተንግዶ ዙሪያ እንደሆነ የዚህ ጥናት ውጤት ያሣያል፡፡

በኮሚሽኑ የተደረገው ጥናት ሙስናን ከመከላከል አንፃር ጠቃሚ ነበር ወይ የሚለውን ጥያቄ 761 የመለሱት ሲሆን 67 ከመቶ የሚሆኑት ጠቃሚ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የጥናቱን አስፈላጊነት በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያምኑበት አመልክተዋል።

ተመሣሣኙ ዓጸቄ በቃለመጠይቁ ለተሣተፉ ሰዎች ቀርቦ የነበረ ሲሆን አብዛኛዎቹ ተገኙ ያሏቸውን ተጨማሪ ውጤቶች በዝርዝር አስረድተዋል:: ዋና ዋናዎቹም የሚከተሉት ናቸው::

- የአሰራር ግልፅነት እና ተጠያቂነት እንዲኖር አድርጓል፣
- ሙስና መስራት ሊያስጠይቅ እንደሚችል በሰራተኛው ዘንድ ግንዛቤ ፈጥሯል (ኃላፊዎችንና ሰራተኞችን በተጠያቂነት ስሜት እንዲሰሩ አነቃቅተዋል)፣
- ኃላፊዎች በሚወስኑት ውሳኔ ላይ ጠንቃቃ እንዲሆኑ አድርጓል፣
- ስራዎች በደንብና በመመሪያ መሰረት በጥንቃቄ እንዲከናወኑ ረድቷል፣
- የግዥ ስርዓቱን ለማጠናከር ምክንያት ሆኗል (የግዥ ስርዓቱ ደንብና መመሪያን የተከተለ እንዲሆን አድርጓል)፣
- ብልሹ አሰራርን አስቀርቷል፣
- የሙስናና ስነ-ምግባር ጉድለት ክፍተት የሚታይባቸው የስራ ክፍሎች እንዲስተካከሉ አድርጓል ፣
- ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ለመለየት አስችሏል (የአሰራር ክፍተቶችን በማየት እርምት ለመውሰድ ዕድል ፈጥሯል)፣
- ኃላፊዎችና ሰራተኞች የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ አድርጓል፣
- የተለያዩ የስራ ክፍሎች ስራቸውን በመመሪያ መሰረት እንዲሰሩ ረድቷል፣
- ለሰራተኞች እስከ ታች ድረስ ስልጠና እንዲሰጣቸው ምክንያት ሆኗል፣
- አሳታፊነትን ጨምሯል፣
- የጨረታ አሰራር ተሻሽሏል (ምሳሌ፣ ጨረታ በጋዜጣ ወጥቶ የሚቆይበት ጊዜ አጭር ነበር አሁን ግን ሰላሳ ቀናት ሆኗል)፣
- የተሻሻሉ የአሰራር ስርዓቶች እንዲዘረጉ ተደርጓል (ግልፅና ተጠያቂነት ያለው መመሪያ ማውጣት ተችሏል)፣
- የአሰራር መመሪያ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፣
- የሰራተኞች ተነሳሺነትና ተቆርቋሪነት ጨምሯል ፣
- የስነ-ምግባር መኮንን ጽ/ቤት እንዲቋቋም ተደርጓል
- ኃላፊዎችም ሆኑ ሰራተኞች በስነ-ምግባር እንዲታነፁ አድርጓል፣

- ስለሙስና ያለውን ግንዛቤ አሳድጓል፣
- የግዥ መመሪያ በአዲስ መልክ እንዲዘጋጅ ሆኗል፣
- በሰራተኞች የቢሮ ሰዓት አጠቃቀም ላይ መሻሻል አምጥቷል፣
- የስነ-ምግባር ደንብና መመሪያ ለሁሉም ሰራተኞች ተሰራጭቷል፣
- የደንበኞች መስተንግዶ ቅሬታን በተወሰነ ደረጃ ቀንሷል እና
- ሰነዶች በአግባቡ እንዲያዙ አድርጓል ወዘተ ናቸው፡፡

በመስሪያ ቤትዎ ውስጥ መጠናት ሲገባቸው ያልተጠኑ የሥራ ክፍሎች ካሉ ቢገልፁልን ለሚለው ጥያቄ የጥናቱ ተሣ□ፊዎች የሚከተለውን ዘርዝረዋል፡-

- የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር ክፍል/የፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር ንዑስ የስራ ሂደት/፣
- የግዥ ክፍል (የግዥ የስራ ሂደት)፣
- የሰው ኃብት አስተዳደር፣
- የሽያጭ ክፍል፣
- የመሬት አስተዳደር የስራ ሂደት፣
- የውልና ማስረጃ የስራ ሂደት፣
- ተሽከርካሪ ደህንነትና ቁጥጥር ክፍል፣
- የደንበኞች አገልግሎት ዘርፍ  እና
- የስነምግባር መከታተያ ክፍል

በአዲስ አበባ ነዋሪዎች (□ረም) ቡድን ውይይት የተሳተፉትም ተመሣሣይ መልስ የሰጡ ሲሆን ቀደም ብለው ያልተነሱ ተጨማሪ የሥራ ክፍሎች □ንዳሉም ቶልናኽል፡፡ □ነዚህም፡-

- የንብረት፣ ፋይናንስና የግዥ የሥራ ዘርፎች፣
- የሰው ሐብት አስተዳደር (የሰራተኞች ቅጥር፣ ምደባ፣ እድገት)፣
- የደንበኞች አገልግሎት ክፍል፣
- የተሽከርካሪ ጥገና ክፍል፣
- የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት (የሕዝብ ግንኙነት የስራ ሂደት)፣

- የስነምግባር መከታተያ ጽ/ቤት፣
- የሕግ አገልግሎት ክፍል፣
- የግንባታ ስራዎች ማስተባበሪያ ቢሮ፣
- የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክፍል፣
- የቴክኒክ የስራ ሂደት፣
- የኦፕሬሽን የስራ ሂደት፣
- የትራንስፖርት ዘርፍ፣
- የውጭ ግኙ ክፍል፣
- ኦዲት መምሪያ፣
- ምርት ክፍል፣
- የሰራተኛ ማሕበር፣
- የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት፣
- ወንጀል ምርመራ ክፍል፣
- የቤቶች ማስተላለፍ ክፍል፣
- የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ክፍል፣
- መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ክፍል፣
- የአየር ቲኬት መሸጫ ክፍሎች፣
- መሬት አስተዳደርና ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ጽ/ቤት፣
- ቦታን በጨረታ የማስተላለፍ የስራ ሂደት እና
- የቅሬታ፣ አቤቱታና ደንበኞች እርካታ ክትትል ፈፃሚ የስራ ሂደት ናቸው፡፡

የሥራ ክፍሉ ቢጠናም አሁንም ድረስ ችግሩ አልተፈ□ም የሚሉ ከሆነ ይዘርዝሩ ለሚለዉ ዓጸቁ □ጥናቱ ተሳ□ፊዎች የሚከተሉትን ጠቅሰዋል፡፡

- የንብረት ብክነት፣
- የተጠያቂነትና ግልፅነት አለመኖር፣
- የገንዘብ ብክነት እና ምዝበራ እና
- በፊት የነበሩት ችግሮች አንዳሉ መታየታቸው

በተጨማሪም በቡድን ውይይት የተሳተፉት በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ ሃሣብ አቅርበዋል።

- ዕቃ ግዥን በተመለከተ (በተጋነነ ዋጋ ዕቃ ይገዛል፣ ጊዜው ያለፈበትና የማያገለግል ዕቃ ይገዛል፣ በወቅቱና በመስፈርቱ መሰረት ግዥዎች አለመከናወናቸው፣ የግዥ ስርዓቱ በአጠቃላይ ከችግር አለመፅዳቱ፣ የፕሮፎርማ አሰባሰብ ችግር)፣
- በንብረት አስተዳደር ቀልጣፋ አሰራር ያለመታየት (ምሳሌ፣ የንብረት ብክነት ሊቀንስ አልቻለም)፣
- ኮሚሽኑ ካጠና በኋላ ያስቀመጣቸው የመፍትሄ ሐሳቦች ተግባራዊ ያለመሆን
- ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም (ለምሳሌ፣ የመንግስት የስራ ሰዓትን ለመንግስት ስራ ብቻ አለማዋል)፣
- የደንበኞች አገልግሎት በተቀላጠፈና ከሙስና በፀዳ መልኩ መስጠት አለመቻል፣
- ከብሔር ጋራ በተያያዘ የሚንፀባረቅ አዱሏዊነት፣
- መጥፎ አስተሳሰብ ባላቸው ጠቋሚዎች የተነሳ ኃላፊዎች ስራቸውን ለመስራት ነፃነት አጥተዋል፣
- የደንበኛ ፍላጎትና የመስተንግዶ ጥራት አለመጣጣም፣
- የባለሙያ እጥረትና የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች አለመሟላት፣
- ወደ ቀደመው አሰራር መመለስ እና
- መወገድ ያለባቸው ንብረቶች አለመወገድ

ሠንጠረዥ 16 ኮሚሽኑ ያቀረባቸው የመፍትሄ ሐሳቦች ተገቢነት

| አስተያየት | በቁጥር | በመቶኛ | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|
| ተቂ/በ□ም ተቂ | 323 | 45.9 | |
| መወሰን አልችልም | 369 | 52.5 | 323.79* |
| ተገቢ/ፈጽሞ ተገቢ ያልሆነ | 11 | 1.6 | |
| ትምር | 203 | 100 | |

* $P < .01$

ከላይ ያለው ሰንጠረዥ እንደሚያሳየው ለጥያቄው መልስ ከሰጡት መካከል ግማሽ ያህሉ መወሰን አልችልም ያሉ ሲሆን ከቀሪዎች ግን ሁሉም ሊባል በሚችል ሁኔታ የመፍትሄ ሀሳቡን ተገቢነት ተቀብለዋል፡፡ ይኸም በስተትስቲክስ ($\chi^2$=323.79, P<.05) ተ□ፅጧል፡፡ ኮሚሽኑ ያቀረባቸው ሐሳቦች ተገቢ እንደሆኑ በጉልህ ይታያል፡፡

ኮሚሽኑ የሚያጠናቸው ጥናቶች እና የሚያቀርባቸው የመፍትሄ ሐሳቦች እንዲተገበሩ የጥናቱ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ጠቁመዋል፤

- ብዛት ያላቸው ተሳታፊዎች በተደጋጋሚ ያቀረቡት የመፍትሄ ሐሳብ የአፈፃፀም ክትትል መደረግ አለበት የሚል ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች ኮሚሽኑ የሚያጠናቸውን ጥናቶች እና የሚያቀርባቸውን የመፍትሄ አቅጣጫዎች ተግባር ላይ መዋላቸውን በደንብ ይከታተል ብለው መክረዋል፡፡ በተጨማሪም የተጠናው ጥናት ተግባራዊ መሆኑ በተወሰነ ጊዜ እየተገመገመ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል ብለዋል፣
- በጥናት የሚቀርቡት የመፍትሄ ሐሳቦች ለእያንዳንዱ ሰራተኛ በግልፅ ማሳወቅና ተግባራዊ ማድረጉን መከታተል፣
- ከሁሉም ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችለው መድረክ ኮሚሽኑ ሊኖረው ይገባል፡፡ ለምሳሌ፣ ሙያዊ እገዛ በማድረግና ትምህርት በመስጠት፣
- ኮሚሽኑ የያዘውን ዓላማ በማጠናከር በበለጠ ሕብረተሰቡን ማስተማር (ሰራተኛው በየጊዜው መሰልጠን አለበት)፣
- ቅጣትን ብቻ ሳይሆን ማስተማርንም የሚያበረታታ ስርዓት መዘርጋት፣
- የአሰራር ቆራጥነት መኖር አለበት/አመራሩ ቆራጥነትን ማጠናከር መቻል አለበት/፣
- የጥናቱ ሂደት አሳታፊ መሆን አለበት፣
- ሙሰኞችን ተከታትሎ ጠበቅ ያለ የሕግ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ማድረግ
- በጥናቱ ሁሉንም ዘርፎች ለማካተት መሞከር

- ኮሚሽኑ እራሱን ከሙስናና ስነ-ምግባር ጉድለቶች ማፅዳት፣ አርዓያ መሆንና ከመንግስት (ከፖለቲካ) ጣልቃ ገብነት ነፃ መሆን አለበት፣
- በየመስሪያ ቤቱ የሚመደቡ የስነ-ምግባር መኮንኖች የትምህርት ዝግጃነታቸው እና ስነ-ምግባራቸው እየታየ እንዲመደቡ መደረግ አለበት፡፡ በተከታታይም የማስፈፀም አቅማቸውን ለማጎልበት ስልጠና እንዲሰጣቸው መደረግ አለበት፣
- ኮሚሽኑ ባጠናቸው ጥናቶች እና ባቀረባቸው የመፍትሄ ሐሳቦች መሰረት እርምጃ ወይም ማስተካከያ መወሰዱን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ አንድ ተሳታፊ አስፈላጊው ቁጥጥርና ክትትል በስነ-ምግባር መኮንኑና በኮሚሽኑ ሰራተኞች ሊደረግ ይገባል ብለዋል፡፡ ሌላው ተሳታፊ ደግሞ በጥናቱ ውጤት መሰረት ሰነድ ማዘጋጀት፣ ባዘጋጀው ሰነድ መሰረት የተቋሙን አደረጃጀት አስተካክሎ ወደ ተግባር መግባትና አፈፃፀሙን እየገመገመ ቀጣይ ስራ መስራትን ጸስ□ልፉል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሌሎች ተሳታፊዎችም እንዲህ ብለዋል፡፡ ኮሚሽኑ ጥናቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚመለከታቸውን ሐላፊዎች ድጋፍ ለማግኘት መጣር አለበት፡፡ የጥናቱ ውጤትና መፍትሄ ሐሳቦች ተግባራዊነታቸውን መከታተልና የተገኘ ለውጥ መኖሩን መገምገምና በውጤቱም መሰረት መፈፀም፣
- ኮሚሽኑ ያጠናውን ጥናትና ውጤቱን ለተቋሙ ሰራተኞች በደንብ ማሳወቅ፡፡ ይህም ማለት ኮሚሽኑ ጥናቱን በሚገባ ማስተዋወቅና ግንዛቤ ማስረፅ እንዲሁም የተጠናው ጥናት ስራ ላይ መዋሉን መከታተል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንዳንድ ተሳታፊዎች የጥናቱን ውጤትና የመፍትሄ ሐሳቦችን ለማኔጅመንቱ፣ ለፀረ-ሙስና መኮንኑና ለሰራተኞች በጋራ ግንዛቤ የሚያገኙበት ስርዓት ቢዘጋጅ ሲሉ መክረዋል፣
- መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች አቅም እንዲፈጥሩ እገዛ ማድረግ አለበት፣
- ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ሙሉ ተሳትፎ ማድረግ አለበት፡፡ ለዚህም ስኬታማነት ኮሚሽኑ ለሕብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት

ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት፡፡ ኮሚሽኑ ሳይፈራ ሁሉም መስሪያ ቤት፣ ግለሰብና ባለስልጣን ዙሪያ መስራት አለበት፣

- በስነ-ምግባራቸው የተሻሉ የስነ-ምግባር መኮንኖች በየተቋሙ መመደብ አለባቸው፣
- የሚጠቆሙ ጥቆማዎች በሚስጥር ሊያዙ ይገባል፣ ለጠቋሚዎችም የሕግ ከለላ ሊሰጣቸው ይገባል፣
- ጥናቱ ከጥናት አልፎ የድርጅቱ/የመስሪያ ቤቱ የስራ መመሪያ ሊሆን ይገባል፡፡ ከተቻለም በመንግስት ድረጃ ታይቶ ዘለቄታዊ እንዲሆን የሕግ አካል የሚሆንበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፣
- በኮሚሽኑ እጅ የሚገኙ የሙስና ወንጀሎችን ጉዳይ እየተከታተሉ በአስቸኳይ ውሳኔ ማሰጠት፣
- ኮሚሽኑ እራሱን በሰው ኃይልና በቁሳቁስ ማጠናከር አለበት፣
- ከባለ ድርሻ አካላት ጋር የተቀናጀ አሰራር መዘርጋት አለበት፣
- አቅምና ልምዱ ካላቸው አማካሪ ድርጅቶች ጋር በመሆን መስራት አለበት፣
- የሚቀርበው የመፍትሔ ሐሳብ አቅምን ያገናዘበና ሊተገበር የሚችል መሆን አለበት፡፡ ይህንን በተመለከተ አንድ ተሳታፊ ሲገልፁ በጥናቱ የሚቀርቡት የመፍትሄ ሐሳቦች ቁንፅል እና የአንድ ወገን አስተሳሰቦችን ብቻ የተከተሉ ሳይሆን በበቂ መረጃ የተደገፉ እንዲሁም የመስሪያ ቤቶችንና ድርጅቶችን አሰራር ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ መሆን ይገባዋል ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ጥናቶችን ተከትሎ አንዳንድ መሻሻሎች በቢሮ አካባቢ እንደተመለከቱ በርካታ ተሳታፊዎች የገለፁ ሲሆን አብዛኛዎቹ ግን አሁንም (ማለትም 65 በመቶ የሚሆኑት) በዚህ ጉዳይ በቂ መረጃ እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡ ይህም የጥናቱ ውጤት በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ሲተነተን ማለትም የግዥ ሥርዓቱን፣ የሠው ኃይል አስተዳደር ስርዓቱን፣ የፋይናንስ ስርዓቱን፣ የንብረት ብክነትን፣ የመከላከልና የደንበኞችን መስተንግዶ ከማሻሻል አንፃር የነበረው ሚና ጎልቶ የወጣ እንዳልሆነ አብዛኛዎቹ "መረጃ የለኝም" የሚለውን መልስ በመስጠት አመልክተዋል፡፡

ቢሆንም መወሰን አልችልም ካሉት ውጭ ያሉት ሲታይ በጣም ተሻሽሏል ወይም ተሻሽሏል ያሉት አልተሻሻለም ካሉት ቁጥራቸው የበዛ መሆኑ በስታስቲክስ □ይቷል:: (የእያንዳንዱን $X^2$ በሰንጠረዡ ውስጥ ይመለከቱ፡፡ ይኸም ማለት መረጃ ካላቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል በኋላ መልኩ ከፍ ያለ ቁጥር ያላቸወ በመ/ቤቶች የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የታየው ተጽዕኖ አወንታዊ እና አበረታች መሆኑን አመልክቷል::

**ሠንጠረዥ 17 በኮሚሽኑ ጥናት መሠረት በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ስለተደረገው መሻሻል**

| | ዕዴ | | □ሰው □ጁል አስተዳደር | | ፋይናንስ | | የንብረት አጠቃቀምና አስተዳደር | | የደንበኞች መስተንግዶ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በቁዓ ር | በመቶኛ | በቁዓ ር | በመቶኛ | በቁዓ ር | በመቶኛ | በቁዓ ር | በመቶኛ | በቁዓ ር | በመቶኛ |
| በ□ም ተሻሽሏል | 14 | 2.4 | 15 | 2.9 | 21 | 4.0 | 24 | 4.2 | 41 | 7.5 |
| ተሻሽሏል | 148 | 25.8 | 120 | 23.1 | 148 | 28 | 178 | 31.1 | 187 | 34.2 |
| መወሰን አልችልም | 371 | 64.6 | 335 | 64.4 | 327 | 61.9 | 346 | 60.4 | 283 | 51.8 |
| አልተሻሻለም | 30 | 5.2 | 36 | 6.9 | 27 | 5.1 | 20 | 3.5 | 30 | 5.5 |
| □ ራሽ አልተሻሻለም | 11 | 1.9 | 14 | 2.7 | 5 | .9 | 5 | .9 | 5 | .9 |
| ትምር | 574 | 99.9 | 520 | 100 | 528 | 99.9 | 573 | 100.1 | 546 | 99.9 |
| □ተ□ለለ | 1121 | | 1175 | | 1167 | | 1122 | | 1149 | |
| $\chi^2$ | 826 | | 714 | | 703 | | 757 | | 532 | |

የኮሚሽኑ ጥናት በአጠቃላይ (የአምስቱም ድምር) ከመ/ቤቶች አንፃር ሲ□ጁ እንደሚከተለው ቀርቧል::

**ሠንጠረዥ 18 ኮሚሽኑ ያካሄደው ጥናት ውጤታማነት ከመ/ቤቶች አንፃር በANOVA ሲ□ጁ**

| መ/ቤቶች | በቁዓ ር | አማካይ | ሥርጭት | F |
|---|---|---|---|---|
| የፌደራል መንግሥት መ/ቤቶች | 269 | 16.24 | 2.80 | 0.25 |
| የመንግስት ልማት ድርጅቶች | 148 | 16.08 | 2.41 | |
| ሌሎች መ/ቤቶች | 12 | 16.33 | 3.03 | |
| | 429 | 16.18 | 2.68 | |

**ሠንጠረዡ እንደሚያሳየው የአስተያየቶች አማካይ ውጤት** (Mean=**16.18) ወደ አወን□ዊ አስተየየት ያዘነበለ ነው:: ከፍተኛው (አወንታዊ) አስተያየት 25 ሲሆን ዝቅተኛዉ (አሉታዊ) አስተያየት 5 ነው::**

**ይኸ አስተያየት በ**ANOVA **ሲ□ጁ** (F=0.25, P>.05) **በመስሪያ ቤቶች መካከል ልዩነት □ንደሌለ ያሳያል::**

**ሠንጠረዥ 19 ኮሚሽኑ ያካሄደው ጥናት ውጤ□ማነት በየዘርፎቹ ካለው መሻሻል ጋር ያለው ዝምድና**

| | 1 | 2 | 3 | 4 |
|---|---|---|---|---|
| 5. ዕጼ | - | | | |
| 6. □ሰዉ ኃይል አስተዳደር | .55** | - | | |
| 7. የፋይናንስ ስርዓት | .62** | .63** | - | |
| 8. የንብረት ብክነት | .57** | .63** | .70** | - |
| 5. የደንበኞች መስተንግዶ | .45** | .55** | .57** | .61** |
| | | | | |

** P< .001

**ኮሚሽኑ በየመ/ቤቶች ላካሄደው ጥናት ውጤታማነት በጥናቱ ተሳታፊዎች የተሰጡት ግምገማዎች ተዛማጅነት እንዳላቸው ከላይ የተሰጠው የስታቲስትክስ (**Pearson's r**) ውጤቶች አሳይቷል::**

**ይህ ማለት በአንድ መ/ቤት የተወሰነ ዘርፍ ውስጥ የሚኖር የስራ መሻሻል በመ/ቤቱ ሌሎች ዘርፎችም ሊታይ እንደሚችል በተዘዋዋሪ መንገድ ይጠቁማል::**

**ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተነሣው ጥያቄ ኮሚሽኑ ሙስናን ለመከላል የሚያደርገው በጥናት የተደገፈ እንቅስቃሴ ሙስና እንዲቀንስ አስተዋፅኦ አድርጓል ብለው ያምናሉ ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ 40 በመቶ የሚሆኑት (ማለትም ጥያቄውን ከመለሱት 958 ተጠያቂዎች 383) በእርግጠኝነት መናገር እንደሚችሉ ነው የገለፁት:: ለ□ህም የተለያዩ ምክንያቶችን ሰጥተዋል:: ለመጥቀስም ያህል**

- ተከታታይ የሆነ ማስተማር የአስተሳሰብ ለውጥ ስለሚያመጣ፣
- በትምህርት የማይለወጥ ነገር ስለሌለ፣
- ማስተማር የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት ቁልፍ መሳሪያ በመሆኑ፣
- ትምህርት የሰውን ጭንቅላት ወደተሻለ ደረጃ ያሳድጋል ብዩ ስለማምን ወዘተ

በሌላ በኩል በርካታ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች የኮሚሽኑን ውጤታማነት በተጨባጭ ተገኝቷል ብለው ከሚያስቧቸው ለውጦች አንፃር ገልፀውታል፡፡ በዚህ መሠረት መላሾቹ የሚከተሉትን ለውጦች የኮሚሽኑን ውጤታማነት ማሳያ ናቸው ብለው ጠቅሰዋቸዋል፡፡

- ኮሚሽኑ የሰጠው ትምህርት ሙስና ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ በማሳየቱ፣
- በሙስና ዙሪያ የህብረተሰቡ ግንዛቤ እየጨመረ በመምጣቱ /እጅግ በርካታ መላሾች የጠቀሱት/፣
- ትምህርቱን በድራማና በጭውውት መልክ በመገናኛ ብዙሃን ማሰራጨቱ፣
- ትምህርቱ ሰዎች ወደ ሙስና ከመግባት እንዲቆጠቡ የማስጠንቀቂያ መልክት በማስተላለፉ፣
- የሙስና ወንጀል፣ ክስና ቅጣት በመገናኛ ብዙሃን በማስተላለፍ የህብረተሰቡን ግንዛቤ አሳድጓል /እጅግ በርካታ መላሾች/፣
- ትምህርቱ የሰራተኛውን አመለካከት እንዲቀየር በመርዳቱ፣
- ትምህርቱ በመልካም የሥራ ባህል ማጐልበት አስችሏል፣
- የኮሚሽኑ ትምህርት፣ ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል የሚለውን አባባል አደጋ አሳይቷል፡፡

ኮሚሽኑ ሙስናን በመከላከል ረገድ ያስገኘውን ውጤታማነት "መወሰን አልችልም" በማለት የመለሱ ተሳታፊዎች ያስቀመጧቸው ምክንያቶች፡-

- መረጃ የሌላቸው መሆኑን፣
- ሙስና ያለበትን ደረጃ እንደማያውቁ፣
- ሀገሪቱ ከሙስና ነጻ ስላልሆነች፣

➢ ኮሚሽኑ ሥራ በሌላ አካላት ተፅዕኖ ሥር የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ወደፊት መጠናት አለባቸው የሚባሉ የሥራ ዘርፎች ካሉ እንዲገልፁ ተጠይቀው ብዛት ያላቸው በዚህ ቡድን የተካተቱ የጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጡት ምላሽ በመስሪያ ቤታቸው ወይም በድርጅታቸው የአሰራር ስርዓት ጥናት አለመደረጉን አልያም ደግሞ መደረጉን እንደማያውቁ ነው፡፡ የተወሰኑ ተሳታፊዎች ግን የሚከተሉትን መጠናት ሲገባቸው ያልተጠኑ የሥራ ዘርፎችን ዘርዝረዋል፡፡

- የንብረት፣ ፋይናንስና የግዥ የሥራ ዘርፎች፣
- የሰው ሐብት አስተዳደር (የሰራተኞች ቅጥር፣ ምደባ፣ እድገት)፣
- የደንበኞች አገልግሎት ክፍል፣
- የተሸከርካሪ ጥገና ክፍል፣
- የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት (የሕዝብ ግንኙነት የሥራ ሂደት)፣
- የስነ-ምግባር መከታተያ ጽ/ቤት፣
- የሕግ አገልግሎት ክፍል፣
- የግንባታ ሥራዎች ማስተባበሪያ ቢሮ፣
- የግብርና አወሳሰንና አሰባሰብ ክፍል፣
- የቴክኒክ የሥራ ሂደት፣
- የኦፕሬሽን የሥራ ሂደት፣
- የትራንስፖርት ዘርፍ፣
- የውጭ ግዥ ክፍል፣
- ኦዲት መምሪያ፣
- ምርት ክፍል፣
- የሰራተኞች ማሕበር፣
- የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት፣
- ወንጀል ምርመራ ክፍል፣
- የቤቶች ማስተላላፍ ክፍል፣

- የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ክፍል፣
- መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ክፍል፣
- የአየር ቲኬት መሸጫ ክፍሎች፣
- መሬት አስተዳደርና ግንባታ ፍቃድ አሰጣጥ ጽ/ቤት፣
- ቦታን በጨረታ የማስተላለፍ የሥራ ሂደት፣
- የቅሬታ፣ አቤቱታና ደንበኞች እርካታ ክትትል ፈፃሚ የሥራ ሂደት

## 5.6 የሙስና ወንጀልን በመመርመር፣ በማጋለጥና ለሕግ በመክሰስ ረገድ

*የፌደራል የሥነምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን አንዱ አብይ ተግባር የተፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችን መመርመር መክሰስና ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ ማስቀጣት ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ ኮሚሽኑ ባለፉት 9 ዓመታት ውስጥ ምን ያህል ውጤታማ ነበር የሚለውን ለማወቅ ለጥናቱ ተሳታፊዎች የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ነበር፡፡*

*በመስሪያ ቤትዎ/ድርጅትዎ ምርመራና ክስ ሊመሠረትበት የሚያስችል ሙስና ወንጀል ተከስቶ ያውቃል ወይ ለሚለው ጥያቄ 45 ከመቶ የሚሆኑት አዎን ብለው የመለሱ ሲሆን አነስተኛ ቁጥር ያላቸው (ማለትም 20 በመቶ) በኮሚሽኑ መመርመር አለበት የሚሉት ሁኔታ በድርጅታቸው/ መ/ቤታቸው ውስጥ አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡ ይህ የሚያሣየው ሙስና አሁንም የአገሪቱ አሳሳቢ ችግር መሆኑንና ቀደም ብሎ ሙስና ቅኝት በኢትዮጵያ* (Corruption Survey, 2001:55) *በሚል በተካሄደው ጥናት ከተገኘዉ መረጃ ጋር ተመሣሣይነት እንዳለው ነው፡፡*

*ከዚህ ላይ መረዳት □ንደሚቻለው ምንም እንኳ አብዛኛዎቹ ተጠያቂዎች መልስ ከመስጠት ቢቆጠቡም መልስ ከሰጡት ውስጥ ብልጫ ቁጥር ያላቸው ሙስና ጋር የተያያዘ ስነምግባር የጐደለው አካሄድ በድርጅታቸው ውስጥ እንደተከሰተና ጁህም በኮሚሽኑ መመርመር አለበት ብለው □ንደሚያምኑ ገልፀዋል፡፡*

*ሠንጠረዥ 20 በኮሚሽኑ ምርመራ የሚያስፈልጋቸው ሙስና-ነክ ሁኔ□ዎች በድርጅታቸው ስለመከሰቱ*

| ሙስና ነክ ሁኔ□ዎች | በቁጥር | በመቶኛ | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|
| ተከስቷል | 544 | 44.8 | |
| መወሠን አልችልም | 428 | 35.2 | |
| አልተከሰተም | 244 | 20.1 | |

**ሙስና በተከሰተባቸው መ/ቤቶች ኮሚሽኑ ምርመራ በማትረፅ ክስ መስርቶ አስቀጥቷል ወይ ለሚለው ጥያቄ ወደ ግማሽ የሚጠጉት (ማለትም 371 ከ777 ተጠያቂዎች) አናውቅም ያሉ ሲሆን 19 ከመቶ (144 ተጣያቂዎች) ብቻ በድርጅታቸው ውስጥ የታየው ሙስና በኮሚሽኑ እንደተመረመረና ክስም ተመስርቶ እንደነበር ይሁን እንጂ ተከሳሾች ቅጣት እንዳልተላለፈባቸው ገልፀዋል፡፡**

**ሠንጠረዥ 21** ኮሚሽኑ ወንጀሉን መርምሯል? ከሷል? አስቀጥቷል?

| | | | |
|---|---|---|---|
| *ድምር*<br>የተዘለለ | ***1216***<br>*1275* | ***100.0*** | ***112.92**** |
| **ጠቅላላ ድምር** | ***2491*** | | |

* P<.01

| | በቁዓ ር | በመቶኛ | አማካኝ ውጤት በመቶኛ | አጠቃላይ ድምር በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| መርምሯል ግን አልከሠሠም | 74 | 2.5 | 9.5 | 9.5 |
| አልመረመረም | 54 | 1.8 | 6.9 | 16.5 |
| መርምሯል ከሷል ግን አልቀጣም | 144 | 4.8 | 18.5 | 35.0 |
| መረጃው የለኝም | 371 | 12.4 | 47.7 | 82.8 |
| ሌላ ካለ | 134 | 4.5 | 17.2 | 100.0 |
| ትምር | 780 | 25.9 | 100.0 | |
| □ተ□ለለ | 2216 | 74.1 | | |
| ቷቅላላ ትምር | 2996 | 100.0 | | |

ተመሣሣጁ ዓጸቄ በቃለመቷጁቅ ለተሣተፉት የቀረበ ሲሆን አንዳንድ የመስሪያ ቤ□ቸው ሠራተኞች በኮሚሽኑ ተከሰው የተቀጡ መሆኑን አመልክተው በመቀ□ታቸው ተገኙ ያሏቸውን ተጨባጭ ውጤቶች □ንደሚከተለው □ርዌረኘዉ።

- ሌሎች ሠራተኞች ጥንቃቄ አድርገው ሥራቸውን እንዲሠሩ ትምህርት ሰጥቷል፡፡ ይህም ማለት ሌሎች ሠራተኞች ሥራቸውን ሲያከናውኑ ሙስና/ስርቆት ከፈፀሙ የሚጠየቁ መሆናቸውን በመገንዘባቸው የተጠያቂነት ስሜት እየዳበረ መጥቷል፡፡ አንድ ተሳታፊ ይህንን ጉዳይ "እኔን ያየህ ተቀጣ እንደሚባለው ሙሰኞች እንደፈለጉት እጃቸውን እንዳይዘረጉ አስተምሯል" ሲሉ ገልፀውታል፡፡ ሌላው ተሳታፊ ደግሞ ሙስኞችን መቅጣት የተጠያቂነት መንፈስ ያጎለብታል፣ ሕገ ወጥ ድርጊት ብፈፅም ልያዝ እችላለሁ፣ ከተያዝኩ ደግሞ እርምጃ ይወሰድብኛል ብለው እንዲጠነቀቁ ረድቷል ብለዋል፣
- የሙስና ወንጀል ቀንሷል፣
- ሙሰኞች እንደፈለጉ ዘርፈው እንደማያመልጡ እና ለመንግስት ኃብት ንብረት የሚቆረቆር አካል እንዳለ ግንዛቤ ፈጥሯል፡፡ ማለትም ሕግ እንዳለና ተመልካች መኖሩን ሠራተኛው ተረድቷል፣
- በገንዘብ አያያዝ በጣም ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲደረግ አድርጓል፣
- ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው አሠራር እንዲፈጠር እያደረገ ነው፣

- በሕግና ደንብ መሰረት ብቻ ሥራ እንዲሠራ አድርጓል (ደንብንና ስርዓትን ተከትሎ የመሥራት አዝማሚያ ታይቷል)፣
- ኃላፊዎች በተወሰነ መልኩ መስሪያ ቤቱን ከመመዝበርና ስል□ናቸውን አላግባብ ከመጠቀም ተቆጥበዋል፣
- ሠራተኞችም ሆኑ ኃላፊዎች ከስነ - ምግባር ጉድለት እንዲታቀቡ አድርጓል፣
- የመንግስት ሐብትና ንብረት እንዲመለስ ተደርጓል፣
- በግዥ ክፍል የነበረው የአሰራር ጉድለት ተስተካክሏ

ሙስኞችን መርምሮ ከሶና አሰቀጥቶ ሙስና እንዳይስፋፋ በማድረግ ረገድ የኮሚሽኑን ውጤታማነት በጣም አምናለሁ ወይም አምናለሁ በማለት የመለሱ የጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጧቸው ምክንያቶች፡-

- ኮሚሽኑ በተለያዩ ጊዜያት የሙስና ወንጀለኞችን ከሶ በማስቀጣቱ ሙሰኞች እንዲታቀቡ ረድቷል /ብዙ መላሾች የጠቀሱት/፣
- ኮሚሽኑ በተለይ በአዲስ አበባ የመሬት አስተዳደር፣ በመንግስት ንብረት ሽያጭ ጨረታና፣ በግዥ ሂደት የተከሰቱ የሙስና ወንጀሎችን መርምሮ ጥፋተኞችን ማስቀጣቱ የሙስና ወንጀል እንዳይስፋፋ ትልቅ እገዛ አድርጓል፣
- እየተወሰደ ያለው እርምጃ ሰዎች ህጋዊ መንገድን /አሠራርን/ እንዲከተሉ አድርጓቸዋል፣
- የኮሚሽኑ እንቅስቃሴ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት ጭምር እንዳሚከሰሱና እንደሚቀጡ በማመላከቱ የሙስና ወንጀልን መስፋፋት ቀንሶታል፣
- የኮሚሽኑ የሙስና ወንጀሎችን የመመርመር፣ ወንጀለኞችን የመክሰስና የማስቀጣት እንቅስቃሴ በመገናኛ ብዙሃን መገለፁ ሙስና እንዳይስፋፋ ረድቷል

ሙስና በተድበሰበሰና በስውር ሁኔታ ስለሚከናወን ሙስና የሚፈፅሙ ግለሰቦችን በተጨባጭ መረጃ አስደግፎ ለፍ/ቤት ማቅረብ የኮሚሽኑን ሥራ ፈታኝ ከሚያደርጉት ተግባራት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ኮሚሽኑ ሙስና ሲፈፀም ያዩ ግለሰቦች ጥቆማ እንዲሰጡ ያበረታታል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ለጥናቱ ተሳታፊዎች የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ነበር፡፡ ኮሚሽኑ በድርጅትዎ ውስጥ ሙስና ሲፈፀም እንዴት ነው መረጃ የሚደርሰው ለሚለው ጥያቄ 56 በመቶ (673 ከ 1212 ተጠያቂዎች) የሚሆኑት በጥቆማ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ 28 በመቶ የሚሆኑት ግን (336 ከ1212) መረጃው እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡

ሠንጠረዥ 22 ለኮሚሽኑ የመረጃ ምንጮች

| መረጃ ምንጭ | በቁጥር | በመቶኛ | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|
| በጥቆማ (1) | 673 | 55.5 | |
| በራሱ ጥርጣሬ (2) | 14 | 1.2 | |
| መረጃው የለኝም (3) | 336 | 27.7 | |
| ሌላ ካለ (4) | 48 | 4.0 | |
| 1 እና 2 | 96 | 7.9 | 1657.14* |
| 1 እና 4 | 45 | 3.7 | |
| ድምር | 1212 | 100.0 | |
| መልስ ጸልሰቷ | 1784 | | |
| ጠቅላላ ድምር | 2996 | | |

* P<.01

ይህም የሚያመለክተው ሙስናን ለመከላከል ጥቆማ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሠራተኞች ሙስና ሲፈፀም ለመጠቆም ብሎም ለማጋለጥ ይደፋፈሩ ዘንድ ከኮሚሽኑ የህግ ከለላ ማግኘታቸው በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ያለዚያ ለደህንነታቸውም ሆነ ለህይወታቸው ዋስትና ስለማይኖራቸው የሙስና ወንጀልን ከመጠቆም ይታቀባሉ፡፡ ስለዚህም የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች ጥቆማ የሚሰጠው ግለሰብ የህግ ከለላ እንደአስፈላጊነቱ ይደረግለታል ወይ ተብለው ተጠይቀው አብዛኞቹ (67.6%) መወሰን እንደሚያስቸግራቸው የገለጹ ቢሆንም ከተቀሩት ግን

በተቀራረበ መልኩ በከፊል (16.9%) በቂ ነው ሲሉ በከፊል (15.5%) ደግሞ በቂ የህግ ከለላ እንደማይሰጣቸው ገልጸዋል፡፡

በተመሣሣይ ሁኔታ ሙስና ለሚፈ□ሙ ሠራተኞች የሚሰጠው ቅጣት በቂ ነው ትላላችሁ ለሚለው 15.5 ከመቶ ብቻ አዎ ሲሉ 6.5 ከመቶ በቂ አይደለም እንዲሁም 77.8 ከመቶ መወሰን አንችልም በማለት መልሰዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው አብዛኞቹ ተጠያቂዎች ለሙሰኞች ስለሚሰጠው ቅጣት በቂ መረጃ እንደሌላቸው ነው፡፡ በሙሰኞች ስለሚፈፀሙ የተላያዩ ወንጀሎች በተመለከተ በስልጣን አለአግባብ መጠቀም በብዛት እንደሚከሰት የተጠቀሰ ሲሆን ምዝበራና መረጃ ማጭበርበር፣ እንዲሁም ስርቆትና ጉቦ መስጠት በዋናነት ተጠቅሰዋል፡፡

ሠንጠረዥ 23 ለሙሰኞች የሚሰጠው ቅጣት ብቃት

| ቅ□ቱ | በቁጥር | በመቶኛ | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|
| በቂ ነው | 114 | 15.5 | |
| በቂ አይደለም | 48 | 6.5 | 669.50* |
| መወሰን አልችልም | 569 | 77.8 | |
| ድምር | 731 | 100.0 | |
| መልስ ጸልሰቷ | 1760 | | |
| ጠቅላላ ድምር | 2996 | | |

* P<.01

በድርጅትዎ (መ/ቤትዎ) ውስጥ መከሰስና መቀጣት ሲገባው ያልተከሰሰ ሠራተኛ አለ ወይ ለሚለው ጥያቄ 11.2 በመቶ ብቻ አለ ብለው የመለሱ ሲሆን 25 በመቶ የሚሆኑ መከሰስ አለበት የሚባል የመ/ቤታቸው ሠራተኛ እንደሌለ ገልፀዋል፡፡ ጥያቄውን ከመለሱት አብዛኞቹ ማለትም 63.8 ከመቶ (645/1011) የሚሆኑት መልስ ከመስጠት ተቆጥበዋል፡፡

ሠንጠረዥ 24 በመስሪጸ ቤቱ መከሰስ አለበት የሚባል ሠራተኛ ስለመኖሩ

| | በቁጥር | በመቶኛ | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|

| | | | |
|---|---|---|---|
| አዎ | 113 | 11.2 | |
| የለም | 253 | 25 | |
| መረጃው የለኝም | 645 | 63.8 | 451.32* |
| ድምር | 1011 | 100.0 | |
| የተዘለለ | 1985 | | |
| **ጠቅላላ ድምር** | 2996 | | |

* P<.01

መከሰስና መቀጣት ሲኖርባቸው ለምን አልሆነም ለሚለው ጥያቄ 8.7 ከመቶ የሚሆኑት ጣልቃገብነት እንደምክንያት ሲያቀርቡ በኮሚሽኑና (4.8 በመቶ) በፍ/ቤት ችግር (2.1 በመቶ) ነው በማለት መልሰዋል፡፡ አሁንም 74 በመቶ የሚሆኑት (278/378) አናውቅም በሚል መልሰዋል፡፡ ይኸም በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 25 መከሰስና መቀጣት ሲገባቸው ያልተከሰሱበትና ያልተቀጡበት ምክንያት

| ያልተከሰሱበትና ያልተቀጡበት ምክንያት | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|
| በፍርድ ቤት አፈፃፀም ችግር | 8 | 2.1 |
| የኮሚሽኑ ምርመራና ክስ ሂደት ውጤታማ ባለመሆኑ | 18 | 4.8 |
| ሌላ ካለ | 33 | 8.7 |
| አላውቅም | 278 | 73.5 |
| በሌሎች አካላት በተፈጠረ ተፅዕኖ | 41 | 10.8 |
| ትምር | 378 | 100.0 |
| መልስ ጸለሰቷ | 2618 | |
| ቷቅላላ ትምር | 2996 | |

ከዚሁ ጋር በተያያዘ አሁን ባለው ሆኔታ ለሙስናና ለብልሹ አሠራር የተጋለጡ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ካሉ ቢገልፁን ለሚለው ጥያቄ የሚከተለውን ዘርዝረዋል፡፡

- ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣
- የአዲስ አበባ መስተዳድር፣ ክፍለ ከተሞች እና የክልል ከተሞች መሬት አስተዳደር፣
- ፍርድ ቤቶች፣
- ፌዴራል መንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን፣

- ባንኮች፣
- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን፣
- ፖሊስ ኮሚሽን (በየደረጃው ያለው)፣
- የኮንስትራክሽን ድርጅቶች (የመንግስት)፣
- የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን፣
- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣
- ቀበሌ መስተዳድሮች፣
- ክፍለ ከተማ መስተዳድሮች፣
- ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣
- የጤና ተቋማት (በተለይ ሆስፒታሎች፣)
- ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፣
- የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣
- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ፣
- የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣
- ኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ መምሪያ፣
- የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣
- የጥራትና ደረጃዎች መዳቢ ባለስልጣን ናቸው::

ከዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት ከአስር ዓመት በፊት በተካሄደው ሙስና ቅኝት ጥናት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአዲስ አበባ መስተዳደር ባሉት ክ/ከተሞች ስር □ሚቶኘው የመሬት አስተዳደርና ፍርድ ቤቶች ለህብረተሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት በ□ም □ካማ እንደሆነ የተገለፀ ሲሆን ከአስር ዓመት በኋላ እነዚሁ መ/ቤቶች ለሙስናና ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ እንደሆኑ (ከ1-3 ያለውን ተራ ቁጥር ይዘዋል) በቡድን ውይይት ተሳታፊዎች አመልክተዋል:: ይህም የሚያመለክተው ኮሚሽኑ በሚያካሄደው ፃረ-ሙስና ትግል ለነዚህ በአገሪቱ ውስጥ ቁልፍ ሚና ላላቸው የመ/ቤቶች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ □ንዳለበት ይህ ጥናት አመልካች ነው::

## 5.7 ስለ ኮሚሽኑ እንቅስቃሴ አጠቃላይ እይታ

ቀደም ሲል የሥነምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን 3 ዋና ዋና ተግባራት እንዳሉት ተገልጿል፡፡ እነዚህም የሥነምግባር ትምህርት መስጠት፣ የአሠራር ስርዓት ጥናት ማካሄድና ምርመራ፣ ክስና ቅጣት ናቸው፡፡ ከነዚህ 3 ተግባራት ውስጥ በኮሚሽኑ ባለፉት 9 ዓመታት ክንውን የተሻለ ውጤት የተገኘበት የትኛው ነው ለሚለው ጥያቄ 33 በመቶ የሚሆኑት (ማለት 841 ከ2567 መላሾች) የሥነምግባር ትምህርት የተሻለ ውጤት እንዳስገኘ ገልፀዋል፡፡ 40 በመቶ የሚሆኑት (ከ2567 ዉስጥ 1014 ሰዎች) ከመወሰን ተቆጥበዋል፡፡ ከመወሰን የተቆጠቡትን ትተን የሌሎች መላሾችን ብዛት ስናይ በአንደኛ ደረጃ የሥነምግባር ትምህርት እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ የአሠራር ስርዓት ጥናት ውጤት እንዳስገኙ መላሾች ገልጸዋል፡፡

ሠንጠረዥ 26 የተሻለ ውጤት ያመጣው የኮሚሽኑ ተፅባር

| የተሻለ ለውጥ የመጣው | በቁጥር | በመቶኛ | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|
| የስነምግባር ትምህርት (1) | 841 | 32.8 | |
| የአሠራር ስርአት ጥናት (2) | 298 | 11.6 | |
| ምርመራ፣ ክስና ቅጣት (3) | 46 | 1.8 | |
| መወሰን አልችልም (4) | 1014 | 39.5 | 2579.90* |
| ሁሉም ውጤት የላቸውም | 106 | 4.1 | |
| 1 እና 2 | 219 | 8.5 | |
| 1፣2 እና 3 | 43 | 1.7 | |
| ድምር | 2567 | 100.0 | |
| የተዘለለ | 429 | | |
| ጠቅላላ ድምር | 2996 | | |

* P<.01

በአጠቃላይ በማስተማር መልካም ስነምግባርን በማስረፅ ረገድ የኮሚሽኑ ውጤታማነት “በጣም አምናለሁ” ወይም “አምናለሁ” በማለት የመለሱ ሰዎች በርካታ ምክንያቶች አስቀምጠዋል፡፡ ከፊሎቹ ምክንያቶች ትምህርት በጥቅሉ የአስተሳሰብ ለውጥን ያመጣል ከሚል እምነት የሚመነጩ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል በርካታ ተሳታፊዎች የኮሚሽኑን ውጤታማነት በተጫባጭ ተገኝቷል ብለው ከሚያስቧቸው ለውጦች አንፃር ከትምህርት ጋር አያይዘው ገልፀውታል፡፡ በዚህ መሰረት መላሾቹ የሚከተሉትን ለውጦች የኮሚሽኑን ውጤታማነት ማሳያ ናቸው ብለው ጠቅሰዋቸዋል፡፡

- ኮሚሽኑ የሰጠው ትምህርት ሙስና ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ በማሳየቱ፣
- በሙስና ዙሪያ የህብረተሰቡ ግንዛቤ እየጨመረ በመምጣቱ/እጅግ በርካታ መላሾች የጠቀሱት፣
- ትምህርቱን በድራማና በጭውውት መልክ በመገናኛ ብዙሃን ማሰራጨቱ፣
- ትምህርቱ ሰዎች ወደ ሙስና ከመግባት እንዲቆጠቡ የማስጠንቀቂያ መልክክት በማስተላፉ፣
- የሙስና ወንጀል፣ ክስና ቅጣት በመገናኛ ብዙሃን በማስተላለፍ የህብረተሰቡን ግንዛቤ አሳድጓል /እጅግ በርካታ መላሾች/፣
- ትምህርቱ የሠራተኛውን አመለካከት እንዲቀየር በመርዳቱ፣
- ትምህርቱ መልካም የሥራ ባህል ማጎልበት አስችሏል፣
- የኮሚሽኑ ትምህርት፣ ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል የሚለውን አባባል አደጋ አሳይቷል፡፡

ኮሚሽኑ የሚሰጠው ፀረ-ሙስናና ስነምግባር ተኮር ትምህርት ወደፊት በምን መንገድ መካሄድ አለበት ለሚለው ጥያቄ በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው የጥናቱ ተሳ□ፊዎች ኮሚሽኑ ሠራተኞችንና የሥራ ኃላፊዎችን ወደሱ በመጋበዝ ትምህርቱን መስጠት እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡ በፀረ-ሙስና ዙሪያ የተዘጋጁ ጽሑፎችን በማሰራጨት የሚለው በጣም ጥቂት ቁጥር ያላቸው ተጠያቂዎች ናቸው ያመለከቱት፡፡ በሬዲዮና ቴሌቭዥን መልዕክቶችን በማስተላለፍ የሚለውን አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ተጠያቂዎች ቆልናዉ□ል፡፡

የጥናቱ ተሳ□ፊዎች ኮሚሽኑ ከመመስረቱ በፊት ያለውን ሁኔ□ ከአሁኑ ጋር በማወዉ□ር በትርፀ ታችሁ ውስጥ ሙስናና ኢ-ስነ ምግባራዊ ድርጊቶች በምን ሁኔ□ ላጁ ጁቐኛል ለሚለው ጥያቄ በርከት ያሉ በጥናቱ የተሳተፉ ሰዎች (32.3%) ሙስና ባለፉት 9

□መ□ት ቀንሷል በማለት የመለሱ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 24 በመቶ የሚሆኑት ሙስና ቀንሶአል ሲሉ 8 በመቶ በጣም ቀንሶአል ብለዋል፡፡ (ሠንጠረዥ 27ን ይመልከቱ)፡፡

ከመወሰን የተቆጠቡትን ትተን የሌሎችን መላሾችን ብዛት ስናይ ባብዛኛው፡ (በቁዓ ር 833) ሙስና ቀንሷል ወይም በጣም ቀንሷል ሲሉ አነስ (157) ያሉት ጨምሯል ወይም በጣም ጨምሯል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም አነስተኛ ቁዓ ር (150 ብቻ) ያላቸው ሙስና ላይ የ□□ ለውጥ የለም ብለዋል፡፡ ይኸ ግኝት ለፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ አበረታች ውጤት ነው፡፡

*ሠንጠረዥ 27 ባለፉት 9 ዓመታት ሙስና ስለመቀነሱና ያለመቀነሱ*

| ሙስና ቀንሷል | በቁጥር | በመቶኛ | $X^2$ |
|---|---|---|---|
| በ□ም ፊ ምሯል | 80 | 3.1 | |
| ፊ ምሯል | 77 | 3.0 | |
| መወሰን አልችልም | 1436 | 55.7 | |
| ቀንሷል | 627 | 24.3 | 3320.33 |
| በጣም ቀንሷል | 207 | 8.0 | |
| ለውጥ አላሳየም | 150 | 5.8 | |
| ትምር | 2577 | 100.0 | |
| □ተ□ለለ | 419 | | |
| ቷቅላላ ትምር | 2996 | | |

* P<.01

የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከተቋቋመ ወዲህ ብልሹ አሰራርንና ሙስናን ለመቀነስና ለመግታት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እንዴት ያዩታል ለሚለው ጥያቄ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ከ35 ተሳታፊዎች አምስቱ እንቅስቃሴውን ብዙም ጠንካራ ያልሆነ ወይም ችግር ያለበት አለያም መረጃ የሌላቸው መሆኑንና ጥናት አለማድረጋቸውን ስለዚህም ለመግለፅ እንደሚቸገሩ የተናገሩ ሲሆን አብዛኛዎቹ ግን በመልካም ሁኔታ እንደሚያዩት የሚከተሉትን በመሰሉ ቃላት ገልፀውታል፡፡ “ጅማሮው ጥሩ ነው”፣ “መልካም ነው”፣ “የሚያበረታታ ነው”፣ “ብዙ ጥቅም አስገኝቷል”፣ “ብዙ ጥሯል”፣ “በጣም ጥሩ እንቅስቃሴ አድርጓል”፣ እና በአጥጋቢ ሁኔታ ተንቀሳቅሷል” የሚሉት ናቸው፡፡

እነዚህ አወንታዊ ምላሾቻቸውንም በሚከተለው መልኩ በዝርዝር ገልፀዋል፡፡ ለምሳሌ አንድ የስራ □ላኝ እንዲህ ቶልናዉ□ል ሙስና ጠፍቷል እያልኩህ አይደለም ምክንያቱም ሙስና የሚሰራው በድብቅ እና ስራውን በሚያውቁ ሰዎች በመሆኑ፣ ይህም የኮሚሽኑን ስራ ከባድ ያደርገዋል፡፡ ነገር ግን ኮሚሽኑ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ በጣም ጥሩ ነው፡፡” ይህንኑ የኮሚሽኑን ጥሩ እንቅስቃሴ ግን የሚጠብቀውን ከባድ ስራ ሌላ አስተያየት ሰጭ ቀደም ሲል በሀገራችን በተለምዶ ወይም በሃይማኖት የሚከበሩ ብዙ እሴቶች እንደነበሩ በመግለፅ አሁን ግን ያ ተሸርሽሮ አብዛኛው ሰው ያገኘውን አጋጣሚ በመጠቀም ለዝርፊያ እንደተነሳ በመሆኑም ኮሚሽኑ ብዙ እንደሚጠበቅበት ገልፀው ኮሚሽኑም ጥሩ እንቅስቃሴ እያደረገ እንደሆነና እንቅስቃሴው መጀመሩ በራሱ አበረታች መሆኑን ገልፀዋል፡፡

አንዳንድ ተሳታፊዎች ሙስናን በተመለከተ የሚወጡት ፖሊሲዎች እና የሚሰጡት ውሳኔዎች በጣም ጥሩ እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ አንድ አስተያየት ሰጭ እንዲህ ብለዋል “በተለይ ህብረተሰቡን በጉዳዩ ዙሪያ ለማስተማር የሚደረገው ጥረት እጅግ የሚያበረታታ ነው”፡፡ ሌላው ተሳታፊ ከትምህርት ቁ□ ሳያስፈቅዱ መቅረት፣ ማርፈድ፣ እና የማርክ አያያዝ ችግር እንዲቃለል የኮሚሽኑ ትምህርት እንደረዳና በተለይም ከኩረጃ ጋር ተያይዞ እየተሰራ ያለው ነገር በጣም ጥሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ አንድ ሌላ ተሳታፊ በተለይ ህብረተሰቡን በማስተማር እና በማንቃት ረገድ የተዋጣለት ስራ ተሰርቷል ብለዋል፡፡ በመጨመርም የሰራተኞች ስልጠና፣ የአሰልጣኞች ስልጠና፣ የመስሪያ ቤቶችን አሰራር በመፈተሽና ሙሰኞችን በማስቀ□ት ዙሪያ መልካም ስራ እየተሰራ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ኮሚሽኑ ብዙ እንደሰራ የገለፁት አንድ ተሳታፊ አዎንታዊ ተግባሮቹን ሲገልፁ፤ በየመስሪያ ቤቱ የስነ-ምግባር ቢሮዎች መቋቋማቸውን፣ በየመስሪያ ቤቱ የባለሙያ እገዛ ማድረጉን፣ በመገናኛ ብዙሃን ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጡን፣ መመሪያና ደንቦች በማዘጋጀት በመሥሪያ ቤታቸውም እንዲተገብሩ ማድረጉን፣ ከሃይማኖት አባቶችና ሲቪል ማህበራት ጋር በጥምረት መሥራቱንና የመሬትና ወርቅ ማጭበርበር ሙስናዎችን በማጋለጥ አጥፊዎችን ለፍርድ እንዲቀርቡ መጣሩን

ጠቅሰዋል፡፡ በተለይ የፀረ-ሙስና ቢሮዎችና የስነ-ምግባር መኮንኖች በየመስሪያ ቤቶች መመደባቸውን እንደ መልካም ጅምር ሌሎችም ተሳታፊዎች ደጋግመው ገልፀውታል፡፡ ሌሎች ተጨማሪ በጐ አስተያየቶች የሚከተለውን ያካትታሉ፡፡

- ጥሩ ሙስናን የማጋለጥ ጅምር አለ ለምሳሌ በአዲስ አበባ መስተዳደር በመሬት አስተዳደር ላይ ያሉ ችግሮችን ማጋለጥ፣
- ረጅም ጊዜ እንቅስቃሴ ካደረጉ ሃገራት አንፃር ለምሳሌ ከማሌዥያና ሆንግ ኮንግ (36 ዓመት) ሲነፃፀር ኮሚሽኑ በአጭር ጊዜ ጥሩ እንቅስቃሴ አድርጓል፣
- ወንጀለኞች ላይ ተገቢው እርምጃ እየተወሰደ ነው፣
- ብዙ ችግሮች በግልፅ እየወጡ ነው ለምሳሌ በዩኒቨርሲቲዎች አካባቢ በተለይም በሂሳብ ክፍል የነበሩ ችግሮች ይፋ እየወጡ ነው፣
- ግብረ ገብነትና ፀረ ሙስና እንቅስቃሴዎች እየተጠናከሩ ናቸው፣
- የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ በተደጋጋሚ ተነስቷል፡፡ በሚዲያ ሰው ሙስና፣ ሰርቶ እስር ቤት ውስጥ ገብቶ ሲሰቃይ፣ ልጆች ሲበተኑ፣ ሙስና የሰራው ሲፀፀት፣ እኔን ያየህ ተቀጣ ሲልና በእንባ ሲታጀብ ወንጀል መስራት ምን ያህል አሰቃቂ እንደሆነ በሰው አዕምሮ እንዲመላለስ አድርጓል፣
- ህብረተሰቡ ጠንቃቃ እንዲሆንም አድርጐታል፣
- በፀረ-ሙስና ዙሪያ ስልጠናዎችን ስለመስጠቱም እንዲሁ በተደጋጋሚ ተነስቷል፣
- አንድ ተሳታፊ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ቢሮዎች በክልሎች እንደተቋቋሙ ገልፀው የእሳቸው መስሪያ ቤት ሲቪል ሶሳይቲ አንቲ-ኮራፕሽን ፎረም መመሥረቱን እና ከኮሚሽኑ ጋር በመሆን በቀበሌ ደረጃ የፀረ-ሙስና ክበብ በመመስረት ላይ መሆኑን ገልጿል፡፡ (የብሔራዊ ፀረ-ሙስና ጥምረት ተቋቁሟል፡፡) እንዲሁም በኮሚሽኑ ኮሚሽነር የበላይ ጠባቂነት የኮንስትራክሽን ሴክተር ትራንስፓረንሲ ኢኒሸቲቭ የሚል የሙከራ ፕሮግራም መተግበሩ፣

- የስነ-ምግባር ኦፊሰራቸው በማስረጃ የተደገፉ ሰነዶችን በማያያዝ ለዲሲፐሊን ኮሚቴ እያቀረበ መሆኑን (የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተሳታፊ) ገልፀዋል፣
- ከዚህ በፊት የአሰራር ሥርዓት አልነበረም አሁን ግን ሥልጠና፣ ሪፖርት፣ ግምገማ እና ምርመራም በመኖሩ ጥሩ ለውጥ እየታየ መሆኑን ተሳታፊዎቹ ገልፀዋል፣
- በአሁኑ ወቅት የሃብት ማስመዝገብ ስርዓት መጀመሩ በዜጎች ላይ ግልፅነትን ሊፈጥር ይችላል የሚል አስተያየት ተሰንዝሯል፣
- የመንግስት ሰራተኞች ጠንቃቃ እንዲሆኑ እያደረገ ነው፣
- ሙስናን የሚፀየፍ ህብረተሰብ በመፍጠሩ ረገድ አጥጋቢ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 28 በኮሚሽኑ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

| | በቁጥር | በመቶኛ | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|
| የስነምግባር ትምህርት (1) | 755 | 28.4 | |
| የአሠራር ስርአት ጥናት (2) | 403 | 15.2 | |
| መወሰን አልችልም (3) | 264 | 9.9 | 699.36* |
| ምርመራ፣ ክስና ቅጣት (4) | 71 | 2.7 | |
| 1 እና 2 | 559 | 21.0 | |
| 1፣2 እና 4 | 608 | 22.9 | |
| ድምር | 2660 | 100.0 | |
| የተዘለለ | 336 | | |
| ጠቅላላ ድምር | 2996 | | |

* P<.01

ወደፊት ኮሚሽኑ በስፋት መሥራት ያለበት ተግባር የትኛው ነው ለሚለው ጥያቄ አሁንም በትምህርት ዙሪያ (28 ከመቶ) ቢሠራ ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል አመልክተዋል፡፡ ይህም ሙስናን ለመዋጋትና ስነ ምግባርን ለማስፈን የትምህርት አስፈላጊነት ጉልቶ የታየበት ሁኔታን ያሣያል፡፡

በሠንጠረዡ ላይ የተጠቀሰው መረጃ በተጨማሪ እንደሚያመለክተው የአሠራር ሥርዓት ጥናት ማካሄድ ሊተኮርበት እንደሚገባ የገለጹት ሰዎች ብዛት (15.20 በመቶ) ትንሽ የማይባል ነው፡፡ ምርምራ ክስና ቅጣትን በተመለከተ ግን ለብቻው ወደፊት ሊተኮርበት ይገባል ያሉት ቁጥራቸው ትንሽ ቢሆንም (2.7 በመቶ) ከሥነ ምግባር ትምህርት እና ከአሠራር ሥርዓት ጥናት ጋር አብሮ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ያሉ ቁጥራቸው (22.9 በመቶ) ከፍ ያለ ነው፡፡ እነዚህን ግኝቶች አንድ ላይ ስናያቸው በቀዳሚነት የሥነ ምግባር ትምህርት በተከታይነት የአሠራር ሥርዓት ጥናትና በመጨረሻም ምርመራ ክስና ቅጣት ኮሚሽኑ በወደፊት ሥራው በተናጥልም ሆነ በቅንጅት ሊያተኮርባቸው እንደሚገባ ጸመለ□□ሉ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ተመሣሣይ ጥያቄ በቡድን ውይይት ለተሳተፉ የቀረበላቸው ሲሆን ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው ያሏቸውን የኮሚሽኑን ሥራዎች እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፡፡

- የስነምግባር ትምህርትን ለሕብረተሰቡ በስፋት ማስተላለፍ (ብዙ መላሾች የጠቀሱት)፣
- የሥነምግባር ትምህርትን በማስተላለፍ ረገድ የትምህርት ቤቶችንና የሚዲያን ሚና ማጎልበት፣
- በየመሥሪያ ቤቱ የአሠራር ሥርዓትን ማጥናትና ማሻሻል (ብዙ መላሾች የጠቀሱት)፣
- ለሙስና ተጋላጭ በሆኑ መሥሪጸ ቤቶች ላይ ክትትሉን ይበልጥ ማጠናከር፣
- ሕብረተሰቡ ሙስናን እንዲዋጋ ማስተባበር፣
- በየመሥሪያ ቤቱ የሥነ ምግበራና ፀረ ሙስና ዩኒት ማቋቋም፣
- የሙስና ወንጀልን የመመርመር፣ ወንጀለኞችን የመክሰስና የማስቀጣት እንቅስቃሴን ማጎልበትና በቀጣይነት ማጠናከር፣
- በተለይ በመሬት አስተዳደር ዙሪያ የተጀመረው ክትትልና ምርመራ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፣

- ኃብት የማስመዝገብ ተግባር ከኃላፊዎች በተጨማሪ ሌሎች ለሙስና ክፍተት በሚፈጥሩ ቦታዎች በተመደቡ ሠራተኞች ላይ በስፋት ተፈፃሚ ቢደረግ፣
- የሙስና ወንጀልን የሚከታተሉ ፖሊሶችና የፍትህ አካላት ራሳቸው ከሙስና የፀዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚሉ ናቸው፡፡

ኮሚሽኑ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ሙስና ባለፉበት 9 ዓመታት ቀንሷል ወይስ ጨምሯል ለሚለው ጥያቄ 24 ከመቶ (ማለትም 627 ተጠያቂዎች ከጠቅላላው 2577) መቀነሱን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ተጠያቂዎች (1436 ከ2577) መልስ መስጠት አልችልም በሚል ተቆጥበዋል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ 24 ከመቶ ሙስና መቀነሱን መግለፃቸው በኮሚሽኑ አበረታች እንቅስቃሴ ባለፉት 9 ዓመታት መካሄዱን ያሣያል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ብዛት ያላቸው መልስ አለመስጠታቸው ኮሚሽኑ ስለሚሠራቸው ሥራዎችና በሥራዎቹም ምክንያት ስለመጡት ለውጦች ብዙዎች በግልጽ አለማወቃቸውን ሲያሳይ ኮሚሽኑ በዚህም ረገድ ስለሚሠራቸው ሥራዎችና ስለውጤታቸው በጥናት የተደገፈ ገለፃ ማድረግ እንዳለበት ያመላክታል፡፡

በቢሮ አካባቢ ስለሙስና አደገኛነት ግልፅ ውይይት ይካሄዳል ወይ ለሚለው ጥያቄ 48.8 በመቶ የሚሆኑ ግልፅ ውይይት መኖሩን ያመለከቱ ሲሆን 37.9 በመቶ የሚሆኑ ውይይት የሚባል ነገር አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ጥያቄውን በአዎንታዊና በአሉታዊ የመለሱትን ብቻ ብንመለከት ከፍ ያለ (56.3 በመቶ) ቁጥር ያላቸው መላሾች አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ ከዚህ በመጠኑም ቢሆን ያነሰ (43.7 በመቶ) ቁጥር ያላቸው ሰዎች አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል:: በስታትስቲክስ እንደታየው የመጀመሪያዎቹ ከኋለኞቹ በጣም የበለጡ ናቸው ($\chi^2$=38.03,df=1,p<.01) ይህ ማለት አብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች ስለሙስና በመስሪያ ቤታቸው ግልጽ ውይይት እንደሚካሄድ አመልክተዋል ማለት ነው::

ይህ ግኝት የጥናቱ ተሳታፊዎች ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች ከመመረጣቸው አንፃር ስናየው በአንዳንድ መ/ቤቶች ግልጽ ውይይት እንደሚካሄድና በሌሎች ደግሞ ስለሙስና ግልጽ ውይይት እንደማይካሄድ ያሳያል:: ግልጽ ውይይት በመስሪያ ቤታቸው እንደሚካሄድ የገለፁት ሰዎች ብዛት ግልጽ ውይይት እንደማይካሄድ ከገለፁት ሰዎች ብዛት ጎላ ባለ

ሁኔታ የበለጡት ከፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ ከተመረጡ የጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል ነው:: አዎ ግልፅ ውይይት ይካሄዳል ብለው የመለሱ ለዚህም አመልካች የሆኑ ሁኔታዎችን ገልፀዋል፡፡ ዋና ዋናዎቹም ህብረተሰቡ ስለሙስና ያለው ንቃተህሊና መዳበር (21.4 በመቶ)፣ በሥራ ኃላፊዎች ስምምነት (19.2 በመቶ)፣ በኮሚሽኑ ጥረት (6.6 በመቶ)ና በሠራተኛው ግፊት (4.4 በመቶ) የሚሉ ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 29 በመስሪጸ ቤታቸው ውስጥ ስለ ሙስና ግልጽ ውይይት ስለመኖሩ

| ስለ ሙስና ግልጽ ውይይት አለ ወይ | በቁጥር | በመቶኛ | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|
| ግልጽ ውይይት ይደረጋል | 1350 | 48.8 | |
| ግልጽ ውይይት የለም | 1048 | 37.9 | 545.99* |
| መወሰን አልችልም | 370 | 13.4 | |
| ድምር | 2768 | 100 | |
| መልስ ጸልሰቷ | 228 | | |
| **ጠቅላላ ድምር** | **2996** | | |

* P<.01

በሌላ በኩል ደግሞ ኮሚሽኑ የሚሰጠው ትምህርት በሥነምግባር የተላበሰ ሠራተኛ ከመፍጠር አንፃር ውጤታማ ነበር ማለት ይቻላል ወይ ተብለው ተጠይቀው 62 በመቶ የሚሆኑት (1759/2813) አዎ ውጤታማ ነው ሲሉ 16.4 በመቶ የሚሆኑት ውጤታማ አይደለም 21 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ መወሰን አንችልም ብለዋል፡፡ ጁህም በካጁእስኬር ስታስቲክስ እንደታየው ኮሚሽኑ ውጤታማ ነው ብለው የሚያምኑት በእጅጉ ቁጥራቸው እንደሚበልጥ አሳይቷል::

ይህም ብልጫ በሁሉም መስሪያ ቤቶች (በትምህርት ቤቶች፣ በዩኒቨርስቲዎች፣ በፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በሲቪል ማህበረሰብና በመንግስት የልማት ድርጅቶች) ጸለ ልዩነት ተንፃባርቋል:: በተጨማሪም በአዎንታዊ የመለሱት በአሉታዊ ከመለሱት በእጅጉ እንደሚበልጡ በወንዶችም በሴቶችም ያለ ልዩነት ተንፀባርቋል::

ሠንጠረዥ 30 ኮሙሽኑ ስነ-ምግባርን በማስረፅ ውጤታማ ስለመሆኑ

| ኮሚሽኑ ውጤ□ማ ነው ብለው ያምናሉ | በቁጥር | በመቶኛ | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|
| አምናለሁ | 1759 | 62.5 | |
| አላምንም | 462 | 16.4 | 1088.16* |
| መወሰን አልችልም | 592 | 21.0 | |
| **ድምር** | 2813 | 99.9 | |
| መልስ ያልሰጡ | 183 | | |
| **ጠቅላላ ድምር** | 2996 | | |

* P<.01

ከዚህ ጋር በተያያዘ ኮሚሽኑ ሙስናን በመከላከል ረገድ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ያደረገው እንቅስቃሴ ውጤታማ ነበር ወይ ለሚለው ጥያቄ በጠቅላላ በጥናቱ ከተሳተፉት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ውጤታማነቱን በርግጠኝነት መናገር እንደሚችሉ ገልፀዋል፡፡ ጁህም ቁዓር በስታስቲክስ ሲሰላ ሌሎቹን ከመለሱት ከእያንዳንዱ በጅጉ እንደሚበልጥ ማየት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 31 ኮምሽኑ ሙስናን በመከላከል ውጤታማ ስለመሆኑ

| ኮምሽኑ ውጤታማ ስለመሆኑ | በቁጥር | በመቶኛ | $\chi^2$ |
|---|---|---|---|
| ውጢታማ ነበር | 1480 | 53.3 | |
| ውጢታማ አልነበረም | 575 | 20.7 | 508.99* |
| መወሰን አልችልም | 723 | 26.0 | |
| ድምር | 2778 | 100 | |
| መልስ ያልሰጡ | 218 | | |
| **ጠቅላላ ድምር** | 2996 | | |

* P<.01

በተጨማሪም ወንዶችም ሆኑ ሴቶች (የጥናቱ ተሳታፊዎች) ያለ ልዩነት ኮሚሽኑ ውጢታማ ነበር የሚሉት ኮሚሽኑ ውጤታማ አልነበረም ካሉትም ሆነ መወሰን አልችልም ብለው ከመለሱት በ□ፀቶ ጁበል□ሉ፡፡ በ□ህ ረቶት □ኖታ ልዩነት አለመታየቱን ያሳያል ማለት ነው፡፡

## 6. ማቷቃለጸ፣ መደምደሚያና አስተያየት

## 6.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዓላማ በፌዴራል የሥነ-ምፅባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ባለፉት ዘጠኝ □መታት በሥነ-ምግባር ትምህርት፣ በሙስና መከላከልና የሙስና ወንጀሎችን በመመርመር እና ለሕግ በማቅረብ የተሠሩ ሥራዎች በተቋማትና በህብረተሰቡ ዘንድ መልካም ሥነ-ምግባርን በማስረጽና የሙስና ችግሮችን በመቅረፍ ያስገኙትን የአመለካከት፣ የአስተሳሰብና የአሠራር ለውጦች ለመገምገም ነው፡፡

ይህን ዓላማ ለማሳካትም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከመነሻው በማስቀመጥ መልስ ለማፅኘት ጥረት አድርጓል፡፡

1. ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት በሥነ-ምግባር ትምህርት የተሠሩ ሥራዎች በተቋማትና በህብረተሰቡ ዘንድ መልካም ሥነምግባርን በማስረፅ እና ሙስናን የማይሸከም ዜጋን ከመፍጠር አኳያ ያመጡትን የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦች መፈተሽ፣
2. ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት ብልሹ አሠራርን እና ሙስናን በመከላከል የተከናወኑ ተግባራት በተቋማትና በህብረተሰቡ ዘንድ ያስከተሉትን የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦች መዳሰስ፣
3. ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት የሙስና ወንጀልን በመመርመር እና ለሕግ በማቅረብ የተሠሩ ሥራዎች በተቋማትና በህብረተሰቡ ዘንድ ያመጡትን የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ እና የአሠራር ለውጦች ለመዳሰስ፣
4. በተፅዕኖ ትንተናና በጥናቱ ግኝቶች መሠረት የፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን ጥንካሬዎች እና ጉድለቶችን ለመለየት እና
5. የጥናቱን ግኝቶች መሠረት በማድረግ የኮሚሽኑን የወደፊት አሠራር ለማሻሻል ናቸው፡፡

□ነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚረዱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ □□ሑአ መጠይቆች፣ ቃለመጠይቅ፣ የቡድን ውይይት እና የሰነዶች ትንተና ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመጠቀም ከፌዴራል መንግስት ተቋማት፣ ከፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅቶች፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ከሁለተኛ □ረጃ

ት/ቤቶችና ከመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ኃላፊዎችና ሠራተኞች መረጃዎቹ ተሰብስበዋል:: በሌላ አነጋገር መረጃው 210 ከሚሆኑ መስሪያ ቤቶች ከተመረጡ ኃላፊዎችና ሠራተኞች □ተቶኝ ነው:: መረጃዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ በአ□ዊ የተደገፉ መረጃዎች (quantitative data) ወ□ SPSS እንዲገቡ ተደርጓል:: ሌሎች መረጃዎች ማለትም በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት አማካኝነት የተገኙት መረጃዎች (Qualitative data) ደግሞ በተለየ መልኩ በ□ፀ ተቀናብረው በቃል ተተንትነዋል::

በአኃዝ የተደገፉም ሆኑ በአኃዝ ያልተደገፉ መረጃዎች ከተጠናቀሩ እና ከተተነተኑ በኋላ የሚከተሉትን ግኝቶች ጥናቱ አመላክቷል::

- ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ትምህርትና ሥልጠናን በተመለከተ ኮሚሽኑ የሚሰጠውን የአጭር ጊዜ ስልጠና 40 በመቶ የሚሆኑት የጥናቱ ተሳ□ፊዎች የሚያውቁ ሲሆን ቀሪዎቹ የዚህ ዓይነት ሥልጠና ለመስሪያ ቤ□ቸው ኃላፊዎችና ሠራተኞች አለመሰጠቱን ወይም መስጠቱን አለማወቃቸውን ገልጸዋል:: በኮሚሽኑ ትምህርት አሰጣጥ ዙሪያ አለ ያሏቸውን ችግሮች □ንዲገልጹ በተጠየቁት መሠረትም ተሳ□ፊዎች ትምህርቱ ተከ□□ይነት እና ዘላቂነት እንደሌለው፣ የትምህርቱ አቀራረብ ሳቢ አለመሆኑን እና በሬዲዮና በቴሌቪዥን ብቻ ከሚሰጥ ይልቅ ትምህርቱን በአካል ወደ ህብረተሰቡ ወርዶ መስጠት □ንዳለበት □ንዲሁም ሰው በብዛት በሚገኝባቸው □ንደ ትምህርት ቤቶችና የሀይማኖት ማራመጃ ቦ□ዎች በመሳሰሉ ተቋማት ሁሉ ትምህርቱ መሰጠት □ንዳለበት ገልጸዋል:: በተጨማሪም የትምህርቱ አሰጣጥ በማስ□ወቂያ መልክ የተዘጋጁትን ጨምሮ የተቀባዩን ዕድሜ ያላገናዘበና ለሁሉም አንድ ዓይነት መሆኑንና በተለይ በቴሌቭዥን ከሚተላለፉት አንዳንዶቹ ሙስናን □ንዴት መፈጸምና ማምለዓ □ንደሚቻል ለዐዋቂዎች ብቻ ሳይሆን ለልጆችም የሚያስተምሩ መሆናቸውን የጥናቱ ተሳ□ፊዎች ገልጸዋል:: በሙያው የሰለጠኑና የማስተማር ክህሎት ያላቸው ሰዎች ስልጠናውን ቢሰጡ የተሻለ ውጤት ስልጠናዉ ሊጸመ□ □ንደሚችልም ገልጸዋል:: በተጨማሪም ለስልጠናው የሚሆኑት ርዕሶች በጥንቃቄ ቢመረጡና በድራማ፣ በጭውወት፣ በዝማሬ እና በዶክመንታሪ ፊልም ቢቀርብ የተሻለ ውጤት ያመጣል ብለው እንደሚያምኑ፤

- የስልጠናውን ጊዜ በቂነት በተመለከተ ተሳታፊዎች የተለያየ ሀሳብ እንዳላቸው ግኝቱ ያሳየ ሲሆን ከፍ ያለ ቁጥር ያላቸው 74 በመቶ ተሳታፊዎች ጊዜው በቂ አለመሆኑን ወይም መወሰን እንደማይችሉ ገልጸዋል:: በዚህም ረገድ ኮሚሽኑ ሥልጠና ወደፊት ለመስጠት ሲያቅድ የጊዜውን በቂነት መመርመርና ማሻሻል እንዳለበት ጥናቱ ያመላክታል::

- ትምህርቱ ወይም ስልጠናው በመስሪያ ቤቶች ውስጥ መልካም ሥነ ምግባርን ለማሰረጽ ምን ያህል እንደረዳ እንዲገልጹ ተጠይቀው አብዛኞቹ (44 በመቶ) አዎንታዊ መልስ የሰጡ ሲሆን ሌሎች (41 በመቶ) እንዲሁ እርፅቷኛ መሆን እንደማይችሉ ገልፀዋል:: አዎንታዊ መልስ ከሰጡት መካከል ትምህርት ከተሰጠው ህብረተሰቡ የአመለካከት ለውጥ የማያመጣበት ምክንያት እንደሌለ፣ ኮሚሽኑ ከተቋቋመ በኋላ በህብረተሰቡ ዘንድ የአመለካከት ለውጥ እንደታየና በአንዳንድ መስሪያ ቤቶች እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች አስተማሪ እንደሆኑ በመግለጽ ስልጠናው ያመጣውን ለውጥ በማስረጃ አቅርበዋል::

- □ናረ-ሙስና ትምህርት ያገኙበትን ዘዴ ተጠይቀው አብዛኞቹ (43.9 በመቶ) የጥናቱ ተሳታፊዎች በሬዲዮና በቴሌቪዥን አማካኝነት ያገኙ መሆናቸውን ቆል□ዥል::

- ከተሳታፊዎች መልስ እንደታየው የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በ□መስሪጸ ቤቱ በማቋቋምና በማገዝ ኮሚሽኑ ያደረገውን አስተዋጽኦ አብዛኞቹ ከፍተኛ ወይም በጣም ከፍተኛ ብለው የገመገሙት ሲሆን በዚህ ረገድ ኮሚሽኑ ገና ብዙ ስራ መስራት እንደሚገባው ግኝቶቹ አመላክተዋል::

- ኮሚሽኑ በየመስሪያ ቤቱ የተለያዩ የሥራ ዘርፎች አሠራር ላይ ጥናት ማካሄድ አለማካሄዱን ተጠይቀው ጥያቄውን ከመለሱት ውስጥ 35 በመቶው ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ኮሚሽኑ የተለያዩ ጥናቶችን እንዳካሄደ ጠቁመዋል:: የጥናቶቹ ትኩረትም በዕቃ ግዥ፣ በፋይናንስ፣ በሠራተኛ አስተዳደር፣ በንብረት አጠቃቀምና ደንበኞች መስተንግዶ ላይ እንደነበር የጥናቱ ወጤት አሳይቷል:: በተጨማሪም 67 በመቶ የሚሆኑት ተሳታፊዎች ሙስናን ከመከላከል አንፃር የተደረገው ጥናት ጠቃሚ እንደነበርና ጥናቱም በጣም አስፈላጊ መሆኑን እንደሚያምኑበት ገልጸዋል::

- ኮሚሽኑ የሚያጠናቸው ጥናቶች እና የሚያቀርባቸው የመፍትሔ ሀሳቦች □ንዲተገበሩ የጥናቱ ተሳታፊዎች ካቀረቧቸው ሀሳቦች መካከል 1/ የአፈፃፀም ክትትል ማድረግ 2/ ለሰራተኞች የሚቀርቡትን የመፍትሔ ሐሳቦች በግልፅ ማሳወቅ እና 3/ ከሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል መድረክ ኮሚሽኑ ሊኖረው ይገባል የሚሉ ይገኙበ□ል::

- በኮሚሽኑ ምርመራ የሚያስፈልጋቸው ሙስና - ነክ ሁኔታዎች በመስሪያ ቤታቸው መከሰቱን ተጠይቀው አብዛኞቹ (44.8 በመቶ) መከሰቱን የገለፁ ሲሆን በቁጥር አነስ ያሉ (20.1 በመቶ) ተሳታፊዎች ግን እንዳልተከሰተ ጠቁመዋል:: ከዚህ በማያያዝም ኮሚሽኑ የሙሰኞችን ወንጀል መመርመሩን፣ መክሰሱንና ማስቀጣቱን ያውቁ እንደሁ ተጠይቀው 74% ያህሉ መልስ ያልሰጡ ሲሆን ከሰጡት ውስጥ ግን ኮሚሽኑ መመርመሩን እና መክሰሱን ግን አለማስቀጣቱን 26% ጸህሉ ቶል□ዥል::

- ኮሚሽኑ በድርጅቶች ውስጥ ሙስና ሲፈጸም መረጃ እንዴት ይደርሰዋል ለሚለው ጥያቄ ከመለሱት ውስጥ አብዛኞቹ (55.5 በመቶ) በጥቆማ መሆኑን ወጁም መረጽዉ እንደሌላቸው (22.7 በመቶ) ገልፀዋል::

- ከሦስቱ የኮሚሽኑ ተግባራት መካከል ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ክንውን ኮሚሽኑ የተሻለ ውጤት ያስመዘገበበት በየትኛው ነው ለሚለው ጥያቄ ብዙ ተሳታፊዎች 32.8 በመቶ በስነምግባር ትምህርት የተሻለ ውጤት ማስመዝገቡን ገለጸዋል:: ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ሙስና ስለመቀነሱ ወይም ስላለመቀነሱ ተጠይቀውም አብዛኞዎቹ 55.7 በመቶ መወሰን እንደሚያስቸግራቸው የገለጹ ሲሆን በተከታይነት ግን ሙስና በጣም መቀነሱን ወይም መቀነሱን የገለጹት 32 በመቶ ያህሉ ናቸው:: በተጨማሪ አንዳንዶች እንደገለፁትም ኮሚሽኑ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ በጣም ጥሩ እንደሆነ ካሰመሩበት በኋላ የሚጠብቀውም ገና ከባድ ሥራ እንዳለ ቷቁመኘል::

- በመጨረሻም አብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች ኮሚሽኑ ስነ - ምፅባር በማስረ□ ዉቷታማ መሆኑን 62.5 በመቶ ያመኑ ሲሆን ሙስናን በመከላከልም ረገድ ኮሚሽኑ 53.3 በመቶ ውጤታማ ነው ብለው እንደሚያምኑ ገልጸዋል:: በአጠቃላይ የጥናቱ ተሳታፊዎች የኮሚሽኑን

ውጤታማነት በተመለከተ የሰጡት ግምገማ አበረታች እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በዛ ያሉ ጥያቄዎች ላይ ግን ብዙ ተሳታፊዎች መረጃው እንደሌላቸው ወይም መወሰን እንደማይችሉ ገልፀዋል፡፡

## 6.2. መ□ም□ሚጸ

በአሀዛዊ መረጃም ሆነ በቃለ መጠይቅ ወይም በቡድን ውይይት ከተገኙት ምላሾች በመነሳት የኮሚሽኑን ውጤታማነት ከተነሱት ዋና ዋና ጥያቄዎች አንፃር እንደሚከተለው መደምደም ይቻላል፡፡

- የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርትና ሥልጠናን በተመለከተ ኮሚሽኑ በሰፊው መስጠቱን ይህም የተሻለ የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣቱን መረጃዎቹ አመልክተዋል፡፡ ነገር ግን በትምህርት አሠጣጥ ሂደቱ ላይ ክፍተቶች እንዳሉ ተጠቁሟል፡፡ ይህም የትምህርቱ ተከታታይነት ማነስ፣ ትምህርቱ ታች ድረስ አለመውረዱና ኃላፊዎችንና ሚዲያን ያተኮረ መሆኑ፤ በተለይም ከመዋዕለ ህፃናት ጀምሮ፣ በዕድርና በዕቁብ ወደ ሰፊ ህብረተሰብ አለመግባቱን መደምደም ይቻላል፡፡ እንዲያም ሆነ ትምህርቱ ሰፊ የሚባል የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣቱን ከመረጃዎቹ መደምደም ይቻላል፡፡ ስለዚህም ትምህርቱ ክፍተቶቹን በመሙላት ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት መሆኑን መደምደም ይቻላል፡፡ በአቀራረብ በኩል ግን ሙስናን ሊያስተምር የሚችልም ችግር እንዳለውና ልዩ ጥንቃቄ እንደሚያሻ ያሳያል፡፡

- በተለያዩ መረጃዎች የተገኘው ሌላው ውጤት ኮሚሽኑ ቢሮዎችን በተለያዩ መስሪያ ቤቶች ማቋቋሙ የሚያበረታታ ጅምር መሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን የዚህ ሥራ ተግባራዊ ውጤት የሆነው ሙስና መቀነስ ላይ የጐላ ለውጥ □ንደማይታይ ከመረጃዎቹ መደምደም ይቻላል፡፡ ኮሚሽኑ ብዙ ቢጥርም የሙስና ድብቅና ውስብስብነት ችግሩ ገና ሰፊ ጥረት እንደሚጠይቅ መረጃዎቹ አሳይተዋል፡፡ እንዲያውም ሙስና በአስደንጋጭ ሁኔታ መልኩን በመቀጸ□ር እየተካሄደ እንዳለ ከመረጃዎቹ መደምደም ይቻላል፡፡ ነገር ግን ይህ የኮሚሽኑን አለመጣር አመላካች አይደለም፡፡ ይልቁንም የኮሚሽኑ ጥረት □ሚበረታታ ነው የሚለው ጉልቶ ወጥቷል፡፡

- የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድ ግልጽነትና ተጠያቂነትን የማስፈን አሠራርን በተመለከተ የትምህርቱን ያህል የጐላ ባይሆንም ቀላል የማይባል ጥናቶችን ማካሄዱን ከመረጃዎቹ መደምደም ይቻላል። ነገር ግን የጥናቱ ተሳታፊዎቹ በአጠናኑ ሂደትና በሚጠኑት ጉዳዮች ላይ ጥያቄዎችን አንስተዋል።

- ኮሚሽኑ ብዙም ጠንካራ ሥራ አልሠራም የተባለው ማስቀጣት /ማስወሰን/ ላይ ነው።

- በጠቅላላው የዘጠኝ ዓመት እንቅስቃሴው በትምህርት በኩል በጣም ጥሩ የሚባል፣ በጥናት በኩል ደግሞ ጥሩ ፀምር □ሚባል እና ለፍትህ አቅርቦ ማስቀጣቱ ግን ብዙ የሚቀረው መሆኑ ከመረጃዎቹ መደምደም ይቻላል። በተወሰነ መልኩ ኮሚሽኑ እራሱን ማፅዳት እንዳለበትና በተለይ የበላይ ሹማምንትን ሳይፈራ መስራት እንደሚጠበቅበት የጥናቱ መረጃዎች አመላክተዋል።

## 6.3. አስተያየት (Recommendations)

በዚህ ጥናት ከተደረሰባቸው ግኝቶች እና መደምደሚያዎች በመነሳት የሚከተሉትን በኮሚሽኑ ሊተገበሩ የሚገባቸውን አስተያየቶች ለመሰንዘር እንወዳለን።

- ብዛት ያላቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደገለፁትና በልምድም እንደሚታወቀው ትምህርት አመለካከትን በመለወጥ መተኪያ የሌለው መንገድ ነው። ስለሆነም ትምህርቱ በተከታታይነት ወይም ዘላቂነት ባለው መንገድ ለሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች መዳረስ አለበት። ይህ ከተደረገ ሙስናን የሚጠየፍ እና በስነምግባር የጎለበተ ዜጋን በማፍራት ሙስናን ከስር መሰረቱ ማጥፋት ይቻላል፣
- ሌላው ኮሚሽኑ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያለበት በትምህርቱ አቀራረብ ዙሪያ ነው። ትምህርቱ የተለያዩ ተግባራዊ ልምዶችን እና ተሞክሮዎችን በማቅረብ ከተቻለ ስነ-ጥበባዊ በሆነ መልኩ ካልተቻለ ደግሞ የተለያዩ መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም በማያሰላችና ሳቢ በሆነ መልኩ መሰጠት ይኖርበታል። የትምህርቱ አሰጣጥ ዘዴም ከላይ ወደ ታች እና እውቀትን እና

መረጃን በማስተላለፍ መልኩ ሳይሆን አሳታፊና ውይይትን የተመረኮዘ መሆን ይኖርበታል፣

- በሚዲያ የሚተላለፉ ማስታወቂያዎችና ድራማዎች የጎንዮሽ አሉታዊ ውጤት እንዳይኖራቸው ጥንቃቄ ቢደረግ የተሻለ ይሆናል፡፡ ከመለቀቃቸው በፊት በየዘርፉ ያሉ ባለሙያዎች ግምገማ የሚያደርጉበት አሰራር ቢመቻች የተሻለ ይሆናል፡፡ እነዚህ የማስተማሪያ ስልቶች ጠቀሜታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሕብረተሰቡን ባህል እና ወግ ያገናዘቡና የተለያየ የዕድሜ ክልልን ያገናዘቡ ቢሆን የተሻለ ይሆናል፣

- የገፅ ለገፅ ስልጠና በሚሰጥበት ጊዜ አሰልጣኞች በዘርፉ ትምህርት ያላቸው፣የማስተማር ክህሎት እና ስልጠና ያላቸው እንዲሁም ሞዴል ሊሆኑ የሚችሉና ልምድ ያላቸው ቢሆኑ ትምህርቱ ለውጥ የሚያመጣ እንዲሆን የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል፣

- በየጊዜው ለተለያየ የህብረተሰብ ክፍል የሚሰጠው ትምህርት የማያስገኘውን ለውጥ ለማየት በተከታታይ ጥናታዊ ዳሰሳ ማካሄድ ቢቻል ጥሩ ነው፣

- ኮሚሽኑ በየመስሪያ ቤቱ የአሰራር ሥርዓት መሻሻል እንዲኖር የሚያስጠናቸው ጥናቶች እና የሚያቀርባቸው የመፍትሄ ሐሳቦች መተግበራቸውን ኮሚሽኑ ክትትል በማድረግ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ የአሰራር ጥናት በማድረግ እና የመፍትሄ ሐሳቦችን በመስጠት ኮሚሽኑ አበረታች ሥራ እያከናወነ እንደሆነ ይህ ጥናት ያመለክታል፡፡ ነገር ግን በጥናቱ መሰረት የሚቀርቡት የመፍትሄ አቅጣጫዎች ምን ያህል □□ተተገበሩ እንደሆነ ክትትል በማድረግ በኩል ክፍተት ስላለ በዚህ በኩል ሊታሰብበት ይገባል፡፡ ይህም እንዲሆን የመፍትሄ ሐሳቦችን ለሰራተኞች ማሳወቅ፤ የሙያ እገዛ ማድረግና ክትትል በማድረግ አስፈላጊውን □ርምጃ መዉሰት ይጠበቅበ□ል፣

- ከተነሳው ነጥብ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት በዚህ ጥናትም ሆነ ቀደም ብሎ በኮሚሽኑ በተካሄደው Corruption Survey □ንደተመለከተው የተወሰኑ

